# ፍኖተ ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ ሚያዚያ 30 ቀን 2004 ዓ.ም. ዋጋ ብር 6.00

2ኛ ዓመት ቅጽ.2 ቁ.41


የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!



## በህዝበ ክርስቲያኑ ላይ ያንዣበበ ምንም አይነት አደጋ እንደሌለ በቅን ልቡና ይረዳልን

ኢስሃቅ እሸቱ

7

# በነፃ አስተሳሰብ ላይ የተቃጣው ጥቁር ሽብር




2

## አንድነት በደቡብ ክልል ታላቅ ህዝባዊ ውይይት አደረገ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ (አንድነት) ፓርቲ በደቡብ ክልል ለሁለት ተከታታይ ቀናት ታላቅ ህዝባዊ ውይይት አደረገ፡፡ ፓርቲው ሚያዝያ 27 ቀን 2004 ዓ.ም. ወላይታ ዞን ዋና ከተማ በሚገኘው የሶዶ ዙሪያ ወረዳ አስተዳደር አዳራሽ ከአካባቢው ህዝብ ጋር መከሯል፡፡ በውይይቱ ላይም የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ጉዳይ ኃላፊ ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ፣ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ኢንጂነር ዘለቀ ረዲ፣ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ አቶ ተመስገን ዘውዴ፣ የፓርቲው የደቡብ ቀጠና ሰብሳቢ አቶ ዳንኤል ሺበሺ የደቡብ ቀጠና አደራጅ አቶ ግርማ አማረ እና ከኤዲቶሪያል ቦርድ አቶ ወንድወሰን ክንፌ ተገኝተዋል፡፡

በወላይታ ሶዶ ከተማ በተደረገው ውይይት ላይ የደህንነት ኃላፊዎችና አባላት ሰሌዳ በሌለው ሞተር ሳይክል እየተንቀሳቀሱ ወደ ውይይቱ የሚመጣውን ሰው ለመረብሽ ቢሞክሩም ህዝቡ ባሳየው ቆራጥነት ሊከሽፍ መቻሉ ተጠቁሟል፡፡ በተለይ የወላይታ ዞን የህዝብ አደረጃጀት ኃላፊ የሆኑት አቶ ንጋቱ ቡሽራ የአካቢው የአንድነት አባላትና አመራሮች በተሽከርካሪ መኪና ቅስቀሳ እያደረጉ ሳለ ገቢና ያለውን አመራር በእርግጫ

ወደ ገፅ 20 ዞሯል

## የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ስልጠና ባልጨረሱ ፖሊሶች ተደበደቡ

-በጥይትና በከባድ ድብደባ የተጎዱ ተማሪዎች ህክምና ላይ ናቸው

-የከተማው ነዋሪም ተቃውሞውን ተቀላቅሏል

ትላንት ለተቃውሞ በወጡ የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ታጣቂዎች በጥይትና በዱላ ጉዳት ማድረሳቸውን ምንጮቻችን ገለፁ፡፡

ከትላንት በስቲያ እሁድ ሚያዝያ 28 እና ትላንት ሰኞ ሚያዝያ 29 በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ግጭት ሊከሰት የቻለው ተማሪዎች ተጓደለ ያሉትን የምግብ ጥራት በመቃወማቸው እንደሆነ ምንጮቻችን ዘግበዋል፡፡ እሁድ ሚያዝያ 28 ከቀኑ 10፡30 ጀምሮ በተቀጣጠለው በዚህ ተቃውሞ አብዛኛው ተማሪ ቁጣውን የዩኒቨርስቲውን መስታወቶች በመሰባበር እንደገለፀ የሚናገሩት ምንጮቻችን ምሽት ላይ በድንገት ወደ ግቢው የገቡት ታጣቂዎች ተማሪዎቹ ላይ ከመጠን ያለፈ ኃይል በመጠቀም ጉዳት እንዳደረሱ ገልፀዋል፡፡

በወቅቱ በታጣቂዎች በተወሰደው እርምጃ ከ60 ያላነሱ ተማሪዎች መታሰራቸውና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ላይ ድብደባ እንደተካሄደ ታውቋል፡፡ በወቅቱ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ከፍተኛ የተኩስ እሩምታ የተሰማ ሲሆን ኢብራሂም መሀመድ የተባለ የ2ኛ አመት የማኔጅመንት ተማሪ በጥይት መመታቱ ታውቋል፡፡ ተማሪው በደረሰበት ከፍተኛ ጉዳት በደብረ ማርቆስ ሆስፒታል የህክምና እርዳታ በመከታተል ላይ እንደሚገኝ ፍኖተ ነፃነት ስፍራው ድረስ በመደወል አረጋግጣለች፡፡ ተማሪ ኢብራሂም መሃመድ በስልክ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፀው ከትላንት በስቲያ ምሽት ታጣቂዎቹ በቀጥታ በጥይት እግሩ ላይ መተው አቁስለውታል፡ ፡ ሌላው በታጣቂዎች ከፍተኛ ድብደባ የተፈፀመበት የ2ኛ አመት የማኔጅመንት ተማሪ

ወደ 16 ዞሯል

## የብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅትና የአሳታሚዎች ውይይት አደረጉ

- ውይይቱ እንዲቀጥል ቀጠሮ ተይዟል

የብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት በቅርቡ ባወጣው "የህትመት ሥራ ስታንዳርድ ውል" አስታዎች ከፍተኛ ተቃውሞ በማንሳታቸው፤ የማተሚያ ድርጅቱ ኃላፊዎች እና አሳታሚዎች በትላንትናው ዕለት ተገናኝተው ውይይት ማድረጋቸውን ምንጮቻችን ገለፁ፡፡ እንደ ምንጮቻችን ገለፃ "ማተሚያ ድርጅቱና አሳታሚዎች በተዘጋጀው ውል ላይ በርካታ

ወደ 13 ዞሯል

### ርዕዮት፣ ኤልሻዳይ፣ የአቶ መለስ ፎቶና የጊዮን ሆቴል ምሽት

11

### ከመንግስት መግለጫ በኋላም የሙስሊም ተቃውሞ ቀጥሏል

13

### የፖለቲካው ውጥረት ሩብ ጉዳይ?

4

### የሙስሊሞች ጉዳይ የኢትዮጵያ ጉዳይ፤ የህገመንግስት ጉዳይ የሁላችን ጉዳይ፤ የመለስ ዜናዊ ጉዳይ የራሳቸዉ ጉዳይ

6

# በነፃ አስተሳሰብ ላይ የተቃጣው ጥቁር ሽብር



ብስራት ወ/ሚካኤል
afrosonb@gmail.com

ሀገራችን ኢትዮጵያ 1960ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ካየቻቸው ፈታኝ ወቅቶች አንዱ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ የአንድ እናት ልጆች በቡድን ተከፋፍለው የቃየልን የክፋት ድንጋይ "ነጭ ሽብርና ቀይ ሽብር" በሚል በመወራወር የተጠፋፉበት ወቅት፡፡ የአንድ እናት ልጆች የሀሳብ ልዩነታቸው በእሳት በትር (በጠመንጃ) ለመፍታት የሞከሩበት፡፡ በወቅቱ "የአብዮት መፈንዳት" የሚባል ሂደት በሀገሪቱ በቀለማት ስያሜ የመጠፋፋት ለውጥን አንግቦ መጣ፡፡

ዜጐችም ሐሳባቸውንና ተቃውሞአቸውን እንዳያሰሙ በሶሻሊስት ፍልስፍና እመራለሁ ያለው መንግስት ህግ አወጣ፡፡ ይህንንም በመቃወም ከሀሳብ የበላይነት ይልቅ የጠብመንጃ የበላይነት አይሎ በየአቅጣጫው ወደትጥቅ ትግል ተገባ፡፡ ከዚያም የተሳካላቸው ሻዕቢያና ህወሓት በተለያዩ ሀይሎች ድጋፍ መንበሩን ቢቆናጠጡም ትርፉ ሀገር ማስገንጠልና መገንጠል ሆኖ እንዳረፈ ዛሬም ድረስ እየተነገረ ይገኛል፡፡

በለስ የቀናው ህወሓት በስሩ ሦስት ሌሎች አምሳያዎቹን በመፍጠር ራሱን ኢህአዴግ ብሎ በመሰየም በ1983 ዓ.ም መገባደጃ ላይ የመምራት ዕድል ገጠመው፡፡ በወቅቱም ለአራት ዓመታት (ከ1983-1987 ዓ.ም) "የሽግግር መንግሥት" ተቋቁሞ አቶ መለስ ዜናዊ የመሪነቱን ሚና ተጫወቱ፡፡ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ በሽግግር ወቅት ኢትዮጵያ ትመራ የነበረው በሻዕቢያ እንደነበር ነው፡፡ ለዚህም በወቅቱ አቶ መለስ የህወሓትንም ሆነ የኢትዮጵያን ጥቅም ከማስጠበቅ ይልቅ ለሻዕቢያ (ኤርትራ) ጥቅም ይኳትኑ እንደነበር የቀድሞ የትግል አጋሮቻቸው ያስታውሳሉ፡፡

## ጥርስ የሌለው ህገመንግስትና የመጨረሻው ዘመቻ

እንደ አለመታደል ሆነና ዓለም በሰለጠነበት ዘመን ኢትዮጵያውያን የፕሬስ ነፃነትን ለማረጋገጥና ለመተግበር የግድ 90 ዓመታት ወደኋላ ተመልሰን ዳግማዊ አፄ ምኒልክን "ተንስው ለፕሬስ" እንድንል እየተገደድን ነው፡፡

በእሳቸው አገዛዝ ዘመን ነፃው ፕሬስ እንዲያብብ ያበረታቱ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ በወቅቱ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ (የራስ ተፈሪ መኮንን/የአፄ ኃይለ ሥላሴ ንብረትነትን) ጨምሮ የህትመት የግል መገናኛ ብዙኃን ከ1890ዎቹ እስከ 1913 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለማስተዋወቅ ሞክረው እንደነበር የዶ/ር ንጉሴ ተፈራን የመመረቂያ ጽሑፍ ዋቢ በማድረግ በታህሳስ 1998ዓ.ም. በፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር(ETHIOPIAN MASSMEDIA PROFILE) በሚለው ስር ተጽፎ እናገኛለን፡፡ በሂደትም ራስ ተፈሪ የራሳቸውን ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በማቋቋም(አሁን ሳንሱር ለማድረግ የተዘጋጀው ማተሚያ ቤት) ወደ ንግስናቸው እየተቃረቡ ሲመጡ ብርሃንና ሰላም የሚባል ጋዜጣን እያሳተሙ እንዲሰራጭ ያደርጉ እንደነበር አይዘነጋም፡፡

አፄ ኃይለ ሥላሴ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ የግል ጋዜጦች እንዲኖሩ እንዳላበረታቱ መረጃዎች ቢያስረዱም በእሳቸው ምትክ የተተኩትም ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያምም የፕሬስ ነጻነት ከመቃብር በታች እንዲሆን አድርገውት ነበር፡፡በወቅቱ አሁን ፒያሳ አቡነ ጴጥሮስ ኃውልት ፊትለፊት የሚገኘው አዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ዋና መ/ቤት ያኔ ሳንሱርና ምርመራ ክፍል እንደነበር ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ በኮሎኔል መንግስቱ የተተኩት አቶ መለስ ግን ወደ መንበረ ስልጣን ሲመጡ መተግበር ባይችሉም በ1984 ዓ.ም ቃል ገብተው ነበር፡፡ በሽግግር መንግሥቱ ወቅትም የዛሬው አቶ መለስ ያኔ(በ1984 ዓ.ም) ኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደሚረጋገጥላቸው፤ በቀን አንዴ ሳይሆን ሦስቴ እንደሚመገቡና የሰብዓዊ መብቶች መከበርና የፕሬስ ነፃነትም እንደሚረጋገጥ በቃልም ሆነ በጽሁፍ መረጋገጡ ይነገር እንደነበር የሚሰወር አይደለም፡፡ እውነታው በነበር ቀርቷል እየተባለ ቢሆንም፡፡

ይህንንም ኢህአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ የፕሬስ ነፃነት በአዋጅ 34/85 አረጋግጫለሁ በማለት ካስነገረ በኋላ በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 29(3) ሀ እና ለ ላይ "የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙኃን እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል፡፡ የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፤

ሀ. የቅድመ ምርመራ (ሳንሱር) በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣

ለ. የህዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት ዕድልን ያካተተ" በሚል በግልፅ ተቀምጧል፡፡

በዚህም ምክንያት ዜጐች ሰው በመሆናቸው ብቻ የሚያገኙትን ሰብዓዊ መብት "ሐሳባቸውን በነፃነት የመግለፅ መብት" እና ዴሞክራሲያዊ የሆነውም ደግሞ የሚገለፁ ሐሳቦች የኪነ ጥበብ መንገድን ጨምሮ በማንኛውም መንገድ መግለፅ እንደሚችሉም በማከል፡፡ በተለይ በመገናኛ ብዙኃን የሚንሸራሸሩ ሐሳቦች በማንኛውም መልኩ የቅድመ ምርመራ( ሳንሱር ) ሥራ መከልከሉና ዜጐች መረጃ የማግኘት ዕድል መከበርም ጭምር እንዲሁ፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ከላይ የተጠቀሱት መብቶች በትንሹም ቢሆን የሰሩት እስከ ምርጫ ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ ብቻ ነው፡፡ የዚህ ዋነኛ ምክንያት ደግሞ በወቅቱ የነበሩ ነፃ ጋዜጦች (ፕሬሶች) የኢህአዴግን ብልሹ አሰራር በማጋለጥ፤ በነበረው ምርጫ ላይ ትልቅ ሚና በመጫወታቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡

እስከ ምርጫ 1997 ዓ.ም. መገናኛ ብዙኃን (የነፃው ፕሬስ) ቁጥር ካለው የሕዝብ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝና በቂ ባይሆኑም ብዙ እንደነበሩ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ በመጨረሻም በበቀል ስሜት በተለይ ነፃው ጋዜጣ (የግሉ ፕሬስ) መካነ መቃብር ተበጀለት፡፡ ጋዜጠኞችም ግማሾቹ ሲታሰሩ ቀሪዎቹ የስደት ሰለባ መሆናቸው አይዘነጋም፡፡

በህገመንግስቱ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ የመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 አንቀጽ 4 "መገናኛ ብዙኃን ነፃ ስለመሆናቸው" በሚለው ስር ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ "የመገናኛ ብዙኃን ነፃነት በህገ መንግስቱ ዕውቅና አግኝቷል፡፡ ቅድመ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ ነው፡፡" ይላል፡፡ ይህ ማለት ማንኛውም ግለሰብም ይሁን ተቋም ቅድመ ምርመራ ማድረግ እንደማይችል በግልፅ ያረጋግጣል፡፡ እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ቢሆንም፡፡

ሌላው የመገናኛ ብዙኃን ነጻነትን በሚመለከት በአዋጅ 590/2000 አንቀጽ 2 ላይ ደግሞ "በመገናኛ ብዙኃን ነፃነት ላይ ገደቦች የሚጣሉት ህገ መንግስቱን መሠረት በማድረግ በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል" ይላል፡፡ ይህ ማለት ማንኛውም ህግ ሲወጣ ህገ መንግስቱን መሠረት ማድረግ መሆን እንዳለበት በግልፅ ያመለክታል፡፡

ነገር ግን በቅርቡ የመንግስት መስሪያ ቤት የሆነውና "ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት" አይመለከተኝም በሚል እሳቤ በተለይ የመገናኛ ብዙኃን (የፕሬስ) ነፃነት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 29(3) ላይ የተቀመጠውን "የህትመት ሥራ ስታንደርድ ውል" በሚል አዲስ ህገ መንግስቱን በግልፅ የጣሰ ሰነድ አዘጋጅቷል፡፡ ይህም "ህግን የተላለፈ ይዘትን አለማተም" በሚለው ስር ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ "አታሚው (ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት) በአሳታሚው (በጋዜጣ፣መፅሔትና መፅሐፍ አሳታሚዎች) እንዲታተም የቀረበለት የፅሑፍ ስክሪፕት ህግን የሚተላለፍ ስለመሆኑ ለማመን በቂ ምክንያት ካለው አላትምም የማለት መብት አለው፡፡" ይላል፡፡ ይሄ ደግሞ በግልፅ ቅድመ ምርመራ(ሳንሱር) መሆኑን ያሳያል፡፡

የሚገርመው ከህገ መንግስቱ ጋር የሚጋጭና የሚፃረር ማንኛውም ህግ፣ ደንብም ሆነ መመሪያ ተቀባይነት እንደሌለውም በህገመንግስቱ አንቀጽ 9(1) ላይ "የህገ መንግስት የበላይነት" በሚለው ስር ንዑስ አንቀጽ (1) "ህገ መንግስቱ የሀገሪቱ የበላይ ህግ ነው" ይላል፡፡ ማንኛውም ህግ ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም" ተብሎ በግልፅ ተቀምጧል፡፡

ምንም እንኳ በወረቀት ላይ ተፅፎ የቀረ ህገ መንግስት ቢሆንም፡፡ ከዚህ በፊት የፕሬስ አዋጅ፣ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶ አዋጅን ጨምሮ ጠቅላይ ሚኒስትሩና የተለያዩ የኢህአዴግ ባለስልጣናት ህገ መንግስቱን ሲጥሱ በተደጋጋሚ ቢታይም፣ የተወሰደባቸው ርምጃ ግን አልነበረም የሚል ሰሚ ያጣ አቤቱታ መኖሩ ባይካድም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ እነሱ ከህግ በላይ በመሆናቸው እና ህገመንግስቱ ማስፈራሪያ እንጂ የዜጐች የጋራ የቃልኪዳን ሰነድ እንዳልሆነ በሚያሳብቅ መልኩ እየተንፀባረቀ ይገኛልና፡፡

ለዚህም ማስረጃነት በሀገሪቱ እውነት ህግ የሚከበርና ህገ መንግስት የሀገሪቱ የበላይ ህግ ቢሆን ኖሮ ብርሃንና ሰላም (የመንግስት መስሪያ) ቤት ሳንሱር የሚያደርግ አዲስ ውል ተፈጻሚ ሊያደርግ ባልደፈረ ነበር፡፡ነገር ግን ውሉ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ስም ይምሰል እንጂ መመሪያው የተላለፈው ከአቶ መለስ ዜናዊ አሊያም ከአቶ በረከት ስምዖን እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይሄ ደግሞ በህግ ፈቅዶ በማተሚያ ቤት መከልከል ስጋ ሰጥቶ ቢላዋ እንደመከልከል ይቆጠራል፡፡

ሌላው በዚሁ ውል አንቀጽ 10(2) ላይ ደግሞ "አታሚው (ብርሃንና ሰላም) አሳታሚው የህግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል የህትመት ይዘት የማውጣት ዝንባሌ ያለው መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ካለው በማናቸውም ጊዜ ውሉን ለማቋረጥ ወይም ለመሰረዝ ይችላል፡፡" ይላል፡፡ይሄም ግልፅ አይደለም፡፡ምክንያቱም ዋና አዘጋጅን ጨምሮ በህትመቱ ላይ የሚሳተፉት ጋዜጠኞችና አሳታሚው ቀድሞም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት እንዳለበት በህግ ተደንግጓልና፡፡ ነገር ግን ብርሃንና ሰላም አዲስ ላመጣው ውል መልስ "ሃያ ጅቦ ሳታመሃኝ ብላ" አይነት ነገር መሆኑ ግልፅ ነው፡፡አሁን ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት እንደራሴ ሆኖ እየገበረ ያለው የኢህአዴግን አዲስ የታወጀውን የመጨረሻ ዘመቻ የሚያሳይ ይመስላል፡፡

## የዴሞክራሲ ካባ፣ ዕርዳታና የጨለማው ጉዞ

ኢህአዴግ የቅንጅት ተወዳዳሪዎችን በተለይም ከፍተኛ አመራሮች ጋር የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞችን ማሰሩ ከፍተኛ ዋጋ በማስከፈል አስደንግጦት ነበር፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ሳይወድ በግድ የዴሞክራሲ ስርዓትን እገነባለሁ ብሎ መድረሻው ባይታወቅም በዴሞክራሲያዊ ካባ ስም ዕርዳታ ይቀበላልና፡፡ ከዚያም በበቀል የሄደበት ስሜት እንዳላዋጣው ሲረዳ የተሰደዱትን መመለስ ባይችልም የታሰሩትን የፖለቲካ አመራሮችን ሲፈታ ጋዜጠኞችንም ለቋቸዋል፡፡ ከተፈቱት አንዳንድ ጋዜጠኞችም በድጋሚ ጋዜጣ እንዳያሳትሙ ተደርገዋል፡፡ወደ ህትመት ስራ የገቡት ላይም አሳሪ ህግ ከማውጣት በተጨማሪ ከፍተኛ የሆነ የማተሚያ ዋጋ እንዲጨምር መደረጉ አይዘነጋም፡፡

ቀስበቀስም በዴሞክራሲ ስም የሚመጣው እርዳታ እንዳይነጥፍ ጋዜጠኞችንና ፖለቲከኞችን ከመሬት ተነስቶ ማሰር ስለማያዋጣ እንቅስቃሴያቸውን ለመገደብ የሚያስችል ህግ በማውጣት አማራጭ የሌለው መሆኑን በማሰብ ገዥው ፓርቲ ተግብሮታል፡፡ ለምሳሌ ከህገመንግስቱ ጋር የሚፃረሩ በርካታ አንቀጾች እንዳሏቸው የሚነገርላቸው "የነፃው ፕሬስ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የፀረ ሽብርተኝነት እና የበጎ አድራጎት ማኅበራጽ አዋጆች" ከምርጫ 1997 ዓ.ም ምርጫ በኋላ የወጡ አሳሪ ህጎች ናቸው የሚሉ አልታጡም፡፡

ይሄንንም አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች በተለይ ኢህአዴግ በሀገሪቱም ሆነ በህዝቡ ላይ በርካታ በደሎችን፣ ከህደትንና ሙስና ስለፈፀመ ከስልጣን ቢወርድ የሚመጣበትን መዘዝ በማሰብ ዜጐችን ከመካስ ይልቅ አመራሮቹ እስከ ፍጻሜ ለመቆየት ያወጡት ህግ እንደሆነ ይደመድማሉ፡፡

በነዚህም ምክንያት ኢህአዴግን ጠንቅቀው የሚያውቁና በእጅጉ የሚግደረደሩ ናቸው የተባሉና እስከዛሬም ድረስ የሚፈራቸው አንዳንድ የቀድሞው የቅንጅት አመራሮችም በሀገር ውስጥ "የዴሞክራሲ ሥርዓት አብቅቶለታል፣ ይሄንንም በምርጫ ተወዳድሮ መቀየር አይቻልም፣ ኢህአዴግ በምርጫ ቢሸነፍም ስልጣኑን የመልቀቅ ፍላጐት የለውም" በማለት ወደሌላ የትግል ስልት (ኢህአዴግ የመጣበትን) መንገድ የተከተሉም አሉ፡፡

ይሁን እንጂ ገዥው ፓርቲ በበኩሉ "የለም! በሀገሪቱ የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲገነባ እየጣርኩ ነው፤ የመደበለ ፓርቲ ሥርዓት እውን እንዲሆንም እየሰራሁ ነው" ሲል በመሞገት በዴሞክራሲ ስም የሚመጣውን ዕርዳታ እንዳይነጥፍ የሚታገል ይመስላል፡፡ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በበኩላቸው "ህገመንግስቱ በአዋጅ እየተሸረሸረ እልቋል፤ የዴሞክራሲ ሥርዓትም ሆነ የመደበለ ፓርቲ ሥርዓት እያከተመ ምህዳሩ እየጠበበ ነው" በማለት ራሱ ኢህአዴግ የሚሰራውንና የሚናገረውን ዋቢ አድርገው ይጠቅሳሉ፡፡ የአባሎቻቸውን መታሰርንም በማስታወስ፡፡

ከላይ ለተጠቀሱ ሐሳቦች ማጠናከሪያም የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞችም በህገ መንግሥቱ የተፈቀዱ መብቶች በአዋጅ መሻራቸውንና መጭው ጊዜ አስፈሪ መሆኑንም ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ለምርጫ 2002 ዓ.ም ለኢህአዴግ ስጋት ናቸው የተባሉ ፖለቲከኞች ለምሳሌ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር የነበሩት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በወቅቱ መታሰራቸውና የአዲስ ነገር ጋዜጣ ከምርጫው በፊት እንዲዘጋ በማድረግ ጋዜጠኞቹ ከእስር አምልጠው መሰደዳቸውንም የሚያስታውሱ አሉ፡፡

## ስጋት ያንጃበበት ፍርሃት

የተፎካካሪ ፖለቲከኞች እንቅስቃሴ መቀዛቀዝ፣ ማቆሚያ የሌለው የዋጋ ግሽበት፣ ሃይ ባይ የታጣለት የምግብ እና የሌሎች መሠረታዊ ፍጆታዎች ዋጋ መናር፣ በነጋዴዎች ላይ ከልክ ያለፈ የግብር ጫና፣ የወጣቱ ሥራ አጥነት፣ የኢህአዴግ የጭፍን ጉዞ እና የቀጠናው አለመረጋጋት ለህዝቡ ትልቅ ስጋት መሆናቸውን የሚናገሩ አልታጡም፡፡ ይህም አውነትም "ጥቁር ሽብር" ይመስላል፡፡ በሀገሪቱም ባለው የገዥው ፓርቲ አፋኝነት በተፈጠረው የመልካም አስተዳደር እጦት እና የኑሮ አለመረጋጋት መምህር የኔሰው ገብሬ፣ ታጠቅ ሀሉፍ የጠባለ የመከላከያ ሠራዊት አባል፤ እና በቅርቡም ምኒሊክ አደባባይ (አራዳ ጊዮርጊስ) ፊት ለፊት ጨምሮ አንድ ዳዊት የሚባል የፖሊስ አባል ራሳቸውን ማቃጠላቸው "የጥቁር ሽብር" ሌላው ማሳያ እንደሆነ የሚገልፁም አሉ፡፡

ከዚህ በፊት ዜጐች "ነጭ ሽብር ቀይ ሽብር" በሚል የመጠፋፋት ፍልስፍና በሀገሪቱ መተግበሩን በማስታወስ አሁን ያለው ከዚህ የተለየ ይመስላል፡፡ ዜጐች ባለው ስርዓት ሲማረሩ ራሳቸውን ባሰቃቂ ሁኔታ ማጥፋት የሰዎች ያልተለመደ ዝምታ (በታመቀ ስሜት) መታየት፣ የርሃብ መበራከት ይህንንም በይፋ ያለመግለፅ፣ የምግብ ዋጋዎች መናር፣ የተለያዩ የመንግስት ተቋማት (ፍ/ቤት፣ ፖሊስ፣ . . . እና

ወደ 20 ዞሯል

**When you want cargo delivered safely, on time and within your budget, call Global Trade and Logistics, LLC**

**GTL** Global Trade and Logistics, LLC
Worldwide Shipping and Trade

— Air and Ocean Shipping —




- አስከሬን በኢትዮጵያዊ ባህልና እንክብካቤ ከማናቸውም ከተማ ወደ ኢትዮጵያ በዝቅተኛ ዋጋ ማጓጓዝ፤
- ተሽከርካሪ መኪናዎችን፤ ትላልቅ የማምረቻ መሣሪያዎችንና የቤት ዕቃዎችን በጥንቃቄ የሚፈለገው ቦታ ማድረስ፤
- ሌሎች ማናቸውንም ዕቃዎች ባየርና በመርከብ ማጓጓዝ።
- የንግድ ሸቀጦችን ወደ አሜሪካን አገር ማስገባት፤ ወደ ኢትዮጵያም ለሚላኩ ሸቀጦችም አስፈላጊውን ሠነድ ማዘጋጀት፤
- ወጪና ገቢ ሸቀጦችን በመጋዘን ማቆየት፤
- የጉምሩክ፤ የFDA እና የ trade mark ሥራዎችን ማከናወን።



**Please contact us at the following Tel. Nos for price quote service**
**Global Trade and Logistics, LLC (GTL)**
**(703) 658-4320 / Toll Free: 1-855-60-cargo (22746), Fax (703) 354-4638 / Cell (703) 798-5395**
**E-mail: meri.demeke@gmail.com**



ታሪክ ፡ ይዳኘው




የመጽሐፉ ዋጋ
$25.00

መላኪያ
$5.00

አድራሻ
Dibu Wolde
P. O. Box 351
Marlborough, CT 06447

enbstv@hotmail.com

**Mark**
**Tax Service**
**ማርክ**
**የታክስ አገልግሎት**



ማግኘት የሚገባዎትን ገንዘብ በሙሉ እናስመልስልዎታለን

ለ2011 ታክስ ፋይሊንግ ፍላጎትዎ
ማርክ የታክስ አገልግሎት

Mark
ታክስን በተመለከተ ለሚነሱ ማናቸውም ጥያቄዎች ቢሮዎቻችን ዓመቱን ሙሉ ክፍት ሆነው ሊያገለግልዎ዗ዝግጁ ናቸው።

በሥራችን ላይ እምነት አሳድረው የአገልግሎታችን ተጠቃሚ በመሆንዎት ከልብ እናመሰግናለን።

Cell:
202 253 4414

AUTHORIZED e-file PROVIDER

Thank you for selecting MARK tax service to file your taxes

Alexandria VA
6303 Little River Turnpike Suite 160
Alexandria, VA 22312
Tel. 703 256 9113

Washington, DC
4526 Georgia Ave. NW
Washington, DC 20011
202 541 7979

Booth rent available

Opening for experianced barber / hair stlist

*Marakie Unisex Salon*
ማራኪ የቁንጅና ሳሎን

ሹሩባ እንሠራለን



- *Highlight*
- *Relaxer / Touch up*
- *Color*
- *Treatment*
- *Barbering*
- *Hair cut*
- *Cornrow / Barbering*
- *Eyebrow wax*
- *Trim*
- *Flex rod*
- *Flat iron*
- *Updo*
- *Weave/Extension*
- *Wrap & curl...*

ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች በተመጣጣኝ ዋጋ እናስውብታልን

የወንድ ፀጉር እንቆርጣለን

*Tel: 202 541 7979, Cell: 202 309 0674*
*4528 Georgia Ave. NW Washington, DC 20011*
*@ the corner of Buchannan & Georgia*
*Next to Mark computer*

Mark **COMPUTER**
- Training
- Sales - New & Used
  - Lap Top / Desk Top
  - Software
  - Accessories

SHOW ROOM INSIDE
- Repair Service
- Upgrades

Mark **ACCOUNTING**
- Business Consultation
- Payroll Preparation
- Bookkeeping

ወደ ማንኛውም አገር ገንዘብ እንልካለን

Mark **TAX SERVICE**
Fast, Accurate and Confidential Service
- Tax Preparation
- E-Tax Filing (FREE)
- Tax Consulation
- Fast Refund

ታክስን እኛ ዘንድ ያሠሩ

የፋክስ አገልግሎት (ዓለም አቀፍ)
የፎቶ ኮፒ እና የህትመት
የስካኒንግ
የኢንተርኔትና
የኮምፒውተር አገልግሎት
Fax, copy, printing, scanning internet and computer service

በልዩ ፕሮግራም
በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ
ያለ አስተማሪ
የሚያስተምር
ሶፍት ዌር በማስጫን
በተመቻችዎት ጊዜ
ራስዎን ያስተምሩበት

የኢሚግሬሽን ፎርም እና የውክልና ወረቀት እንሞላለን

- ለንግድ ሥራ ማማከር
- ኮምፒውተር ስልጠና
- ኮምፒውተር ጥገና
- ኮምፒውተር ሽያጭ
- ገንዘብ መላክ

Cell: 202 253 4414

AUTHORIZED e-file PROVIDER

Mark
ታክስን በተመለከተ ለሚነሱ ማናቸውም ጥያቄዎች ቢሮዎቻችን ዓመቱን ሙሉ ክፍት ሆነው ሊያገለግልዎ ዝግጁ ናቸው።

Washington, DC
4526 Georgia Ave. NW
Washington, DC 20011
202 541 7979

Alexandria VA
6303 Little River Turnpike Suite 160
Alexandria, VA 22312
Tel. 703 256 9113

# የፖለቲካው ውጥረት ሩብ ጉዳይ?

ነብዩ ኃይሉ

ለአፍታ የኢትዮጵያን ወቅታዊ የፖለቲካ ድባብ በአይነ ህሊናው ላስተዋለ፣ዙሪያ ገባውን እያገጣጠመ ላሰላሰለ በጊዜ ርዝመት የተብላላ፣ በብሶት ታምቆ በተቃውሞ የተወጠረ ፖለቲካዊ ድባብ እንዳለም ለማስተዋል አይቸግረውም፡፡ በህብረተሰቡ ውስጥ አንዳንዴ በአርምሞ ሌላ ጊዜ በለሆሳስ የሚንሸራሸሩት የታመቁ ተቃውሞዎች ዘርፈ ብዙ ናቸው፡፡ ለዚህ እትም «ሩብ ጉዳይ» ላይ የደረሱትንና በጊዜ ተገቢ ምላሽ/የማረሚያ እርምጃ ካልተሰጣቸው ሀገራዊ አደጋ የሚጋብዙትን በብሔርና በሐይማኖት ዙሪያ ያረበቡ ውጥረቶች ለመዳሰስ እንሞክር፡፡

## ኢህአዴግ የዘራው የዘውገኝነት በሽታ

«አማራ ማየትም. . . ስለ አማራ መስማትም አልፈልግም፤ ደቡብ ለደቡቦች!» ይህን የመሰለውን ጎምዛዛ ንግግር አንድ ቀሽም ግለሰብ ለዋዛ ሲናገረው ቢሰማ ያበሳጫል፡፡ ከአንድ ባለስልጣን አፍ ሲወጣ ቢሰማስ? አስቸጋሪ ጥያቄ፡፡ ይህን በጥላቻ የጎመዘዘ ንግግር የተናገሩት በደቡብ ክልል ቤንች ማጂ ጉራፈርዳ የአማራ ተወላጆች ሀብት ንብረታቸውን ጥለው እንዲፈናቀሉ በማድረግ ስራ የተጠመዱ አንድ የፀጥታ ኃላፊ ናቸው፡፡ ግለሰቡ ይህን የተናገሩት ከጉራፈርዳ የአማራ ብሔር ተወላጆች በሚፈናቀሉበት ወቅት እንደ ነበር የአካባቢውን ሁኔታ በቅርብ ሲከታተል ከነበረ ጋዜጠኛ ተረድቻለሁ፡፡ የሰብአዊ መብት እና የህግ አዋቂዎችም በስፍራው የዘር ማጥራት ዘመቻ እየተደረገ እንደሆነ ይከሳሉ፡፡

ለመሆኑ ዘር ማጥራት (Ethnic Cleansing) ምን ማለት ነው? www.thefreedictionary.com (The systematic elimination of an ethnic group or groups from a region or society, as by deportation, forced emigration or genocide) «አንድን ብሔር ወይም ቡድን በብልሀት በተዘየደ መንገድ ከአንድ ክልል ወይም ማህበረሰብ ውስጥ በማስገደድ ማስወጣት፣ማፍለስ ወይም የዘር ፍጅት ማድረስ ነው፡፡» የሚል ፍች ይሰጣል፡፡ በዚህ ፍች መሰረት በጉራፈርዳ የተፈፀመውን ድርጊት በስፍራው የዘር ማጥራት ዘመቻ በመንግስት አካላት እንደተካሔደ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በአከባቢው በተለያየ መንገድ ሰፍረው በግብርና ስራ ተሰማርተው ይኖሩ የነበሩት የአማራ ተወላጆች ከአቶ ሽፈራው ሽጉጤ ጽ/ቤት በወጣ ደብዳቤ «ሕገ-ወጥ ሰፋሪዎች ናችሁ» በሚል መፈናቀላቸው ብቻውን በስፍራው የዘር ማጥራት ዘመቻ ተካሂዷል ላያስብል ይችላል ቢባል እንኳን፤ እርምጃው ያለአሳማኝ ምክንያት መወሰዱ(የተወሰኑ ተፈናቃዮች በህጋዊ መንገድ መስፈራቸውን የሚረጋግጡ ሰነዶችን ተመልክቻለሁ)፣ ዜጎቹ በግዳጅ ሲፈናቀሉ ግድያን ጨምሮ የተለያዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች መፈፀማቸው እና ተፈናቃዮቹ ቢያንስ ንብረታቸውን ሸጠው የሚወጡበት ጊዜ አለማግኘታቸው በጉራፈርዳ የዘር ማጥራት መካሄዱን ያረጋግጣል ፡፡ አቶ መለስን ጨምሮ የመንግስት ባለስልጣናት የሰጧቸውን ማስተባበያዎችም ስህተትን ከማረም ይልቅ ጉዳዩን አድበስቡሶ የማለፍ አይነት ነበር ፡፡

የአቶ መለስን የስልጣን ዕድሜ ለማስረዘም ሲባል በተቀየሰው የከፋፍለህ ግዛ የዘውግ ፖለቲካ ኢትዮጵያ አደጋ ውስጥ መግባቷን ያስረዳኝ ወጣት ምሁር በግምት በሰላሳዎቹ አጋማሽ ላይ ይገኛል፣ በፌደራሊዝም የሁለተኛ ዲግሪውን አግኝቷል፤ ስሙን በጽሁፌ እንድጠቅስ ባይፈልግም ሙያዊ አስተያየቱን አልነፈገኝም፡፡ እንደ ምሁሩ ትንተና ኢህአዴግ ያሰመራቸው የክልል መስመሮች እንዲሁም ያዋቀረው ሀሳዊ ፌደራሊዝም(pseudo-federalism) በኢትዮጵያ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ የጎሳ ለ ጎሳ ግጭቶችን አበራክቷል፡፡ «ኢህአዴግ ስልጣኑን ለማስጠበቅ ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው እየቆረሰ የሚያካልልበት መንገድ አንዱ የተጉራባች ክልሎች ፀብ እየሆነ ነው» የፌደራሊዝም ምሁር የጉራፈርዳው ክስተት ኢህአዴግ የዘራው የዘውገኝነት አደገኛ ፍሬ መገለጫ እንደሆነ አስረድቶኛል፡፡ በክልሎች መካከል ያለውም ግንኙነት አንዳንዴ መስመር የለቀቀና በሁለት ሉአላዊ ሀገሮች መካከል የሚደረግ ግንኙነት እንደሚመስል ትዝብቱን አጋርቶኛል፡፡

ዶክተር ዳኛቸው አሰፋ በቅርቡ በአንድነት ፓርቲ ባቀረቡት የአደባባይ ንግግር በኢትዮጵያ የሰፈነው ዘውገኝነት የተለያዩ ክልሎች ተወላጆች ወደ ሌላ ክልል ሄደው መገኘታቸውን በራሱ ወንጀል ወደ ማድረግ እንዳዘገመ ተንትነው ነበር፡፡

የኢህአዴግ የዘውግ ፖለቲካ ቀመር አደረኛ ውጤት የሚያሳየው የጉራፈርዳው ክስተት ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁኑም በአጎራባች ክልሎችና ብሔሮች መሀከል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተበራከተው ግጭት ጭምር ነው፡፡ ለአብነት ያክልም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከተከሰቱት መሀከል፡- በጋሞ ጎፋ ለ2 ሰዎች ሞት ምክንያት የሆነው የብሔረሰብነት ጥያቄ፣ በኦሮሚያና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ አዋሳኝ አካባቢዎች ተከስቶ ከ22 በላይ ሰዎችን ህይወት የነጠቀ ግጭት እና በአፋር፣ በጉጂ ዞን እንዲሁም በሱማሌ ክልል የተለያዩ ጎሳዎች መሀከል የተደረጉት ደም አፋሳሽ ግጭቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህን አደጋዎች መንግስት አላስተዋላቸውም ለማለት አይቻልም፡፡ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ከማስተዋል በላይ እንዳሰጉት ስለሚሳብቁ፡፡ ጥያቄው የመንግስት እርምጃዎች ግብ ምን መሆን አለበት? የሚል ነው፡፡ በእኔ በኩል የአቶ መለስን የስልጣን ዘመን ከማስቀጠል ይልቅ የሀገሪቷንና የህዝቦቿን ዘላቂ ህልውና የሚያስጠብቅ እርምጃ መወሰድ አለበት የሚል እምነት አለኝ፡፡ በአሁኑ ወቅት ሩብ ጉዳይ ላይ የደረሰው የብሄር ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ የሃይማኖት ጉዳይም ከፍ ባለ ደረጃ በተቃውሞ ተወጥሯል፡፡

## የአብዮታዊ ዴሞክራት አባቶች መዘዝ

በሀገራችን ውጥረቱ እየጨመረ ስለመጣው ሃይማኖታዊ ተቃውሞ ሳስብ ባለፈው ሳምንት ለስራ ጉዳይ አንድ የመንግስት ባለስልጣን ጋር ደውዬ የተሰጠኝ ማስጠንቀቂያ ታወሰኝ፡፡ በግርድፉ ማስጠንቀቂያው እንዲህ የሚል ነበር «ማንም ስልጣን ላይ ሊሆን ይችላል... አንድን ሀይማኖት በሀገሪቱ ላይ የበላይ የማድረግ ጥረት ግን አደጋ አለው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አትዘግቡ በእሳት መጫወት የላችሁም፡፡» እኚህ ቱባ ባለስልጣን አልተሳሳቱም፤ እኔም መነሻ ሀሳባቸውን እጋራለሁ፤ አንድ ሀይማኖት ጠቅላይ እንዲሆን አልሻም፡፡ ኢህአዴግስ ጠቅላይ ሆኖ አይደል ነገር ያመጣው፡፡ የሰጡኝ መስጠንቀቂያ ግን አልተመቸኝም፡፡ ይልቁን መንግስት ለጉዳዩ የሰጠውን «የአይነኬነት» ትኩረት አሳበቀልኝ፡፡

በሃይማኖት ዙሪያ የተፈጠረው ውጥረት ጉዳዩ ባለመዘገቡ ብቻ እንደማይፈታ በመገንዘብ ስለውጥረቱ ምንጭ የሚያስረዱኝን ሰዎች ፍለጋ ተጋሁ፡፡ ያገኘኋቸው መረጃዎች ጭምቅ ውጤትም መንግስት ሃይማኖትን ለፖለቲካ መሳሪያነት

ወደ 17 ዞሯል

# 180 የሃዘንና የጭንቅ ቀን በወፍ በረር ሲቃኝ በተለይ “6” ቀናት

የመጨረሻ ክፍል

ብሩክ ከበደ

ባለፈው ሳምንት ክፍል አንድ ጽሁፌ በ1997 ዓ.ም የዲሞክራሲ ጤኔ የያዘው የድሃ አገር ህዝብ ንቅናቄ ለዲሞክራሲና የህግ የበላይነት ጠንቆች ለሆኑት ብቻ ሳይሆን ዴሞክራሲ ከኛ ወዲያ ላሳር ለሚሉ ሁሉ ጉድ ያሰኘውን እለተ ሚያዝያ 30 አንስቼ በቀጣይነት 180 ቀናት ውስጥ የደረሱትን አንኳር ክስተቶች ማስነበቤ ይታወሳል፡፡

በዚህ የእኛው ታህሪሪ (መስቀል ወይም አብዮት) አደባባይ ከዚች ታሪካዊ እለት 24 ሰዓት በፊት በኢህአዴጋዊ ድርጅታዊ አሰራር እና ሌላ ስውር ጥበብ ወደ አደባባዩ ጐርፈው የድርጅቱን ሊቀመንበር ቡራኬ ተቀብለው ከስድስት ቀን በኋላ የሚመሩትን ድርጅት እንደሚመርጡላቸው ተስፋ የሰነቁላቸው አባላቶቻቸው (በአሁኑ ጊዜ ምን ያህሉ በአባልነታቸው እንዳሉ ለመገመት አዳጋች ነው፡፡ ምክንያቱ ሁሉም የድርሻውን እየያዘ እብስ ማለቱ አሊያም ወህኒ መውረዱ ወይም መባረሩ የሚታወቅ ነውና፡፡) ጨምሮ የሬዲዮንና ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች ምሽቱን አጥብቀው የለፈፉለት፣ ለማውራት የተሸቀዳደሙለት ወሬ በማግስቱ እንኳን የከተማውን ነዋሪ ቀርቶ ከአዲስ አበባ ዙሪያ በፈረስና ባገኙት ተሽከርካሪ በመምጣት ባህረ ህዝብ አደባባይን የሞላው ህዝብ የሚመርጠው ሌላኛው መሆኑን በግልጽ አሳየበት፡፡

ከ24 ሰዓት በፊት ካኔቴራና ኮፍያ ታድሎት አደባባይ የዋለው ትናንተኛ “ትናንት ለካኔቴራ ዛሬ ለባንዲራ” ሲል ከእውነት ጐን በመሰለፍ ተዓምር ያሳየበት ዕለት ዛሬ ሰባት ዓመት ሞላው፡፡ ይህን ዕለትና ቀጣይ ወራቶች ያስተናገዱትን ዋና ዋና ክስተቶች ዛሬም ከሞላ ጐደል ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡ ለመግቢያ ያህል ይህን ያህል ከተጓዝን ሳምንት ካቆምንበት እንቀጥላለን፡፡

ታክሲው ሽንኮራ በረንዳን እንዳለፈ ያልታሰበ የሰው ጓርፍ ከወደላይ ቁልቁል ይንደረደራል፡፡ ቀደም ሲል በኢህአፓ ሆነ በሌላ ድርጅት አባልነታቸዉ ደርግን ይቃወማሉ የተባሉ ዜጎች ማሰቃያ ከነበረ ሰፊ የቀበሌ ግቢ የወጡ ወር ተረኛ የፌደራል ፖሊስ አባላት ከላይ የሚተመውን ህዝብ እያራወጡ በዱላ ይቀጠቅጡታል፡፡ ያልጠበቀው የገጠመው ህዝብም ነፍሱን ለማዳን አካባቢውን ያምሰዋል፡፡ ይህ ሲሆን ሰዓቱ ገና ከጠዋቱ 2፡30 ላይ ያመላክታል፡፡

ተሽከርካሪዎቹም ከአብነት ጀምሮ ተጠጋግተው በመቆማቸው አዙረው ለመመለስ ተቸግረዋል፡፡ በተለይ በትራንስፖርት ተሽከርካሪ ውስጥ የነበሩ አውርዱን በማለት ይጯጯኋሉ፡፡ ከማህከላቸው በመስኮት ለመዝለል የሞከሩ ነበሩባቸው፡፡ ሽንኮራ መጋዘን ካለው አራት አቅጣጫ ተጠቅጥቆ የቆመው ተሽከርካሪ ግን መላወሻ አላገኘም፡፡ ከአውቶብስ ተራ ቁል ቁል የሚጓርፈው በተለያየ ዕድሜና ሙያ ላይ የሚገኘው ህዝብም መጉረፉን አላቋመም፡፡ በአንፃሩም የፀጥታ ኃይል ከሚባለው አካል የሚወርድበት የዱላ የሰደፍና እርግጫ እየባሰ ሄደ፡፡ ይብስ ብሎም ተኩስ መሰማቱ ቀጠለ፡፡ ተኩሱም ረብሻውም እንደሰደድ እሳት በአንድ ግዜ በመላው አዲስ አበባ ተቀጣጠለ፡፡

በተለይ በወረዳ 3, 4, 5,6, 7,8, 12, 16 ህዝባዊዉ አመፅና ቁጣ በእጅጉ ገነፈለ፡፡ ከታዳጊ ሕፃናት እስከ አዛውንት፣ ከጤነኛ እስከ በሽተኛ ሳይለይም በዱላ ተደበደበ፡፡ በጥይት ተገደለ፡፡ እናቶች ትምህርት ቤት የገቡ ልጆቻቸውን ፍለጋ ነጠላቸውን ወገባቸው ላይ አስረው በከተማው ውስጥ ፈሰሱ፡፡ ከመሀከላቸውም አንዳንዶቹ የዱላ ሲሳይ ሆኑ፡፡ የከተማው ነዋሪ ሰላም ቢፈልግ፣ ዳር ቆሞ ተመልካች ለመሆን ቢያስብ፣ ከተለያዩ ጥቃቶች ለማምለጥ ባለመቻሉ ቁጣው ከሰኔ 1/1997 ዓ.ም ክስተት በላይ ዘለለ፡፡ የቅንጅቱ ሰሜን አዲስ አበባ ተመራጭ ባለቤትም በጥይት ተገደሉ፡፡ የመንግስት ኃይሎችን እንቅስቃሴ ለመግታትም ይመስላል በየመንደሩ ባሉ መንገዶች ድንጋዮች ተኮለኮሉ፣ ጐማዎች ተቀጣጠሉ፡፡ ውሾችም ከህዝቡ ጩኸትና ሩጫ ጋር በማበር በጩኸት መንደራቸውን አወኩት፡፡ በዚህም የተቆጡ ኃይሎች አማኑኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ሁለት ውሾችን ገደሉ፡፡

በዚህ ምሽትና በተከታታይ ባሉ ምሽቶችም ከላይ በተጠቀሱት ቀበሌዎችና በሌሎችም ቀበሌዎች ጨለማን ተገን ያደረጉ የፀጥታ ኃይሎች የጊቢና፣ የቤት በር በሰደፍና በርግጫ እየሰባበሩ ሰላማዊ ሕዝብን አፍሱ፡፡ በዚህ መጠነ ሰፊ አፈሳ አዛውንቶች፣ ሕፃናቶች፣ ሴቶች፣ ታማሚዎች ለከፍተኛ ሥነ ልቦና ተጋልጠዋል፡፡ በጊዜው ስለነበረው ጥቃት አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ግለሰብ ሲናገሩ “ሁለተኛ ከኢህአዴ ውጭ ማንንም አልመርጥም እንዲህ ከምታመስ ገላጋዩ እስከሚገላግለን መገዛት ነው ብሎ ሕዝቡ ራሱን ለአፋኞችና ለኢ-ዲሞክራቶች እንዲያመቻች ሆን ተብሎ የተደረገ ሥነ ልቦናዊና አካላዊ ጥቃት ነው ካሉ በኋላ ይህን መሰል ድርጊት መፈፀም ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ አለማወቅ ነው” ሲሉ አስተያየታቸውን ሰተዋል፡፡

በጥቅምት 23/1998 ዓ.ም ዕለት ረቡዕ ከሱማሌ ተራ ጫፍ እስከ ኮካኮላ ከሜክሲኮ ቁልቁል እስከ ቄራን ይዞ፣ ጊዮርጊስ፣ ፈረንሣይ ለጋሲዮን፣ ቤላ፣ ኡራኤል፣ መገናኛ፣ አውቶብስ ተራ፣ አማኑኤል፣ ኮልፌ፣ ሰሜን ማዘጋጃ ወዘተ የከተማዋ አካባቢዎች ሕዝባዊው ቁጣ የበለጠ ጋመ፡፡ አውቶብሶች ተሰባበሩ፡፡ የተቃጠሉም አሉ፡፡ በወረዳ 3 ከሚገኘው ፔፕሲ እስከ 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ መዳረሻ ባለው ረጅም መንገድ ላይ ሕዝቡ ባንዲራ ይዞ በመውጣት “አትነሣም ወይ ይሄ ባንዲራ ያንተ አይደለም ወይ? ሀገሬ ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም” የሚሉትን ሕብረ ዝማሬዎች በህብረት በማዜም እየተመመ ባለበት ሁኔታ በፀጥታ ኃይሎች በተከፈተበት ተኩስ ተበተነ፡፡

በዚሁ ዕለት ሌሊትም እንደ ጥቅምቱ 22 የጭንቅ ሌሊት ሁሉ ኢህአዴግ በየሰፈሩ ባደራጃቸው፣ በመለመላቸውና ስኳር ባላሳቸው እንዲሁም በጠባብ አመለካከትና በዘረኝነት ባሰባሰባቸወ ደጋፊዎቹ አማካኝነት በሚድረግ የጥላቻና የይሆናል ጥቆማ ሌሊቱን የከተማዋን ነዋሪዎች ቤትና በር እየሰበረ ዜጐችን በዱላ፣ በሰደፍ በእርግጫ ጥርሳቸውንና እጃቸውን እየሰበረ ሲያግዝ አደረ፡፡ አክራሪ የሚል ታፔላ የተለጠፈላቸዉ የቅንጅቱ አመራሮችም ወደ እስር ቤት ተወረወሩ፡፡ የዚህን ቀን ክስተት ከሌላው ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር በምሽትም ሆነ በቀን በየሰው ቤት የገቡት የፀጥታ ኃይሎች ሞባይል ሲያገኙ የሚወስዱበትን ምክንያት ሣይገልጹ ወይም ማስረጃ ሳይሰጡ እየያዙ መሄዳቸው ነው፡፡

የሙስሊሞች በዓል በተከበረበት በዕለተ ሐሙስም (ጥቅምት 24/ 1994 ዓ.ም) ሕዝቡ አንድነቱን ፍቅሩን፣ አብሮ መኖሩን ለመግለጽ ራሱን አረጋግቶ ዋለ፡፡ ግራ የገባው የፀጥታ ኃይልም እፎይ ብሎ ዋለ፡፡ በበዓሉ ሥነ ሥርዓት ላይም ሕዝብ ያልመረጠው የኢህአዴግ ሹመኛ ቢገኝ ምዕመኑ ተቃውሞውን እንደሚያሰማ መረጃ አስቀድሞ የደረሰው አካል አንዳችም እንግዳ ለመጥራት ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ በበዓሉ ላይም በጊዜዉ የአዲስ አበባ ከንቲባ አቶ አሊ አብዶ ፀሎታቸውን ሲያደርሱ በቴሌቪዥን ታዩ፡፡ ሕዝብ መርጦናል፣ ሕዝብ ወዶናል

ወደ 19 ዞሯል

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሠረተ፡፡ ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ ፍቀድ በአንድነት የሰሜን አሜሪካን የድጋፍ ሰጪ ማህበር ሥር ዘወትር ማክሰኞ በዋሽግተን ዲሲ ከተማ የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በዕወቅታዊ ጉዳዮች እና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነው፡፡

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል ይፈልጋል፡፡ የማንኛውም ሰው ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን ያለው ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲውን ለማቅረብ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነው፡፡

የዝግጅት ክፍሉ ስልክ:-
+25111 124 96 59
+251 922 11 17 62
+251 926 81 46 81
+251 923 11 93 74
+251 913 05 69 42

ፖ.ሳ.ቁ፡- 4222 አዲስ አበባ

ኢ.ሜይል፡-
fnotenetsanet@yahoo.com
udjparty@gmail.com
andinet@andinet.org

ፋክስ ቁጥር +251 111226288

# ርዕሰ አንቀፅ




ሳንሱር

ጋዜጣችን "ፍኖተ-ነፃነት" ብለናታል፡፡ "ፍኖት" ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር "የነፃነት መንገድ" ማለት ነው!!

# የመምህራን ጉስቁልናና የትምህርት ሥራ ውድቀት ቁርኝት



ገሞራው ካሳ

ባለፈዉ ሳምንት በነበረኝ ፅሁፍ ስለመምህራን ያነሰኳቸዉን ሀሳቦች ተከታይ ክፍል እነሆ፡-

ከተሞክሮ እንዳየነው አንድ መምህር የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ የሚያነሳው ከነቤተሰቡ በተጨባጭ ተርቦና ታርዞ ኑሮን ጨርሶ መቋቋም ሲሳነው ነው፡፡ እንዳሻው እጁን ሙሉ ብር ማፈስ የሚችል ሰው መቁጠር ይሰለቸው እንደሁ እንጂ ዛሬ የብር የመግዛት አቅም ምን ያክል እንደወደቀ ላይገባው ይችላል፡፡ የመመህሩ የወር ደሞዝ ለዚህ አይነቱ ሰው ለቀን ሻይ ቡና ወጪው አትበቃውም፡፡ መምህሩ ግን ላቡን አንጠፍጥፎ እንደ እርጉዝ እናት ቀን ቆጥሮ ከሚያገኛት ከንፁኅ የወር ደሞዙ በቀር የጎንዮሽ ገቢ የለውም፡፡ ይችኑ ምኑን ከምን አደርገዋለሁ ጭንቀቱ የሚጀምረው የደሞዝ ክፍያ ቀን ደርሶ ገና ብሩ እጁ ሳይገባ ነው፡፡ ይሄን ከምድር ከሰማይ የተራራቀ የአንድ ሀገር ይጨመርልኝ ጥያቄው እንደቅምጥሎቹ የቅንጦት ኑሮ አምሮት ወይም ገንዘብ በባንክ የማስቀመጥ ሱስ ይዞት ወይም ሰማይ ጠቀስ ህንፃ ሊገነባበት አይደለም፡፡ እየተከፈለው ያለው ወርሀዊ ደሞዝ በዝቅተኛ ደረጃም ሊአኖረው ስላልቻለ ነው፡፡ ስለተራበ፤ ስለታረዘ ነው፡፡ የመምህራን ጥያቄ የሀገር ጉዳይ ነው ሲባል የመምህሩ የመራብና የመታረዝ ችግር በርሱ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ስላልሆነ ነው፡፡

በትምህርት ሙያተኞች የሚታመንበት፤ አግባብ ያላቸው ጥናታዊ ጽሁፎች የሚያሳዩትና በተግባር ተደጋግሞ እንደተረጋገጠው ከመምህሩ ጎስቋላ አኗኗር የሚመነጩ አራት ወሳኝና ከትምርቱ ሥራ ጋር በቀጥታ የተቆራኙ ችግሮች ይከሰታሉ፡፡ እነዚህም፡-

መምህሩ ሙሉ የማስተማር እውቀቱንና ክህሎቱን በተገቢው አቀራረብ እለት በእለት እየተዘጋጀበት በሙሉ ኃይሉ እተግባር ላይ የማዋል ፍቃደኝነትና አቅም ያንሰዋል፤ የመልካም አርአያነት ስብእናና የሞራል ወኔ ስለሚጎለው ቀና ብሎ መሄድ የማይችል መምህር ቀና ብሎ መሄድ የሚችል ዜጋ ማፍራት አይችልም ፤ የማስተማር ሙያ ተገቢውን ትኩረትና ማህበራዊ ከበሬታ ይነፈገዋል፤ ከላይ ከ1-3 በተጠቀሱት ችግሮች ድምር ውጤት የትምህርት ጥራት ወድቆ ተማሪው ህብረተሰቡ የሚፈልገውን የባህሪ ለውጥ ማምጣት ያቅተዋል፡፡

ከሀገር ብሔራዊ ጥቅም አንጻር አደጋው ከሁሉም ከፍቶና ጎልቶ የሚታየው በተራ ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰው ችግር ሲደርስ ነው፡፡ ልብ በሉ፤ ተማሪው ህብረተሰቡ የሚፈልገውን የባህሪ ለውጥ ማምጣት አልቻለም ማለት በትምህርት ሙያተኞች ቋንቋ የትምህርት ሥራ ግብ ከሸፈ ማለት ነው፡፡ ግብ የሌለው ሥራ ትርፉ ከንቱ ድካም (ኪሣራ) ነው፡፡ ለነፍሳቸው ያደሩ ብፁአኖች የዚህን ዓለም ኑሮ ሲንቁና በጾም በጸሎት ሰውነታቸውን ሲአደክሙ መንግሥተ ሰማያት መግባትን ግባቸው አርገው ነው፡፡ በእነሱ እምነት ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት መንግሥተ ሰማያት የመውረስ ግብ ባይሰንቁ ኖሮ እስከዚህ ሥጋቸውን የሚበድሉበት ፍላጎቱም ጽናቱም ባልኖራቸው ነበር፡፡ ወላጅ ልጁን ት/ቤት ሲአስገባ እንደዚሁ በአዕምሮው ልጁ እንዲደርስበት የሚፈልገው ግብ አለው፡፡ ሀላፊነት የሚሰማው መንግሠትም እንደዚሁ፡፡ ልጆች ደብተር ተሸክመው ት/ቤት ሲሄዱ ሲመጡ ስናይ ወደዛ ግብ መዳረሻውን መሰላል ካልተያያዙት፤ በሌላ አባባል የባህሪ ለውጥ የሚገበዩበት የመማር ማስተማር ሂደት ከሌለ እግረ ተማሪ እንጂ የሚያገኙት ቁም ነገር የለም፡፡ በኑሮ ጣጣ ተውጦ ሰውነቱ በአካል እንጂ ቀልቡ አብሮት የሌለ መምህር የሚገባት ክፍል ህይወት የለውም፡፡ ያልታደሉ ህፃናት አጉሮ ማዋያ በድን በረት ነው የሚሆነው፡፡ ህፃናቱ እድሜአቸውን በየቀኑ እየተሰረቁ ነው ማለት ይሄው ነው፡፡ ወላጆችም ድካማቸውንና ተስፋቸውን ሁሉ ውሃ በላው ማለት ነው፡፡ መንግሥት የትምህርት ባጀት መድቦ ገንዘብ ያወጣል፤ ግን ለየሥራ ዘርፉ የሚሆነው የሠለጠነ የሰው ጉልበት ከውጭ ሀገር በከፍተኛ ክፍያ ካልቀጠረ በስተቀር ከሀገር ውስጥ ማፍራት አይችልም ማለት ነው፡፡ ሀገር ሀብቷን አፍሳለች ግን ብሀራዊ ስሜትና የሐገር ፍቅር ያለው ተቆርቋሪ የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት አልቻለችም፡፡ እሁሉም ቤት ኪሳራ ተንሰራፋ ማለት ይሄው ነው፡፡ ውትወታችን የእስካሁኑ ይብቃን፤ እዚህ ላይ እናስቁመውና የወደፊቱን መፍትሔ እንስጠው ነው እንጂ ብናምንም ባናምንም ኪሳራውማ ከጀመረን ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

የዛሬ 50 ዓመት ገደማ እኔና ሁለት ጓደኞቼ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ነበርን፡፡ ከከተማ ርቀው በገጠር ለሚኖሩ ለሰፈራችን ሰዎች በእጅ የተጻፈ ደብዳቤ ከዘመድ ወይ ከባለ ጉዳይ ሲመጣላቸው ከያለንበት ተፈልገን የምናነብላቸውና መልስ የምንጽፍላቸው ይታወሰኛል፡፡ አለወኑ ተዘበራርቀውና በክር ታስረው እሙዳይ ውስጥ ከተቀመጡ የተሻሹ ደብዳቤዎች መሀከል የግብር ካረኒ፤ የመሬት ውል ወይ ሙግት የመሳሰለውን መረጃ ሰነድ በመልክ በመልኩ እንለይላቸው ነበር፡፡ ዛሬ ብሔራዊ ፈተና በመጪው ሰኔ ወር ለመውሰድ ከሚዘጋጁት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ምን ያክሎቹ በየትኛውም ቋንቋ (በአፍ መፍቻቸውም ቢሆን) ደብዳቤ ያውም በእጅ የተጻፈ ማንበብ ቀርቶ ስማቸውን አስተካክለው መጻፍ እንደሚችሉ ደፍሮ መናገር የሚከብድ ይመስለኛል፡፡ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመጀመሪያ ዲግሪ የመመረቂያ ማሟያ የፕሮጀክት ጥናታዊ ስነጽሁፎች እንደዚሁም ከፍተኛ ጥናታዊ ድርሰቶች ተብለው በአንዳንድ ላይበራሪዎች የተቀመጡትን ሥራዬ ብሎ ላገላበጣቸው ምን ያክል የትምህርት ኪሣራ ውስጥ እንደገባን ይነግሩናል፡፡ እነዚህ የመጀመሪያ ዲግሪ ምርቆች የተወሰኑትንም ቢሆን አስተማሪዎቻቸውን ጨምሮ በ1ኛና በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ያለፉባቸው የትምህርት ጥራት ሁኔታ በከፍተኛ የትምህርት ተቋም ትምህርታቸው ላይ ዓይነተኛ ተጽእኖ ማሳደሩ ጥርጥር የለውም፡፡

የአንድን ሀገር የትምህርት አቅጣጫ የሚአሳይ ፖሊሲ ሲነደፍና በየደረጃው ሥርአተ ትምህርት ሲቀረጽ በማንኛም ሀገር ባለድርሻ ተዋንያን መሆን ያለባቸው በዋንኛነት መንግስት፤ ህብረተሰቡና የትምህርት ሙያተኞች ናቸው፡፡ ታላቅ የሀገር ብሔራዊ ጉዳይ ነው ማለቴ ነው፡፡ የሚአስፈልገው ገንዘብ መጠን፤ ጊዜና ጉልበት የዛኑ ያክል የላቀ ነው፡፡ በዚህ አያበቃም፡፡ የመማሪያ ክፍሎች ግንባታ፤ የመማሪያ መጻሕፍትን ጨምሮ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች፤ ስልጠና፤ ደሞዝ የመሳሰለው የሚጠይቀው የሀገር ሀብት ወጭ የት ዕየለሌ ነው፡፡ ይህ ሁሉ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት ሆኖ

ወደ 15 የዞሯል

# የሙስሊሞች ጉዳይ የኢትዮጵያ ጉዳይ፤ የህገመንግስት ጉዳይ የሁላችን ጉዳይ፤ የመለስ ዜናዊ ጉዳይ የራሳቸዉ ጉዳይ

ሰለሞን ስዩም

ዛሬም ሁለት ፍሬ ነገሮችን አስቀምጬ አልፋለሁ፤ የእድል ጉዳይ ሆኖ፣ በነደፍኩት ፕሮግራም መጓዝ አልቻልኩም፤ በዚህች ገፅ ለናንተ በማደርሳቸው ወጎቼም ደንገቴነት ቤተሰቤ ሆኗል፡፡ በየሳምንቱ ለዝግጅት ክፍሉ ከማስይዛቸው አርዕስቶቼ ተሳክቶላቸው በቀናቸው የሚወጡት እያነሱ መጥተዋል፡፡ “seldom do circumistances allow us” እንዳለችው ሩሲያዊት (ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጨረቃ የተጓዘችው ትልሽኮቫ)፡፡ እድሜ ለወቅቱ ሁኔታ ወጋችን ወይ የቅዳሜ አልያም የእሁድ ርዕስ ጉዳይ የወለዱት ሆኗል፡፡ ለማንኛውም አርብ ለት አንዋር መስጊድ የተገኘ አንድ የመገናኛ ብዙሃን ሰው ማክሰኞ ያስያዘውን ርዕስ ይዞ ለመውጣት አይገደድም፡፡

ሁለተኛው ፍሬ ነገሬ በመለስ ዜናዊ ብቃት መውረድ፣ መታመም አሊያም በሆነ ምክንያት ሁሉ አልሰጋም፡፡ ምክንያት ቢባል አንደኛ ኢህአዴግ ባለመሆኔ መለስ ዜናዊን እግር እስኪነቃ ቢዞር ተተኪ የማይገኙላቸው ጥሩ መሪ ሳይሆኑ ብልጣ ብልጥ አምባገነን መሪ አድርጌ ስለወሰድኳቸወ ነው፡፡ ሰዎች ሲጣሉ ገላጋይ ሆነው የሚገቡ ሰዎች አንደኛውን ወገን በመያዝ ሌላኛውን የሚያስጠቁበት አጋጣሚ አለ፡፡ የኢህአዴግ ሥርዓት እንደዚህ ሁላ ሌሎቹን እጅ እግር አስሮ መለስ ዜናዊን ብቻ በነጻነት ሜዳው ላይ የለቀቀ ነው፡፡ አሊያም በቦክስ ልምምድ ላይ እንዳለ ቦክሰኛ ራሱን የማይከላከል የላስቲክ ከረጢት የሚደበድቡ ይመስላሉ፡፡ መለስ ዜናዊ 21 ዓመታት ሙሉ ወይ እጅ እግራቸው ወይም አይናቸው የተሸፈነ “ተወዳዳሪ” አሊያም የመለማመጃውን ከረጢት እየደበደቡ መጓዛቸው ያልታየው የኢህአዴግ አባል በሰው ልጅ ልኬት የማይለኩ ከአምላክ ዝቅ ያሉ (super natural arena) አድርጎ ወስዷቸዋል፡፡ በዚህ የተታለሉት አቶ መለስ ዜናዊ “በከተማው ከኔ በቀር ፖለቲከኛ አልታየም” የሚል ንግግር ቀን በቀን እየጨመረ ይነበብላቸዋል፡፡

ለማንኛውም የመለስ ዜናዊ ብቃት እንጦሮጦስ ቢወረድ አሊያም አንድ ነገር ቢሆኑ ኢትዮጵያ በዚህ ዙሪያ እንደማትሸከረከር አምናለሁ፡፡ በመሆኑም ከዚህ ስጋት ውጭ መሆኔ በኢህአዴግ አባላት ላይ ያለኝ ብልጫ ነው፡፡

የዛሬው ዋና ጉዳዬ “የሙስሊሙ ጉዳይ የኢትዮጵያ ጉዳይ የመለስ ዜናዊ ጉዳይ የራሳቸው ጉዳይ መሆኑን አንድ ሁለት ለማለት ነው፡፡ ይህን ስል በቀጣይ በሁለት ዋና ዋና ጊጤዎች /focuses/ ላይ አተኩሬ የማነሳቸውን አንደኛ ሙስሊሞቹ ያነሱት ጥያቄ እውነተኛ ነገረ ሀሳብ (theme) ከታሪካችንና በወደፊቱ ሂደት የኢትዮጵያዊነት ተዋፅኦ አካል መሆኑንና እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግሥት ነገሩን የሚያጣምምበት የመንግሥቱን ዕድሜ (የመለስ ዜናዊ አገዛዝ) ከማርዘም ጋር የተያያዘ አላማ የሚያይልበት መሆኑን ለማመላከት ነው፡፡

የኢትዮጵያ የመንግሥትነት ታሪክ እስከ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ድረስ ከውስን መቆራረጦች ውጭ የአክሱም-እስራኤልን መዳቀል የቅቡል ማዕዘን በማድረግ የኖረ ነው፡፡ ክርስትና ኢትዮጵያን ከረገጠበት 4ኛ መ/ክ/ዘ/ አንስቶ ኢትዮጵያ የገነባችው ማህበረ ኢኮኖሚ እንዲሁም ፖለቲካዊ ባህሎች የክርስትና እምነትና ትውፊትን ማዕከል ያደረጉ ናቸው፡፡ በታሪክም እንዳየነው የመንግሥት ሀይማኖት ክርስትና ከመሆኑም የዘለለ ባብዛኛው ሀይማኖት የመንግሥት የበላይ የነበረበት (theocracy) አገዛዝ ነበር፡፡ በዚህ ላይ ሀይማኖታዊ ስነ-መለኮቱን ብቻ ነጥሎ ኢትዮጵያ የደረሰው እስልምና በተለይ የመንግስትነት ታሪክ በክርስትና ትውፊታዊ ባህል በተደላደለበት የሀገሪቱ ሰሜናዊ ክፍል መስረግ ከብዶት ነበር፡፡ በመሆኑም የበታችነቱን ይዞ መስፋፋት የሚችለው ቀስ በቀስ የነባሩ ባህል አካል በመሆን ራሱን ማመሳሰል ሲችል ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ እስልምና ከሀይማኖታዊ ስነ መለኮቱ ውጭ ማህበረ ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ትውፊቱን ኢትዮጵያ ዉስጥ ለመስራት ተገዷል፡፡ (ይህ ሁኔታ ግብፅን፣ ቱኒዚያን፣ ሰሜን ሱዳንንና መሰል የሰሜን አፍሪካ አረብ ሀገራትን ልዩ ያደረጋቸዋል፡፡)

ይህ የሀገራዊ ባህላዊ ትውፊት ሀይማኖታዊነት ሁኔታ የኢትዮጵያ መንግሥት የሙብት ጥያቄውን በሌላ አቅጣጫ እንዲያየው ለማድረግ አብዮታዊ ዴሞክራሲም ቀላል እገዛ አላደረገም፡፡ ማለትም ኢትዮጵያዊ መልክ የነበረው የሙስሊሙ ማህበረሰብ ትውፊታዊ ተፈጥሮ ባለፉት 20 ዓመታት በአለም ደረጃ በታየው የሃይማኖት ዳግም መነቃቃት (revivalism) ሲተካ ለቀጣዮቹ 40 ና 50 ዓመታት ለመግዛት የወሰነው ኢህአዴግ ክፉኛ ደነገጠ፡፡ ነገሩ ግን ወዲህ ነበር፤ በአንድ አካባቢ ባህላዊ ማንነት ላይ ተወስነው የነበሩ ኢስላማዊ መገለጫዎች ወቅቱ በፈጠረው ቴክኖሎጂ ከየትኛውም የአለም አቅጣጫ እየጎተተ በየሰው ቤት ማስገባት ጀመረ፡፡ ይህ ሀይማኖቱን አለም አቀፋዊ ዜግነት ቢያጎናፅፈውም በዚህ የተፈጠረው መነሳሳት ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ «የተሰበውን ሁሉ ለማወቅ የመፈለግ ተፈጥሮ» ጋር በቀጥታ ተላተመ፡፡

በሌላ አቅጣጫ ጉዳዩን እንደይረዳ ኢህአዴግን ያዘናጉ ሁለት ሦስት ታሪካዊ እውነቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት እስከ 16ኛ መ/ክ/ዘ) በደገኞቹ የክርስትያን መንግሥት (Christian highland kingdom) እና በምስራቆቹ ሱልጣኞች መካከል የነበረው ሀይማኖዊ ትምዕርት መራሽ ጦርነት በኦሮሞዎቹ መስፋፋት ወደ ብሄርተኝነት ተቀይሮ ነበር፡፡ ይህ ሀይማኖታዊ ማንነትን ከብሄርተኝነት ያነሰ ደረጃ `እንዲኖረው` አድርጓል፡፡

ሁለተኛው ምክንያት የታሪክ ተምኔት መሆኑ የሚነገርለት ነው፤ የአክሱም መንግሥት ገናናነት በንግድ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ቅሉ፣ በወቅቱ የተናቀ ሙያ በመሆኑ `የተናቁ` የተባሉት ሙስሊሞች በብቸኝነት የያዙት ሥራ ንግድ ነበር፡፡ በዚህ ስራ ፖለቲከኞች የሚሳተፉበት አልነበረም፡፡ በሌላ በኩል ከላይ እንዳነሳነዉ የእስልምና በኢትዮጵያ መስፋፋት ኃይል ያልቀላቀለ በመሆኑ የእምነቱ ሰባኪዎች ክርስትና ባልደረሰባቸው የጠረፍና ቆላማ አካባቢዎች ያተኮረ ነበር፡፡ በዚህ አካባቢ ኑሯቸውን የመሠረቱ ሙስሊሞች ከማዕከላዊው መንግሥት የክርስትያን መንግሥት ጋር የሚያቃርናቸውን እንደ አርብቶ አደርነት ዓይነት የኑሮ ዘዴ ላይ መሰማራት ተፈጥሯዊ ነበር፡፡ በዚህ አጋጣሚ ከክርስትያኖች ጋር ተቀላቅለው ከሚኖሩ ሙስሊሞች ይልቅ ለተለየ

ወደ 10 ዞሯል

*ኢስሃቅ እሸቱ ይባላሉ፡፡ የሶስት መጽሐፍት ተርጓሚ እና ጋዜጠኛ (ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ስለእስልምና የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች እና መልሶቻቸው፣ የኢስላማዊ አንድነት ጎዳና፣ የዓይን ምስክር (ከአማርኛ ወደ እንግሊዝኛ) ና የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት ኮፒ ኤዲተር ናቸዉ፡፡ ወቅታዊዉን የሙስልሞች እንቅስቃሴ አስመልክቶ ከባልደረባችን ሰለሞን ስዩም ጋር ያደረጉትን ቆይታ እነሆ፡-*

# በህዝበ ክርስቲያኑ ላይ ያንዣበበ ምንም አይነት አደጋ እንደሌለ በቅን ልቡና ይረዳልን

- **አሁን ያለውን ነገር እንተወው፤ ህዝበ ሙስሊሙ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያለው ውክልና ምን ይመስላል? ባህል ላይ፣ ማንነት ላይ፣ ፖለቲካ ላይ፣ እስልምናዊ ነገሮችን በማዋጣት ያለው ሁኔታ?**

በአጠቃላይ ጠንካራ ነገር አልነበረም፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የራሳችን ምልከታ አለን። ከዚህ አንፃር ታሪካችን ሆን ተብሎ የተዘለለ፣ የጠለሸና የታነቀ ነው። የኢስላማዊ ሱልጣኔቶች፣ የስልጣኔ አስተዋፅኦዎች በተለይ ከዚህ ቀደም በነበሩት መንግሥታት ዋጋ አጥተዋል።

- **ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?**

ሙስሊሞች ትምህርት እንዳያገኙ፣ በልሂቃንነት ጎልተው እንዳይወጡ በማድረግና በከፍተኛ ዘዴ የተደረገ ማግለል ነበር። እንኳን አገርህን ትምዕርታዊ (symbolic) በሆነ ነገር መወከል፣ ገፅታን መገንባት (image making) ይቅርና ኮፍያ ማድረግ፣ ሂጃብ (የሴቶች መከናነቢያ ሻሽ) ማድረግ ብርቅ ነበር። ከዚያ ውጭ አፄ ዓምደ ዮዮን፣ አፄ ዮሐንስ፣ አፄ ቴዎድሮስና ሌሎች ነገስታት ሙስሊሞች ላይ ያደረሱትን ጭቆናና ግፍ ማንሳት ይቻላል።

- **ለዚህ ለውጥ ህገ-መንግሥቱ ምን አበርክቶ ነበረው?**

ህዝብ ሙስሊሙ አመለካከቱን በመጽሐፍ መልክ በመጻፍ፣ ሚዲያዎች ሽፋን በመስጠት ቀስ በቀስ ሀገሪቱ ውስጥ ድርሻ ወደ መውሰድ ሄደ። ድሮ ኮፍያ ማድረግ ይፈራ የነበረው አሁን ሀይማኖቱ የሚጠይቀውን ነገር ግን ከነበረው አገዛዝ የተነሳ የተዋቸውን ትርፍ የሚመስሉ ግን ያልሆኑ ሀይማኖታዊ ተግባራት ሲፈፅም አዲስ እያቆጠቆጠ እንዳለ የሀይማኖት አክራሪነት ታየ።

- **እዚህ ላይ መንግሥት ይህንን ቀድሞ ያለመገመት ችግር ነበረበት? ማለቴ ሀይማኖታዊ ግዴታ ከሆነ በአክራሪነት መፈረጁን ምን አመጣው ብዬ ነው?**

በትክክል ገልፀኸዋል፤ ሌሎችም የፖለቲካ ተንታኞች ይሄንኑ ይላሉ፤ ህዝብ ሙስሊሙ ወደ ሀገሪቱ ታሪክ ተሳታፊነት ሲመጣ ያንን የሚሸከም ከባቢን መንግሥት መፍጠር አልቻለም። መንግሥት ባለበት ቆሟል፤ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ግን እየተለወጠ ሄደ። ያንን ለውጥ ማመቻቸት አልቻለም ይላሉ። በቤተሰቦችህ ቤት ሶላት ትሰግዳለህ፤ ዩኒቨርሲቲ ገብተህም ትሰግዳለህ፤ አሁን ግን አትሰግድም ከተባልክ ከሀይማኖትህ የሆነውን ክፍል እያነሱብህ ነው ማለት ነው።

- **ይህ ወሃቢዝም የሚባለው አይደለም? እስልምናዊ ስነ መለኮቱን የአለማዊ መዋቅር አካል ማድረግ፤ ለምሳሌ በ12 ወይም 7 ሰዓት ከክፍል ወጥተህ ልስገድ ማለት አለማዊ ተቋሙን በሀይማኖት መበረዝ ነው የሚል መከራከሪያም አለ።**

በስህተት መረዳት ያልኩህ ይሄ ነው፤ ቀድሞ ይህንን ያላደረግናቸው መፃህፍቶቻችን ውስጥ ስላልነበሩ አይደለም፤ ያንን የሚፈቅድልን ከባቢ ስላልነበረ ነው፤ ይህ በተለይ መንግሥታቱን ይመለከታል፤ አሁን ከብዙ አመታት መራር ትግል በኋላ ነፃነትና ህገ-መንግሥታዊ የዕኩልነት መብት የሚል ነገር መጣ፤

- **እዚህ ላይ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦችም ቀድሞ እያላቸው ነገር ግን በመንግሥታት ጭቆና ያላንፀባረቁትን ማንነት ማውጣት ጀምረዋል። አጨፋፈሩን ክብር በዓሉን ካየን እጅግ ከፍተኛ መሻሻያ አለ፤ በሀይማኖቱም እንዲሁ ነው፤ በከፍተኛ ሁኔታ የሚገለፀው የባህል ማንነት ካልተከለከለ በእኩል ጊዜ ነፃነት ያገኘው ሀይማኖት በአክራሪነትና በትርፍነት የታየው ለምንድነው?**

ሁለቱም የየራሳቸው ባህሪይ አላቸው፤ ድሮ ሊያደርግ የሚፈራቸውን አሁን ህዝብ ሙስሊሙ ማድረግ ጀመረ። ይህ ነው ያለው።



- **ስለዚህ አሁን እየተከለከለና እየተፈራ የመጣው የሀይማኖት ጉዳይ በመሆኑ እንጂ ባህል ላይ ቢደረግ ወይም በአፄው ጊዜ የማታደርጉትን አታድርጉ አልተባሉም ማለት ይቻላል?**

ምናልባት ሀይማኖቱን ከፈሩት አላውቅም፤ ይህ እኮ ለምሳሌ ተማሪ ነኝ እንበል፤ እናቴ ቤት እያለሁ እበላ ነበር፤ አሁን ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሲሆንም የምተወው ነገር አይደለም፣ ድሮ እለብስ ነበር፣ አሁንም መልበስ አለብኝ፣ ድሮ የማደርጋቸውን ነገሮች እንደሰው ማድረግ ይፈቀድልኛል፤ ድሮ እናቴ ቤት ሆኜ እሰግድ ነበር፤ አሁን ዩኒቨርሲቲ ሆነህ አትሰግድም ከተባልኩ ሀይማኖታዊ ማንነትህን እንደጃኬት በር ላይ አውልቀኸው ግባ እየተባልኩ ነው ማለት ነው። ይህ እንደ የሀይማኖቱ ይለያያል፤ ክርስትና በቀን 5ቴ እንድትሰግድ ላያዝ ይችላል፤ በሌላ መልኩ ግን መስቀልህን (ማተብህን) በጥስና ግባ ቢባል የሚሰማውን ያክል አንድ ሙስሊም ደግሞ የሚበጥሰው መስቀል/ማተብ ባይኖረውም ሶላት ግን አለው፤ ሶላቱን ካቆመ ከእስልምናው አጉድሏል ማለት ነው። እንደ ሙስሊም ሆኜ ማንነቴ ሳይጎድል መማር ከተከለከልኩ ምኑ ጋር ነው የተከሰከሰው አጥንት የፈሰሰው ደም አስፈላጊነት። እንደ ብሔር የተሰጠህ መብት እንደ ሀይማኖታዊ ቡድን ከተነፈገህ መብቱን የሰጠው አካል ቆጭቶታል ማለት ነው።

- **ወሃቢዝም አይደለም እያልከኝ ነው?**

አልኩህ እኮ! ድሮ ማድረግ የማንችለው መፅሐፍታችን ውስጥ ስለሌለ ሳይሆን በነበረው ሁኔታ መተግበር ባለመቻላችን ነው። ሶላትን ወሃቢዝም አልፈጠረውም፤ ድሮ ተደብቀን እንሰግድ ነበር፤ ያምም በወሃቢዝም የተፈጠረ አይደለም፤ አሁን ግን ሞተን፣ መስዋእትነት ከፍለን ነጻነት አወጅንላችሁ ስለተባልን ይፋ አደረግነው፤ ከዚያ መጡና ፂምህን ካልተቆረጥክ ታከራለህ መባል ተጀመረ። ሙስሊሙ ጋር ያለው አክራሪነት ሳይሆን ነፃነትን መግለፅ/መጠቀም መጀመር ነው። ከመፅሐፉ ውጭ ያለ ነገር የለም። ከዚያ ውጭ እንደ ግለሰብ አንዳንዱ ሀይማኖቱን ጠበቅ ሌላው ለቀቅ ሊያደርግ ይችላል። ኦርቶዶክሱን አንተ አጠበቅክ፣ አንተ ደግሞ አላላህ እንደማይሉት ሁሉ እኔም ወይ ወሃቢ አሊያም ሌላ ታፔላ በመስጠት ሊቆጣጠሩኝ አይችሉም። አንዲት ሴት ሚኒስከርት አድርጋ ጭኗን እያሳየች መማር እንደማትከለከል ሁሉ ሌላኛዋ ፀጉሯን ስለሸፈነች አትማሪም መባሏ ትርጉም አይሰጥም።

- **ኸዋሪጂያ ምንድነው?**

ቃሉ “መውጣት” እንደማለት ነው፤ በቀደመው የእስላም ታሪክ ውስጥ መሪዎቻቸው ላይ አምፀው የወጡ ናቸው። ቡድኑ በትናንሽ ነገሮች ሰዎች ከእስልምና እንደወጡ የሚቆጥር ነው፤ ጥቃቅን እንኳ ወንጀል ብትሰራ ከእስልምና ወጥተሃል ብሎ የሚበይንና አክራሪነት የተጠናወተው አስተሳሰብ ነበር።

- **በኢትዮጵያ አለ የለም?**

ነበር ቢባል ይሻላል፤ በአንድ ወቅት ጎንደር አካባቢ በተወሰነ መልኩ ወደ አዲስ አበባም ተጀምሮ ነበር፤ በአንድ እጅህ ቆጥረህ የምትጨርሳቸው ግለሰቦች ናቸው፤ በኢትዮጵያ ቀርቶ ሙስሊም በሆነው የአረቡ አለም እንኳ ተስማምተው መኖር የማይችሉ ናቸው። ታዋቂው አስተማሪ ኡስታዝ ሀሰን ታጁ (ተክፊር) ተክፊር የሚል መፃፍ ከፃፈ በኋላ ቡድኑ ሙሉ በሙሉ በመክሰሙ አጀንዳ ሆኖ ሊነሳ አይችልም። የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ራሱ እንዲህ አይነት አክራሪነትን የሚሸከም አይደለም።

- **አሁን ያለው የሙስሊሙ እንቅስቃሴ ዋነኛ ምክንያት ምንድነው ተብሎ ይገመታል?**

ግምት ሳይሆን እንቅጩን ልንገርህ፤ በ1960ዎቹ የንጉሱን መውደቅ ተከትሎ ህዝብ ሙስሊሙ መጅሊሱን በከፍተኛ መስዋዕትነት መሠረተ። መሪዎቹ በህዝብ ዘንድ የሚከበሩና የሚወደዱ ኢማሞች ነበሩ።

- **ማንን ማንሳት እንችላለን?**

ሃጂ መሐመድ ሳኒ ሃቢብ የሚባሉ የአንዋር መስጂድ አሰጋጅ ነበሩ የመሠረቱት፤ በሊቀ-መንበርነትም እንዲመሩ ተመርጠው ከፍተኛ ተወዳጅነት አትርፈዋል፤ አንድነትንም አጠናክረዋል። የደርግ መንግሥት የነበረውን ፀረ ሁሉም ሃይማኖት ባህሪ እንኳ የቻሉትን ያክል ተከላክለዋል።

- **ታዲያ ተወካይነት የለውም የሚባለው መጅሊስ መቼ ነው ወደ አመራርነት የመጣው?**

ከ1987 ግጭት በኋላ ነበር። በዚህ ግርግር ወቅት ህዝብ ሙስሊሙ ያልወከላቸው ሰዎች በጓሮ በር መግባት ጀመሩ። በነዚህ ውክልና ያልነበረው መጅሊስ በ1992 ዓ.ም ምርጫ ማድረግ ስለነበረበት የይስሙላ ምርጫ ተካሄደ። ከዚህ በኋላ ሙሉ በሙሉ እምነት የማይጣልባቸው ሰዎች መድረኩን ተቆጣጠሩት።

- **ከዚያ በፊት 1987 በነበረው ግጭት ጠ/ሚ/ሩ**

ወደ 9 ዞሯል


BILL PAGE TOYOTA & SCION
እውነትም ለሀገር ልጅ አለኝታ!!
ቢል ፔጅ ቶዮታ
ቢል ፔጅ ቶዮታ እና ሳዮን
2923 Annandale Rd.,
Falls Church, VA 22042
703.532.8800
www.billpagetoyota.com
yeshanew@billpagetoyota.com
TOYOTA IS THE MOST FUEL EFFICIENT FULL-LINE CAR COMPANY ON THE ROAD TODAY
TOYOTA


EDNA
Call 202-588-0337
Unisex Salon
- Hair Cut & Styles
- Body Message
- Manicure & Pedicure
2116 18th St. NW Washington, DC

ከገፅ 7 የዞረ

➢ እንደአሁኑ ተጠይቀው "ይህ የህዝብ ሙስሊሙ ጉዳይ በመሆኑ መንግሥት ጣልቃ አይገባም፤ ምርጫም በራሱ መርሃ ግብር ያደርጋል" ብለው ነበር ይባላል። ተመልሶ ነበር?

1980ዎቹ በነበረው ሁኔታ በተለመደው መልኩ "ተቋሙ የናንተው ነው፤ ምርጫም ማካሄድ ይቻላል" ቢሉም በተለይ በ1992ቱ ምርጫ ክፍለ ሀገር አካባቢ ውክልና የሌላቸው ሰዎች እየገቡ ውክልና የነበራቸው ሰዎች ተገልለዋል። ምርጫው ከፍተኛ ችግሮች የነበሩበት ነበር። አሁን ያሉት አመራሮች ለህዝበ ሙስሊሙ መብት የቆሙ አልነበሩም፤ ችግሮችን እያዩ አልፈዋል፤ በልማት ስራ ተሳታፊ አልነበሩም። በሙስና የተዘፈቁ ነበሩ። በየአመቱ ከሚደረገው የሃጅና ኡምራ ጉዞ ጋር በተገናኘ በርካታ ሚሊዮን ብር ሲመዘብሩ ነበር። አሁን ባለው ፖለቲካዊ ቋንቋ ኪራይ ሰብሳቢዎች የተጠራቀሙበት ነበር።

➢ ምርጫ በአግባቡ ለምን አልተካሄደም?

በጀት የለም የሚል አሊያም ሌላ ምክንያት ይቀርባል። በመጨረሻ ግን ውክልናው በሹመት ሆነ። ምርጫ የሚባል ቀረ።

➢ የመጨረሻ ምርጫ መካሄድ የነበረበት መቼ ነው?

መተዳደሪያ ደንቡ ምርጫ በየ 5 ዓመቱ መካሄድ እንዳለበት ይደነግጋል። 1992 የይስሙላ ምርጫ ከተካሄደ በኋላ በ1997 መካሄድ ነበረበት። ነገር ግን መጅሊሶቹ መንግሥት በራሱ ግርግር ላይ በመሆኑ ምርጫ አያስፈልግም የሚል ሰበብ ሰጡ። 2002 ላይም መደረግ ነበረበት፤ እዚያም እንዲሁ አለፈ።

➢ ምክንያቱ ምን ነበር?

በጀት ነው። ሌላው የፖለቲካ አለመረጋጋት አለ የሚል ነው። ብቻ ማን እንደመረጠው በማይታወቅ ጠቅላይ ጉባኤ በሚባል የ40 ሰዎች አካካቢ ስብስብ የፈለጉትን ይሾማሉ፣ የፈለጉትን ይሽራሉ።

➢ በትክክል 40 ናቸው?

ከ40 ጥቂት ጨመር ይላሉ። ህዝቡ አያውቃቸውም። ከየክልሉ የተወከሉ ናቸው ይባላል። በነቂስ ወጥቶ ህዝቡ የመረጠበት ጊዜ ግን አልነበረም። በሙጅሊሱ ታሪክ ከ1992 በኋላ ምርጫ የሚባል ነገር የለም። የ1992ቱም ቢሆን ተቀባይነት የለውም። ከ1987 በኋላ ተቋሙ ባዶ ሜዳ ላይ ሲንገዋለል ነው የቆየው። 17 ዓመታት ሙሉ ህዝብ ሙስሊሙ የሚያምነው መሪ የለውም። ይህ ቅሬታ ቀስቅሷል።

➢ ወዲያው ለምን አልተቃወሙትም?

ከሚዲያው ደካማነትና በተለያዩ ምክንያቶች ህዝበ ሙስሊሙ ዘንድ ደርሶ አልታወቀም። ሰው ቢያውቅም ተስፋ ቆርጦ የመተው አይነት ነገር መጣ። ከ1992 ጀምሮ መጅሊሱ እንዳለ አካል አይቆጠርም። ሴቶች ሂጃብ ይከለከላሉ፤ ወንዶች ሶላት ይከለከላሉ፤ አንድም ቀን ከሚመለከተው አካል ጋር ተወያይቶ (ተከራክሮ) ተወካይነቱን አላንፀባረቀም። መብትህ ሲጣስ መከታ አይሆንህም። የልማት ስራዎች ላይ በጀት አይመድብም፤ በታሪኩ በራሱ ተነሳሽነትና በጀት አንድም መስጊድ አሰርቶ አያውቅም፤ አሰራሩ በሙስና የተጨማለቀ ነው። ከህዝበ ሙስሊሙ ልብ ከወጣ ቆየ።

➢ የእንቅስቃሴው የመጨረሻ ምክንያት (immediate cause) ምንድነው?

ሐምሌ 2003 ዓ.ም መጅሊሱ 1300 የሚሆኑ ሰራተኞቹን በሐረር ሀሮማያ ካምፓስ አህባሽ የሚባል ትምህርታዊ ስልጠና በመስጠት ሁሉንም መስጂዶችንም፣ ኢማሞችንም ማጥመቅ ጀመረ። 800 ሰዎች ተገኝተው ነበር።

➢ ስልጠናው የአህባሽ ስለመሆኑ ማስረጃችሁ ምንድነው?

በጉባኤው የተቀዱ የኦዲዮም የቪዲዮም ቀረፃዎች ወጥተዋል። ሚዲያዎችም በዚህ ጉዳይ ላይ ሰሩ። ህዝቡም መጅሊሱ ምን አመጣ በሚል ተደናገጠ።

➢ አህባሽ የተባለውና በተለመደው ሙስሊም ዘንድ የሚመለከው እስልምና ተቃርኖ ምንድነው?

በአለም ዙሪያ ያሉ የእስልምና ተቋማትና የተለያዩ የአስተሳሰብ መስመር (school of thought) መምህራን በሙሉ በአንድ ድምፅ የሚያወግዙትና ከእስልምና ያፈነገጠ መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

➢ ይህ በመሰበኩ መንግሥት ምን ይጠቀማል?

እኔ እንደውም የሚጎዳ ነው የሚመስለኝ፤ ምን አስልቶ እንደገባበት ትክክለኛው መልስ እሱ ጋር ነው ያለው። የብዙዎች ግምት ግን የህዝብ ሙስሊሙን ክፍፍል ይፈልገዋል የሚል ነው፤ "divide and rule" የሚሉት አይነት ነው። ጉዳቱ ግን ህዝበ ሙስሊሙ በመንግሥት በጣም ቅር መሰኘቱ ነው፤ በመሆኑም እኔ እስካሁን ጉዳት እንጂ ጥቅም አላየሁም። የበለጠ ግን ራሱ መንግሥት ይጠየቅ።

➢ የአህባሽ ሀሳብ ምንጩ የት ነው?

በሀይማኖት ጦርነት ከምትታመሰው ሊባኖስ ነው፤ ጥሩ ስም የላትም፤ እንኳን ለኢትዮጵያ ለማንም አትጠቀስም። እስልምናን ያለመጥቀም አንድ ነገር ነው፤ እስልምናን ለማጥፋት መነሳት ግን አንድ የሙስሊም ተቋም ነኝ ከሚል አካል የሚጠበቅ አይደለም። ቅሬታው ሲብላላ ቆይቶ ነው እዚህ የደረሰው።

➢ "ህገ መንግሥታዊ ያልሆነ አካሄድ የመረጠው ኃይል" ይላል መንግሥት፤ ለመሆኑ ይህ ኃይል ማን ነው?

አሁን ያለውን ኮሚቴ ከሆነ ሙሉ በሙሉ ህገ መንግሥታዊ ነው፤ ተቃውሞውን ያነሳው እጅግ ሰላማዊ በሆነ አካሄድ ነው፤ ከ500 ሺህ እስከ አንድ ሚሊዮን ሰው አወሊያ ላይ ተሰብስቦ አንድ ጠጠር ሳይወረውር ነበር የሚመለሰው። መንግስት ሰላማዊ ተቃውሞን በፊርማ ማሰባሰብ፣ በሰላማዊ ተቃውሞ መግለፅ እንደሚቻል ደንግጓል። ተቃውሞው በመጀመሪያ ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ቀጥሎ ለጠ/ሚ/ሩ ጽ/ቤት ከዚያም ለፌዴሬሽን ም/ቤት እና ወደ ሌሎችም የህጋዊ ማዕቀፍ ሰንሰለቶች እየሔደ ነው። ከዛ ውጭ ህዝቡ ጁሙአ ሶላት ዱሮም ይሰግዳል፣ አሁንም ወደፊትም ይሰግዳል፤ በዚሁ አጋጣሚ ተገቢ መልስ እስኪያገኝ ተቃውሞውን በሰላማዊ ሰልፍ አሰምቶ ይበተናል። ህገ መንግሥቱ ላይ ከጁመአ ሶላት በኋላ "አላሁ አክበር" ማለት ክልክል ነው የሚል ከሌለው ምኑ ነው ፀረ ህገ መንግሥት? አንድም ኮሽ ያለ ነገር የለም፤ ሰላማዊ ተቃውሞ ነው።

➢ መንግሥት ፖሊስ ተደብድቦብኛል እያለ ነው ምክትል ሳጂን ብርሃኑ ብዙነህ የተባለ።

የለም፤ እኔ እስከማውቀው አወሊያም አንዋርም የተደበደበ ፖሊስ የለም።

➢ ምክትል ሳጂን ብርሃኑ አንዋር መስጊድ ጋ ተደብድቧል የሚል መግለጫ ተሰጥቷል እኮ?

ውሸት ነው፤ አንዋር መስኮት ተሰብሯል ተብሏል፤ ለምን አላሳዩንም፤ ሁሌም እዚያ እየሰገድን? የተሰበረ የለም፤ ቪዲዮ ደግሞ አለው አንድ ያልተቀረፀ የለም፤

➢ መንግሥት እኮ ተገቢውን ምላሽ ቢያገኙም አሁንም ፖለቲካዊ አጀንዳ እያራመዱ ነው ይላል?

ይህ ምክንያታዊ አይደለም ወደ ሚሊዮን የሚደርስ ህዝብ በአንድ ሜዳ ላይ ተሰብስቦ ፖለቲካ ጥያቄ ቢኖረው ምን ነበር የሚያደርገው? የአወሊያን 59 ሺህ ካሬ ሜትር ግቢ ሞልቶ ከዊንጌት አደባባይ እስከ ጄኔራል ዊንጌት ት/ቤት የሞሉ ሰዎች ደንጋይ አላነሱም። የአንዋሩን አላየኸውም እንዴ? ህዝቡ የያዘው ፖለቲካዊ ሳይሆን ግልፅ ትናንሽና ተራ የሙብት ጥያቄዎች ናቸው።

➢ ለከፍተኛ ጥፋት የተዘጋጁ ኃይሎች አሉ ይላል መንግሥት፤ ምን ማለት ነው? ለምሳሌ ክርስቲያኑ ላይ የበላይነት ለመያዝ የተደረገ ዝግጅት አለ? በመስበክ በመሣሪያ በመዘጋጀት?

በፍፁም! በፍፁም!

➢ ግን ምን ማለት ነው? እኔ አይገባኝም። ቦምብ ማፈንዳት መንግሥትን ማወክ የመሳሰሉት ይመስለኛል?

ይህ እኮ የኛ ባህሪ አይደለም፤ መግለጫ መረጃ አይሆንም፤ ህዝበ ሙስሊሙ በዚህ አይታማም። ለማንም ኢትዮጵያዊ አደጋ ያልሆነ ጥያቄ ነው? የተጠየቀው እኮ ጥሩ መጅሊስ ይኖረን ዘንድ ሁኔታው ይመቻችልን ነው፤ ይህ መንግስትን ጭምር ይጠቅማል። ወቀሳ ሳይሆን ሙገሳ ያስገኝለታል።

➢ ባደረጋችሁት እንቅስቃሴ በመንግሥት በኩል የተወሰዱ እርምጃዎች ምን ይመስላሉ? ማሰር፣ መደብደብ አሊያም የተገደለ ሰው ካለ?

ማሰር በሽ ነው፤ አዲስ አበባ ላይ ትንሽ ቢቀንስም ክፍለ ሀገር የለት ተለት ተግባር ነው፤ እኔም ከታሰሩት ውስጥ ነበርኩ።

➢ አንተ በምን ተሳትፈህ ነው የታሰርከው?

ፓምፍሌት መበተንና አመፅ ማነሳሳት በሚል ነው፤ የተገኘ ነገር ባይኖርም እንዲሁ አጉላልተው ለቀቁኝ። 50 ሰዎች ሙጅሊሱን የሚቃወም ቲሸርት ለበሳችሁ ተብለው ታስረው ነበር። መጅሊሱን መቃወም መብት ሆኖ ሳለ የተቃወሙት ላይ ወከባ መፈጸሙ ግልጽ ጣልቃ ገብነት ነው። መጅሊሱን የመቃወም መብት የለኝም እንዴ? አለኝ እኮ! ሶስት ሴቶች ፓምፍሌት ሲያነቡ ተገኝተው ታስረዋል፤ 18 ዓመት ባይሞላቸውም ሁለቱ ተፈተው ይኸው አሁን ድረስ አንዷ እስር ቤት ናት።

➢ የእንቅስቃሴው አላማ እስላማዊ መንግሥት መመሥረት ነው?

በፍጹም አይደለም! ሀይማኖታችንን ለመከተል እና ለመተግበር ህገ መንግሥቱ የሰጠን መብት በቂና ከበቂ በላይ ነው። እኛ ችግራችን ሕገመንግስታዊ መብታችን መነፈጉ እንጂ ሕጉ አይደለም። ሁለተኛ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የሸሪአ መንግስት የሚታሰብ አይደለም። ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሻሽ መልበስ፣ ሶላት መስገድ ብርቅ ሆኖብን የሸሪአ መንግሥት ማሰብ እንዴት ምክንያታዊ ይሆናል? ደግሞ እኮ ቢያንስ 40 ሚሊዮን ክርስቲያኖች ያሉባት ሀገር ናት ኢትዮጵያ። እንዴት ሆኖ ይህን አይነት ጥያቄ ይነሳል?

➢ ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ሙስሊም እንኳ ብትሆን እስላማዊ መንግሥት ያለመመስረት ከሀይማኖቱ ጋር የሚጋጭ ነገር አለው?

የህዝቡ ፍላጎት ይመስለኛል፤ ሀይማኖታዊ ትንታኔ ለመስጠት ይከብደኛል፤ የእኛ ጥያቄ አለማዊነቱ (secularism) ትክክለኛ ይሁን ነው።

➢ እንቅስቃሴው ሀይማኖታዊ ጥያቄ ብቻ ነው ካልክ ክርስትያኖቹ ላይ የሚፈጠርን የስነ ልቡና ጫና ለመቅረፍ የተደረገ አጀንዳውን ግልጽ የማድረግ ስራ ተሰርቷል?

በግል፣ በጋዜጣ፣ በመጽሄት እኔም በግሌ በጋዜጣ ሀሳቤን ገልጫለሁ፤ ደግሞ ብዥታው ይህን ያክል ነው አልልም፤

➢ ሰሞኑን መንግሥት ከሚሰጠው መግለጫ አንፃር ጫና ያለው ይመስላል፤ የየትኛውም ሀይማኖት አባል የሆናችሁ "እነዚህን አክራሪዎች ተዋጓቸው" ሲባል ያልታሰበ ነገር ደረሰ አያስብልም?

ብዙ ነው አልልም፣ ጥያቄው ራሱ ግልፅ ያደርጋል፤ ውጥረትም ካለ ክርስትያን ወንድሞቻችን ነገሩን ለማወቅ ዩቲዩብ ከፍተው በቪዲዮ የተቀረጸውን ማየትና የበለጠ መረዳት ይችላሉ።

➢ ቁጥራችሁ ስንት ነው? በቁጥር አንሰናል የሚለው የእንቅስቃሴው አንድ አጀንዳ ነው?

አይደለም፤ እንቅስቃሴው ሶስት አጀንዳዎች አሉት፡- የመጀመሪያው መጅሊሱ ባልተመረጡ ሰዎች ተሞልቷል የሚል ነው፤ ስለዚህ ምርጫ ፍቀዱ ነው፤ ሁለተኛው አህባሽ የሚባል አንጃ በግድ ከሊባኖስ አምጥተው እየጫኑብን ነው የሚል ነው። መስጊዶቻችንንና መድረሳዎቻችንን እየቀሙን ነው፤ ሦስተኛው አወሊያ የሕዝብ ሙስሊሙ ብቸኛው ጠንካራ ተቋም ሆኖ እንደ መቆየቱ ከመጅሊሱ ወጥቶ ለህዝብ አስተዳደር ይሰጥ ነው። ስለዚህ የህዝብ ቁጥር ችግር ምናልባት ህዝብ ሙስሊሙ በግል ቆጠራው በትክክል አልቆጠረኝም ሊል ይችላል። በዚህ እኮ ፓርላማ ውስጥም የአማራ ህዝብ ቁጥር አንሷል ተብሎ ክርክር ነበር።

➢ ት/ት እና ሀይማኖት ተለያይተዋል ይባላል፤ የአለማዊ ት/ት አለ፤ የመንፈሳዊ ት/ት አለ፤ ታዲያ አወሊያ የተነሳው ምንድነው?

ድሮ የውጭ ኤጀንሲ ያላሟላው ነገር ስላለ ፍቃዱን ነጠኩት፤ በሚል ህዝብ ላልመረጣቸው መጅሊስ ተሰጠ።

➢ ለፈቃድ ተብሎ ነው ወደ መጅሊስ የዞረው?

ሁለቱ የመንግሥት አካላት የተለያዩ መግለጫዎችን ሰጥተዋል፤ የበጎ አድራጎትና ማህበራት ኤጀንሲ ከላይ ያልኩህን ነው ያለው፤ ፌስ ቡክ ላይ አለ። ዶ/ር ሽፈራው ደግሞ ተቋሙ ወደ መጅሊስ የዞረው የአሸባሪዎች መፈልፈያ ስለሆነ ነው የሚል ቃል ሰጡ። በሁለቱ መካከል ተቃርኖ አለ። መጅሊሱ ግን ካሪኩለሙን እቀይራለሁ፤ አረብኛ የሚባል ት/ት መሰጠት የለበትም በሚል 50 የሚደርሱ መምህራንን አባረረ።

➢ ህዝብን ይወክላል የሚባል መጅሊስ ቢኖር የአወሊያ ወደዚያ መዞር ቅሬታ ያስነሳ ነበር?

የሚያስነሳ አይመስለኝም፤ እኔ በግሌ የምቃወምበት ምክንያት አይኖረኝም።

➢ ከእንቅስቃሴው ጀርባ ያሉ የውጭ ሀገር መንግሥታት አሊያም በገንዘብ፣ በእውቀት፣ በቁሳቁስ የሚረዱ ግለሰቦች የሉም?

በኔ እውቀት ያሉ አይመስለኝም፤ ተክቢራ ለማድረግ ምን ገንዘብ ያስፈልጋል? ድሮም እኮ አርብ አርብ እንሰግዳለን አሁንም ሰግደን ተቃውሞ እናሰማለን። ከዚያ ውጭ በራሪ ወረቀቶች ይበተናሉ፤ ህዝቡ በራሱ ተነሳሽነት የሚያደርጋቸው ናቸው። የመብት ጥያቄውን ሽብርና ሁከት ማልበስ ተገቢ አይመስለኝም።

➢ መንግሥት እኮ እንቅስቃሴውን ሲረዱ ነበር ያላቸውን ሁለት የውጭ ዜጎች በፎቶ አስደግፎ አሳይቶ በ24 ሰዓት ሀገር ለቀው እንዲወጡ አድርጓል።

ይህ ብዙዎችን አስቋል፤ ልጆቹ በቦታው የነበሩ ምስክሮች እንደሚናገሩት የዚክር መጻህፍ ሲበትኑ የነበሩ ልጆች ናቸው። የውዳሴ መፅሐፍ እንደማለት ነው፤ ሁለት አረቦች አረብኛ በማይናገር ማህበረሰብ ውስጥ ገብተው አመፅ ቀሰቀሱ ቢባል አስቂኝ ነው፤ በእለቱ አሰጋጁ ሃጂ ጣሃ በህዝቡ በጣም ተቆጥተው እርግማን እያወረዱበት ህዝቡ አሜን ይል ነበር። አረብኛ አይችልማ ህዝቡ። ሁለቱ አረቦች አመፅ ካነሳሱ ወህኒ ከሚገኙት ስዊዲናውያኑ ጋዜጠኞች በምን በልጠው ነው ያልተከሰሱት። ዜግነታቸው ለምን አልተጠቀሰም? ለፕሮፓጋንዳ ቀለል የሚለው በድፍኑ ማቅረብ ስለነበር መንግሥት ያንን ያደረገ ይመስላል።

➢ ከመንግሥት ጀርባስ ሌላ አህባሽ እንዲሰበክ የሚፈልግ ሀገር/ሀይል አለ?

ከግምት ያለፈ አይደለም፤ ነገር ግን የምዕራብ ሀገራት ከዚህ አካባቢ አይጠፉም የሚል ጭምጭምታ አለ።

➢ አርብ ዕለት ግን ህዝቡ እየሰገደ እያለ አንድ ነገር እንደሚያስብ ሁሉ በአንድ ጊዜ ብድግ ብሎ የተቆጣው እንዴት ነው?

ኢማሙ በተደጋጋሚ ህዝብ ሙስሊሙን ሲያስቆጡ የነበሩ ናቸው፤ ይህ በተደጋጋሚ በሚያደርጉት የአህባሽ ዘመቻ የመጣ ነው፤ አሁን ተለምዷል።

➢ መጅሊሱ ውክልና የለውም ከተባለ የኮሚቴው ውክልናስ ምንድነው?

የተወከሉት 700 ሺህ በሚደርስ የፔቲሽን ድጋፍ ፊርማ ነው። ከሁሉም ክልሎች የ17 ሰዎች ስም በተጠቀሰበት ፊርማ ተፈርሞበት ነው።

➢ ጥያቄያችሁ ተፈታ የሚባለው ምን ሲሆን ነው? መንግሥት ፈታሁ እያለ ነው፤

ግልፅ መልስና ትግበራ ሲያገኙ፤ ነፃ ምርጫ ማድረግ ነው፤ ባለፈው አንዋር መስጊድ መውሊድ በሚል በጠሩት ጉባኤ ነገሮች ገና ያልጠሩ ስለሆነ በሹመት ተተክቶ ይተላለፍ የሚል ፕሮፓዛል ቀርቧል።

➢ 1987 ምርጫ ይካሄዳል ተብሎ ጊዜ አልተቆረጠለትም ይባላል፤ አሁንም ምርጫ ይካሄዳል ተብሎ ቀን ያለመቆረጡ የቀድሞውን ስጋት ቀስቅሷል ይባላል፤ አንተ ትጋራለህ?

በትክክል እጋራለሁ፤ ሁለተኛ የከዚህ ቀደሞቹ ብዙ ብር ዘርፈዋል እኮ! ለፍርድ አልቀረቡም፤ በ2003 የሃጅ ጉዞ ብቻ ከ60 ሚሊዮን ብር በላይ የት እንደገባ አልታወቀም ተብሏል። መንግስትም የተቃወማቸውን ሰዎች በማሰር ድጋፍ እየሰጣቸው ነው፤ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር አቶ ወርቅነህ ገበየሁ እና ሚኒስትር ጁነዲን ሳዶን የመሳሰሉ ትላልቅ ባለስልጣናት ገጠር ድረስ እየገቡ ኡለሞችን ስልጠና እንዲወስዱ እየወተወቱ እና እያስጨነቁ መሆናቸው እንኳ በሙስሊም ሚዲያዎች ተዘግቧል። የተቀዳ ድምጽ ሁሉ አለ።

➢ በግድ የአህባሽ ስልጠና እንዲወስዱ የተደረጉ ኡለማዎች አሉ?

በርካታ ናቸው፤ በተለይ በገጠር አካባቢ። አወሊያም እኮ የተቃውሞው መነሻ ኢማሙን ማባረራቸው ነበር። ብዙ ኢማሞችም ታስረዋል።

➢ ዶ/ር ሰሚር ማን ናቸው?

ከሊባኖሱ AICP ወይም Association of Islamic charitable projects የመጡ ዋና አመራር ናቸው። ሰውየው ሎቢስት ነው፤ ስራው በየሀገሩ አህባሽ ተቀባይነት እንዲያገኝ ማድረግ ነው።

➢ እንቅስቃሴው ተፈጥሯዊ በሆነ መልኩ ከአረቡ አለም መነቃቃት ጋር አይገናኝም? ቀድሞ ያልነበራችሁን አረባዊ ባህል በቀላሉ ማግኘት ችላችኋል ብዬ ነው።

እኔ የማምነው መጅሊሱ ገፍቶ ስለመጣበት መሆኑን ነው። ብዙ መብቶችህን ብታጣ ልትታገስ ትችላለህ። የሀይማኖት መሪህ ነኝ ከሚል አካል ሀይማኖትህን የማስለወጥ ዘመቻ ሲመጣብህ እንዴት ትታገሳለህ? መብታችንን ሁላ እኮ ሸጠውታል!

➢ ስለዚህ ተቃውሞውን መጅሊሱ ራሱ ለኮሰው ማለት ይቻላል?

እውነት ነው፤ ሀይማኖት ቀይር የሚል ከኮሶ የሚመር ነገር ሲያመጡ አሁንስ አበዛችሁት የሚል ተቃውሞ ተነሳ።

➢ ከወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ጋር ይገናኛል እንዴ? ማለቴ ሰልፍ ማድረግ ስለማይቻል፣ ኑሮ ስለተወደደ የአለማዊ ኑሮ ምሬቱን በዚህ ለመወጣት የሚያስብ አካል የለም?

የወደፊቱን አላውቅም። እስካሁን ግን እንዲህ አይነት ሰዎች ገብተው ቢሆን ከፍተኛ ችግር ይፈጠር ነበር። ድንጋይ እንኳ አልተወረወረም።

➢ በእስልምና ወንድማማችነት እንኳ ጥያቄያችሁ ፍትሃዊ ነው የሚላችሁ የለም?

❖ በመንግስትና በድርጅት ደረጃ አለ ብዬ አላስብም፤ አሁን ግን አለም አቀፍ ሆኗል። ብዙዎች ሰምተውታል። አልጀዚራ ላይ ሦስቴ ተዘግቧል።

➢ በየድረ ገፁ የሚለጠፉ ፅሑፎች አሉ፤ አንዳንዶቹ ኢ-ህገመንግሥታዊነትን የሚሰብኩ ናቸው ይባላል፤ ማንን የሚወክሉ ፅሁፎች ናቸው?

አላውቅም፤ ህዝብ እንግዲህ ህዝብ ነው፤ ፎርሙላ የለውም፤ ነገር ግን ኮሚቴው በኦፊሴል በሚያወጣቸው ደብዳቤዎች ብቻ ይወከላል። ለምሳሌ "የውሸት ፕሮፓጋንዳ መደጋገም የሙብት ጥያቄን ህገ ወጥ አያደርገውም" የሚል መግለጫ አውጥቷል፤ ይህ ይወክለዋል።

➢ መንግሥት በዚህ እንቅስቃሴ ሰበብ ከሽብርተኞች ጋር ግንኙነት የፈጠሩ አሉ ይላል፤ እውነት አይደለም?

ሽብርተኛ ተብሎ የተሰየመ ድርጅትኮ ለብቻ አለ፤ ከግንቦት ሰባት ጋር ግንኙነት ያለውን አካል አላውቅም። ከነአብነግ ጋርም አልተገናኘንም።

➢ ጅሃድ ያወጁ አካላት አሉ እየተባለ ነው

ጅሃድ የሚታወጀውኮ ሰይፍ ተይዞ ነው፤ ድንጋይ ባልተወረወረበት ስለ ሰይፍ ማውራት ምን የሚሉት ጅሃድ ነው? ማንስ ላይ ነው የምታውጀው? የተሳሳተ ነዉ፡፡

❖ ለክርስትያን ወንድሞችህ ምን ትላለህ?

የጠየቅነዉ የምናምነዉን ጥሩ መሪ ነዉ፡፡ ያ ሙስሊሙን ከማስተማር ከማረጋጋት የዘለለ ስጋት እንደማይሆናቸዉ አረጋግጥላቸዋለሁ፡፡ በህዝበ ክርስቲያኑ ላይ ያንዣበበ ምን አይነት አደጋ እንደሌለ በቅን ልቡና ይረዳልን፡፡

# አሜን የፊልም ቅኝት

መንገሻ ክሉ

ማክሰኞ አሥር ሰዓት “ሡርግ ከአሜሪካ” የተሰኘውን ፊልም ለማየት ከሰው ጋር ቀጠሮ ይዘን ከመሄዳችን በፊት አለም ሲኒማ ደውዬ ስጠይቅ “ወርሃዊው ፕሮግራም ስለተቀየረ የሚታየው አሜን ነው” ተባልኩ፡፡ እኛም ፕሮግራማችንን ላለመሠረዝ ብቻ ቅር እያለን አሜንን ለማየት ሄድን፡፡ ዓለም ሲኒማ መጥፎ ፊልም እንደማያሳየን እምነት አሳድረን፡፡

በግሌ ፊልሙን ለማየት ያልተሳብኩት ስለ ፊልሙ መረጃ ስላልነበረኝ፣ የፊልሙም ርዕስ ጆሮ ገብ አለመሆኑና የዘውጉ የፍቅር ጀብዱ /Romance adventure/ መሆኑ ነው፡፡ እኛ ባለን የፊልም አቅም የጀብድ ፊልሞችን መስራት ያላዋቂ ሳሚ ሊሆንብን ይችላል በሚል ነው፡፡ በርግጥ ቁርጠኝነቱ ካለ ይቻላል፡፡

ፊልሙ ተጀመረ፤ ከጅማሬው የቅርብ ዕይታ ቀረፃ /close up/ ቢያጥረውም ትኩረታችንን በአስደሳች የታሪክ ፍሰትና የትዕይንት ሽግግር /transition/ እየተቆጣጠረው መገስገሱን ቀጠለ፡፡

የካሜራ እንቅስቃሴውና የሚወስዳቸው ቀረፃዎች /shot size/ በጣም ጥሩ ሲሆኑ ምስሎቹም ከተዋናዮቹ እንቅስቃሴ እኩል ብዙ ሳይቆራረጡ መታየታቸው የተዋናዮቹን ስሜትና እንቅስቃሴ ከፍና ዝቅ ሳይል እንድናይ ረድቶናል፡፡

የፊልሙ ዳይሬክተር የቀረፃ ስራውንና የአዘጋጅነቱን ስራ ደርቦ በመያዝ ላቅ ያለ ጥራት ያለው ስራ በመስራቱ በጣም ይደነቃል፡፡ ፊልሙን እያየሁ ለአፍታ ሳስብ የፊልም ኢንዱስትሪያችን ከፖለቲካችንና ከኢኮኖሚያችን በላቀ ፍጥነት እያደገ መሆኑን አስተዋልኩና ኢህአዴግ ግብርና መር የኢኮኖሚ ስርዓትን ከሚያራምድ ለምን ፊልም መር የኢኮኖሚ ስርዓት አይከተልም? ብዬ ተመኘሁ፡፡ ፊልሙ በተቀላቀለበት ብርዝ የፖለቲካ አስተሳሰቤ በትወናው ረገድ የሚቀረው ነገር ቢኖርም በጣም ጥሩ ነው፡፡ በተለይ የሰለሞን ቦጋለንና የፍየሏን የትወና ብቃት፤ ፍየሏ ግን ምን ያህል እንደተከፈላት ቢነግሩን ጥሩ ነው፡፡ ወይስ ለፊልሙ ምርቃት ታርዳ ይሆን? ከሀገራችን ፊልሞች ለመጀመሪያ ጊዜ የእንስሳ ፊልም ጉልቶ ያየንበት ከመሆኑም በላይ የሀገራችንን የባህላዊ መድኃኒት ግኝትንና ምርምርን ለሌላው ዓለም የሚያስተዋውቅ ነው፡፡

ፊልሙ በሙዚቃው ረገድ ምጣኔው ጥሩ ሲሆን አካባቢንና ትዕይንትን ከመግለጽ አኳያም የሚበረታታ ነው፡፡ የምስልና የድምፅ ጥራቱም በጣም ጥሩ ነው፡፡ ሉሲን ወክላ የተጫወተችው፣ በትወናው በጣም ጥሩ ብትሆንም አብዛኛውን ጊዜ ካሜራው እሷን የሚያሳየን ፊቷን ባለመሆኑ ንግግሯን እንጂ ስሜቷን ልንረዳት ትርቀን ነበር፡፡ ሌላው ግልፅ ስህተት በተለያዩ ስሜቶች ውስጥ ሆና የምትናገራቸው ንግግሮች ተመሳሳይ የድምፅ መጠን ፍጥነትና ቅላፄ መያዙ ነዉ፡፡ ዳይሬክተሩ ትልቅ ስራ ሰርቶ እሷ ላይ መላላት አልነበረበትም፡፡ የዲያሎግ ስልጠና በመስጠት ብቃቷን ከፍ ማድረግ ይችል ነበር፡፡

የሉሲ አባት ሆኖ የተወነው እንቁስላሴ ብዙ ፊልሞቻችን ላይ እንደምናየው ህይወት ያለው የትወና ንግግር ድክመት ይታይበታል፡፡ ይልቅ አደጋ ውስጥ በገባበት ወቅት ስለማይናገርና ስለማይንቀሳቀስ ትክክለኛውን ስሜት ሊያስተላልፍልን ችሏል፡፡ ይሄ ደግሞ አንድ ተዋናይ ፍፁም ትወና ለመስራት መሞት / ከራሱ ዓለም መውጣት/ እንዳለበት ያስገነዝበዋል፡፡

ፊልሙ ውስጥ ጮክ ብሎ የሚሠማ እውነት ያዘለ ንግግር ሰምተናል፡፡ ይኸውም ሽፍታ ተብዬውን እንዲገድሉ በክፉ ካድሬ /የከተማ ሽፍታ/ የተላኩ ሁለት ገበሬዎች በሽፍታው እጅ ሲወድቁ የተናገሩት እውነት “አንተን መግደል ፈልገን ሳይሆን ዕምቢ ብንል ማዳበሪያ ይከለክሉናል ብለን ነው” የሚለዉ፡፡ ይሄ የሀገራችን ገበሬዎች ከሚገጥሙዋቸው ፖለቲካዊ ችግሮች አንዱ ነውና፡፡ የአሜን ፊልም ድርሰት የተፃፈው በአምስት ፀሐፊዎች ሲሆን ስድስተኛ ፀሐፊያቸው ቢያደርጉኝ ኖሮ አርማቸው የነበሩ አረሞች፡-

1. የፊልሙ መነሻ ክፍል /set up/ የገፀ ባህርያቱን ማንነትና የርስ በርስ መስተጋብር እንዲሁም አካባቢያቸውን በደንብ ሳያስቃኘንና ሳያስተዋውቀን እንደ አንዳንድ አክሽን ፊልሞች በቀጥታ ከሁለት ደቂቃ ባልበለጠ መንደርደሪያ ትዕይነት ወደ ፊልሙ ሁለተኛ ክፍል ይሸጋገራል፡፡ ሉሲን ወደ አባቷ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት ወደ መጀመሪያው ሴራ /plot point/ የማንነት ጥያቄ ያን ያህል መጣደፍ አግባብ አልነበረም፡፡

2. ከፊልሙ ጅማሬ ለፊልሙ ጡዘት መነሻ የነበረው የሉሲ የማንነት ፍለጋ ጉዳይ ሆኖ ሣለ በቀላሉ የማይበርድ የሚመስለው የማንነት ፍለጋ ባጭሩ መቅረት አሣማኝ አይደለም፡፡ የማንነት ጥያቄ ጥቂት ማህበረሰብንና ባህልን በማየት ብቻ አይመለስምና ምናልባት በማንነት ፍለጋው ላይ ሌላ ሴራ በመፍጠር የፊልሙን ጡዘት ከፍ ማድረግ ተፈልጐም ከሆነ ብዙም አይመከርም፤ ማንነትን ፍለጋ ራሱ ውብና በሴራዎች የተሞላ ነውና፡፡

3. በፊልሙ ሦስተኛ ክፍል Act3/ ታሪኩ በተገቢው መልኩና የጊዜ ርዝመት አልዳበረም፡፡ ለፊልሙ ሁለተኛ ክፍል /Act2/ የተሰጠውን ትልቅ ትኩረት ያህል ለመግቢያውና ለመውጫው አልተሰጠውም፡፡

4. የፊልሙ ርዕስ ፊልሙ ስናይ ከተሠጠው ርዕስ የተሻሉና ሳቢ የሆኑ ርዕሶች ውስጡ ሞልተው አስተውለናል፡፡

ሌላው አስጐብኚው ሼፌር ዳንኤል ብልሃትና ስነምግባር በጐደለው አኳኋን ከአሜሪካ የመጣችውን ሉሲን ለማማለል መጣሩ አያስደስትም፡፡ የአስጐብኚ ድርጅቶችም ገፅታ አይመስለኝም፡፡

ሆኖም ፊልሙ ካለው የፕሮዳክሽን ጥንካሬና ውበት የተነሳ ተመልካቹ አንድም ስህተት ከፊልሙ ውስጥ እንዲያገኝ እድል አይሰጠውም፡፡ እንደኔ ዕይታ ይህ ፊልም መሣጭ እውነታዎችን የያዘ በመሆኑ በጣም ከምንወዳቸው ጥቂት አስቂኝ የፍቅር ፊልሞች በላይ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ፕሮዲውሰሩም ፊልሙን ለማስተዋወቅ ከዚህ በላይ ጥረት ማድረግ በተለይ የቴቪ ማስታወቂያውን መቀየር ይኖርበታል፡፡ አንዱ ምክንያት ከዚህ በፊት የፍቅርና የበቀል ፊልም ተብለን ያየናቸው ፊልሞች በጠቅላላ የወደድናቸው አይደሉም፡፡ በመሠረቱ በፊልሙ ውስጥ ፍቅርንና በቀልን ሣይሆን ማንነትን ፍለጋና የፍትህ ርሃብን ነው ያየነው፡፡ ፊልሙ ሲጠናቀቅ ወደንም ሳንወድም የገባን ቆመን አሜን ብለን ለአሜን ከፍ ባለ አድናቆት አጨበጨብን፤ ቸብቸብቸብ . . . ፡፡

# “ጆሮዎቼ መገሉ!”

አቶ ግርሻ መርጫ የ68 ዓመት አዛውንት ናቸው፡፡ አቶ ግርሻ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግራ ቀኝ ጆሮዎቻቸው እየመገሉ መስማት እየተሳናቸው መጥቷል፡፡ ጆሮዎቻቸው መቁሰል እንደ ጀመሩ ያልገቡበት ቀዳዳ አልነበረም፡፡ ከአበሻ መድሃኒት ጀምሮ እስከ ታወቁ ሐኪም ቤቶች ድረስ ደክመዋል፡፡ መፍትሄ ግን አላገኙም፡፡ አሁን በቅርቡ አንድ የታወቀ ያንገት በላይ ስፔሻሊስት አለ ብለዋቸው ተጣድፈው ቀረቡ፡፡

እውነትም ሐኪሙ አዋቂ ኖሮ አቶ ግርሻን በጥንቃቄ ከመረመራቸው በኋላ ህመሙ መቸ እንደ ጀመራቸውና እንዴት እንደ ጀመራቸው ጠየቃቸው፡፡

“ጆሮዎቼ መቁሰል የጀመሩት ከ83 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ መምገልና መነፍረቅ የጀመሩት ግን አሁን በቅርቡ ነው፡፡ ይህንኑ ተከትሎ መስማት እየተቸገርኩ ነው” በማለት ተረኩለት፡፡ ዶ/ሩ ትንሽ ፈገግ ብሎ “አቶ ግርሻ፤ ቴሌቪዥን ይከታተላሉ?” ሲል ጠየቃቸው፡፡

“በሚገባ እንጂ፡፡ ዐይኖቼን አፍጥጬ ጆሮዎቼን አቅርፌ ነው የምከታተለው” አሉት፡፡

“ለዚህ ነው ጆሮዎችዎ የቆሰሉትና የመገሉት፡፡ ሊሰሙ የማይፈልጉትን ነገሮች እየሰሙ ካቅማቸው በላይ በመሆናቸው ታንቡሮቻቸው በጣም ቆስለዋል፡፡ አክሜ ለማዳን ጥረት አደርጋለሁ፡፡ ካሁን በኋላ ግን ዐይኖችዎ ደግሞ እንዳይጠፉ ዐፍጥጠው ከመመልከት ይቆጠቡ” ብሏቸው እርፍ፡፡

# የሙስሊሞች ጉዳይ . . .

ከገፅ 6 የዞረ

ማንነት እንዲሁም ለሀይማኖታዊ አጥባቂነት የሚያመቸውን የማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር መላላት ዕድል አግኝተዋል፡፡

ሦስተኛ ደረጃ የሚነሳው የ21ኛው ክ/ዘ/ማብቂያ ሁለት ግድፈቶች ናቸው፤ የግራ ዘመም ቡድኑ የመንግሥት ስልጣን ሲይዝ የሀይማኖትና መንግሥት መለያየት በማወጁ የነገሮችን ጫፍ ከአዋጁ ርቀት ፈቅ የማይል አድርጎ ወሰደው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በሀይለኛ ብሔርተኝነት የነደደው ግራ ዘመም ቡድን የያዛቸው ብሔረተኛ ሙስሊም ግለሰቦች ሀይማኖታዊ ክንፉን ሙሉ በሙሉ የሚወክሉ አድርጎ ማሰቡ ነው፡፡ እዚህ ላይ ምሁራኖች አንድ ዋነኛ ችግር ያነሳሉ፣ በብሔርተኛ ቡድን ውስጥ ያሉት ሙስሊም ግለሰቦች ሀይማኖታዊ ክንፉን ሙሉ በሙሉ ባይወክሉም ይባስ ምንም እንዳይወክሉ ያደረጋቸው ደግሞ ቀደም ብለው ወደ ፖለቲካው ከመምጣታቸው በፊት ያላቸው ህብረተሰባዊ ተቀባይነት ጥልቀት የሌለው መሆኑን ያለማረጋገጡ ነው፡፡

በአጠቃላይ ኢህአዴግ ህገ መንግሥታዊ ያደረገው የሀይማኖት እኩልነትና ነጻነት ጥያቄ ዘርፈ ብዙ አፋፋሚ (exacerbating) አንጓዎች አጋጥመውታል፡፡ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያክል ቀድሞ የሙስሊሞች የብቻ ስራ ከመሆኑም በላይ የበታችነት መገለጫ ነው ያልነው ንግድ በመጀመሪያ በክርስትያኑም ጭምር የሚሰራ ስራ እየሆነ ከመምጣቱም በላይ ዛሬ ዛሬ ኢህአዴግ የመረቃቸው ካድሬዎች፣ ባለስልጣናት እንዲሁም የድርጅቱ አባል ድርጅቶች «የማይነካ» ስራ ሆኗል፡፡ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ያለው አማራጭ ልጆቹን ማስተማር፤ ከዚያም የመንግሥት ስራ እንዲያገኙ መፀለይ፤ መንግሥት ደግሞ እንኳን ለተመረቀ ሁሉ ቀርቶ ለአባላቱ መሆን እያቃታው መጥቷል፡፡

የሙስሊሙ ማህበረሰብ ልጆች ዘመናዊ እውቀት መገብየት፣ ከስራ አጥነት እንዲሁም የመገናኛ አውታሮች መስፋፋት ጋር ተዳምሮ በታሪክ የተነፈጓቸውን ጥያቄዎች እንዲያነሱ አስገድዷቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ከገጠር ወደ ከተማ ለሚደረገው ከፍተኛ ፍልሰት የስነ ልቦና ክፍተት መሙያ እየሆኑ የመጡት የኃይማኖት ተቋማት እነዚህን ምልምል የሙብት ጥያቄ አንጋቢዎች ለመማረክ ጊዜ አይፈጅባቸውም፡፡የኢህአዴግ መንግሥት የማንነት ስዕል የሚከሰተው እዚህ መሆኑ ነው፡፡ ኢህአዴግ ከላይ ያየናቸውን የሙስሊሙ ህብረተሰብ አዳዲስ ማንነቶችና ጥያቄዎች ለማስተናገድ ምንም አይነት ዝግጅት አላደረገም፡፡ ኢህአዴግ ከሚኒስትሮቹ ውስጥ ሁለት ወይም ሦስቱ ሙስሊሞች ከሆኑ ከታሪካዊ ፖለቲካዊ ውክልናቸው አንጻር መች አነሳቸው የሚል አቋም አለው፡፡ ሌላው ጉዳይ ኢህአዴግ ሲያጥላላው የነበረውን የኢትዮጵያዊነት ትምእርት ክርስቲያናዊነት ዳግም ለመስበክ መገደዱ ነው፡፡ በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ “አዲስቷ ኢትዮጵያን” ገሸሽ በማድረግ “የቀድሞ ታላቅነቷን መመለስ” በሚል ሀሳብ ላይ አተኩሯል፡፡ ዞሮ ዞሮ ክርስቲያናዊ ባህላዊ ትውፊት የገነባውን ታሪክ ስለመድገም በመሆኑ ሙስሊሞች ወደተለመደው ጠርዝ የሚገፈትራቸው መስሎ ቢሰማቸው አልተሳሳቱም፡፡ ኢህአዴግ ሀይማኖትን ፖለቲካዊ ማድረግ (politicization of religion) የሚለው ሀሳብ ካለገደብ የፈራው ይመስላል፡፡ በመሆኑም ትንሽ ኮሽ ላለ ሀይማኖታዊ ጥያቄ ስሱ በመሆን ያልተመጣጠነ መልስ ወደ መስጠት ለመሄድ ጊዜ አልወሰደበትም፡፡ ሀይማኖታዊ ዋጋ ለመክፈል ለተዘጋጀ ሰው ይህ የማይገኝ አጋጣሚ በመሆኑ ጥያቄውን የባሰውኑ ያጠናክረዋል፡፡ በሌላ መልኩ ወንበሩ የተነቃነቀበት የወቅቱ መጅሊስ የሙብት ጠያቂዎቹን በአሸባሪነት በመወንጀልና ተመሳሳይ መረጃ ለመንግሥት በማቀበል መንግሥትን ብዙ ርቀት ነገር ግን በተሳሳተ ጎዳና መርቶታል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ኢህአዴግ በፖለቲካ ስራ ፈጣሪዎች (political enterprenuers) በመሞቱ ‹እሳቱን› እያጋጋሉ መልሰው በማጥፋት ራሳቸውን ለሹመት የሚያጩ ካድሬዎች ነገሩን ቀልድ አድርገውታል፡፡ በዚህ ላይ የአቶ መለስ የ21 ዓመታት “የካድሬ መምህርነት አባዜ” ወይም በዘመናዊ ትምህርት ቤት “One 0 One /101 ” የሚባለው ኮርስ አይነት “ሁሉንም እኔ ነኝ የማስረዳው” አባዜ ነው፡፡ አቶ መለስ የዛሬዎቹ ወጣት ሙስሊሞች ልክ ከ20 ዓመታት በፊት እንደነበሩት ሙስሊም ነጋዴዎች አሊያም የደደቢት ተማሪ ካድሬዎቻቸው ያነበቡም፣ ያወቁም አይመስላቸውም፡፡ ፓርላማ ተገኝተው የኢህበሽን፣ የሰላፊን፣ የሱፊንና . . . ስነ መለኮት በመተንተን «ስሙኝ» ይላሉ፡፡

ለማንኛዉም የጥያቄያችሁ ትክክለኛዉ ምክንያት ምንድነዉ? ታሪካዊ አመጣጡስ ምን ይመስላል? መንግስት «ህገ-መንግስታዊ አካሄድ ያልመረጡ ሀይሎች» የሚለዉ ማንን ነዉ? «ተገቢ ምላሽ ቢያገኙም ለፖለቲካዊ ፍላጎት እየተንቀሳቀሱ ነዉ» የሚባለዉስ? ትምህርትና ሀይማኖት ተለያይተዋል በሚባልበት በዚህ ዘመን የአወሊያ ትምህርት ቤት ጥያቄያችሁ ምንድነዉ? አህባሽ ሲሰበክ ለመንግስት ምን ይጠቅማል? ለከፍተኛ ጥፋት የተዘጋጀ ሀይል በዉስጣችሁ አለ? ክርስቲያኑን ለማጥፋት ትዶልታላችሁ? መጨረሻችሁ እስላማዊ መንግስት ነው? ወዘተ ጥያቄዎችን አቅርቤ እነሱልጣንን፣ እነ ሰኢድ ጋሼን እንዲሁም በጉዳዩ እዉቀት አላቸዉ የተባሉትን ወዘተ ጠየቅሁ፤ ወዳጅነታችንም ልክ የወትሮዉ ነው፡፡ ታዲያ ከመለስ ዜናዊ መንግስትና ከነሰሚራና ሱልጣን ማንን አምናለሁ? እነ ሱልጣን እንደመንግስት ዋሽተዉኝ አያዉቁም፡፡

የሐሳቤ ማጠቃለያ፣ የነገሩን አያያዝ የተሳሳተው ኢህአዴግ ዛሬ ማጣፊያ ሲያጥረው “የማንም ሀይማኖት ተከታይ የሆናችሁ፣ ‹አክራሪዎቹን› ተዋጓቸው” ማለቱ ምን ይሆን የሚለውን መገመት ነው፡፡ ነገሩ ህገ መንግሥታዊም ሆነ የእስላም መንግሥት ጉዳይ የሚባልበት ደረጃ ላይ አይመስልም፡፡ ከእስላማዊ መንግሥቱም፣ ከህገ መንግሥቱም በላይ የመለስ ዜናዊ መንበር አለ፡፡ ያንን ተከላከሉት ከሆነ አብሮ አደጎቼን እነ ሱልጣንን፣ ሰሚራን፣ ሚራጅን፣ ፍጤንና ሰይድ ጋሼን ከህገ መንግሥታዊ ጥያቄያቸው ሁሉ ተከላክዬ ሙስሊም ወንድም እህቶቼን ጠላት አድርጌ አልገዛቸውም፡፡ የመለስ ዜናዊን ዙፋን አግአዚ ይጠብቅ፡፡ የሙስሊሞች ጉዳይ የኢትዮጵያ ጉዳይ፣ የህገመንግስት ጉዳይ የሁላችን ጉዳይ፣ የመለስ ዜናዊ ጉዳይ የራሳቸው ጉዳይ፡፡

# ርዕዮት፣ ኤልሻዳይ፣ የአቶ መለስ ፎቶና የጊዮን ሆቴል ምሽት

ብዙአየሁ ወንድሙ

ለሆነ አንድ ጉዳይ የቆየ ማስታወሻዬን ሳገላብጥ ህዳር ወር 2003 ዓ.ም ላይ ደረስኩ፡፡ ኤልሻዳይ ከጋዜጠኞች ጋር በጊዮን ሆቴል ያደረገው ውይይት ይላል፡፡ ያን ዕለት ምሽት አልፎ አልፎ ትዝ የሚለኝ ምክንያት ነበረኝ እና ቀልቤን ሳበው፡፡ የምፈልገውን ማስታወሻ ተውኩና ማየት ጀመርኩ፡፡ ማስታወሻው በፍጥነትና በአጭር በአጭሩ የተያዘ ነበር፡፡ ከተለያየ ሚዲያ የተሰባሰብን በግምት ከ20 በላይ ጋዜጠኞች የተገኘንበት ምሽት ነው፡፡

ጋዜጠኞችን የጠራው ኤልሻዳይ የተባለ ግብረሰናይ ድርጅት ነው፡፡ ማስታወሻዬን ከተመለከትኩ በኋላ ለደቂቃዎች በሐሳብ ማዕበል ውስጥ ቆየሁ፡፡ የጋዜጠኞችና የኤልሻዳይ ተወካዮች ንትርክ፣ የአቶ መለስ ፎቶ ጉዳይ ክርክር ታወሰኝ፡፡ ጋዜጠኞች በሐሳብ ሁለት ቦታ ተከፍለው የሚወራወሩት ቃላት ትዝ አለኝ፡፡ በዚህ ምሽት ላይ ዘወትር የማስታውሰው የጋዜጠኛና መምህርት ርዕዮት ዓለሙ አንደበት ትዝ ብሎ ብቻዬን ፈገግ አደረገኝ፡፡ የጋዜጠኛ ስለሺ ሐጐስ ጠንካራ ሐሳቦች ተመላለሱብኝ፡፡ የምሽቱን ዝግጅት አውግዛ ስትወጣ የፊቷ ብስጭትና አረማመድ ታየኝ፡፡ አሃ!! "ሽብርተኛዋ" አልኩና ወረቀትና አስክሪብቶዬን አነሳሁ፡፡ የዕለቱን ገጠመኝ ለአንባቢያን ለማካፈል ወሰንኩኝ፡፡

ኤልሻዳይ የተባለው ግብረሰናይ ድርጅት የተሰማራው ጐዳና ተዳዳሪዎችን በማቋቋም ሥራ ላይ ነው፡፡ ልመናን ማስቀረት እንዲቻል እየሰራ መሆኑን ይገልፃል፡፡ የዚያን ዕለት ምሽት ዓላማ የድርጅቱን የሦስት ዓመት እቅዱን ማስተዋወቅ ነው፡፡ ሚዲያዎች በጠቅላላ የኤልሻዳይን ዕቅድ ተገንዝበው ሽፋን እንደሰጡት የታሰበ ነው፡፡ የዚህ ጹሑፍ አቅራቢ ለዚህ ምሽት የመጣሁት ከጐግል ጋዜጣ ሲሆን ርዕዮት ዓለሙ ደግሞ ከአዲስ ፕሬስ ጋዜጣ፣ እንዲሁም ስለሺ ሀጐስ፣ ከ96.3 ኤፍ ኤም ሬዲዮ ሲሆን ከ20 በላይ የመንግስትና የግል ሚዲያ ጋዜጠኞች ተገኝተዋል፡፡

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ወደዚህ ስብሰባ ከመግባቴ በፊት የ6 ቤተክርስቲያን ቀሳወስት ኤልሻዳይ የተባለው ድርጅት ፈፀሙብን ያሉትን በደልና እየፈፀመ ነው የሚሉት ወንጀል መረጃ በእጄ ይገኝ ነበር፡፡ ይህንን መጨረሻ ላይ እመለስበታለሁ፡፡

ልክ ከምሽቱ 12 ሰዓት ሲሆን በጥሪው መሠረት ጊዮን ሆቴል ሳባ አዳራሽ ጋዜጠኞች ተሰብስበን ተገኘን፡፡ የድርጅቱ መሥራችና ኃላፊ አቶ ይማነ እና ሌሎች ሦስት የድርጅቱ ሠራተኞች ተገኝተዋል፡፡ ሠራተኞቹ ለጋዜጠኞች ጹሑፋቸውን ለማቅረብ ላፕቶፓቸውን ዝግጁ አድርገዋል፡፡ ፕሮጀክተሩና ስክሪኑም (ምስል መከሳቸውም) ዝግጁ ሆኗል፡፡ ትምህርቱ ቀጠለ፡፡ "ጋዜጠኞች ጥሪያችንን አክብራችሁ ስለመጣችሁ እናመሰግናለን፡፡ የዚህ ዝግጅት ዓላማ ድርጅታችን /ኤልሻዳይ/ መንግስት ካወጣው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አኳያ በዚህ አምስት ዓመት ልመናን ከመላው ኢትዮጵያ ለማጥፋት እቅዳችንን ማሳወቅ ነው፡፡ ከሦስት ዓመት በኋላ አባባ ዳቦ ግዙልኝ የሚል ህፃን ሳይሆን አባባ የጫማዎ ክር ተፈታ የሚል ህፃን የሚኖርበት አገር ይሆናል፡፡ ጋዜጠኞች ተባብራችሁን አብረን እንድንሰራ ብለን ነው" ብለው ለባለ ላፕቶፕ አስተላለፉ፡፡ ባለላፕቶፑ ቀጠለ የድርጅቱን ዓርማና መሪ ቃል በስክሪን ላይ ታየ፡፡ የመጀመሪያው ምስል ሲወጣ የአቶ መለስ ዜናዊ በመስቀል አደባባይ "ለመጪው ትውልድ ልመናን አናወርስም" የሚለው መፈክር የኤልሻዳይ ዓርማ ሆኖ ቀረበ፡፡ አሁንም ገለፃው ቀጠለ "ከተማችን የአገሪቱ ርዕሰ ከተማ ናት፡፡ የአፍሪካ ዋና ከተማ ናት፡፡ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ጽ/ቤት የሚገኝበት ነው፡፡ በርካታ ዲፕሎማቶች ያሉበት ነው፡፡ ሆኖም ግን ጐዳና ተዳዳሪ በዛ፡፡ በረንዳ የሚተኛው ብዙ ነው፡፡ የሚተኙት የሚበሉት፤ የሚፀዳዱት አንድ ቦታ ነው፡፡ ከተማውን አቆሸሹት፡፡ የሥራ ባህላቸው መጥፎ ነው፡፡ ከዚህ በፊት በርካታ ጊዜ እየሰበሰብን በመኪና ጭነን አገራቸው ስናደርሳቸው፤ ዘመዶቻቸውን ጠይቀው ተመልሰው ይመጣሉ፡፡ ከእንዲህ እንዳይመለሱ እናደርጋለን፡፡ ይህንን ለማስፈፀም ገንዘብ ያስፈልገናል፡፡ ግለሰቦችም ድርጅቶችም እድሮችም ገንዘብ ሊረዱን ይገባል፡፡ ሚዲያዎች ሁላችሁም ትኩረት ሰጥታችሁ ልትዘግቡልን ይገባል" ቃል በቃል ባይሆንም የሚል መንፈስ የነበረው ነው፡፡

ጋዜጠኞች ጥያቄ ማቅረብ ጀመሩ፡፡ ቴዲ አፍሮ ከእስር ቤት እንደወጣ አዲስ አበባ ስታዲዮም ዘፍኖ የሰበሰበውን አንድ ሚሊዮን ብር ምን ላይ እንደዋለ ግልጽ አይደለም፡፡ መንግስታዊ ያልሆንን ግብረሰና ድርጅት ነን እያላችሁ የአቶ መለስን ፎቶግራፍ ፊት ለፊት ዓርማችሁ አድርጋችሁ የወጣችሁት ለምንድ ነው? ጐዳና ላይ የወጡትን ሰዎች እየሰበሰባችሁ መልሰናል ብላችኋል፡፡ ስትመልሷቸው ከቤታቸው ተፈናቅለው ጐዳና የወጡበት ምክንያት ምንድነው? ዜጐች ከቤታቸውና ከሥራቸው የሚፈናቀሉበት ችግር ሳይፈታ እንዴት ልመናንና ጐዳና ተዳዳሪነትን ማድረቅ ይቻላል? እንዴት ዜጐች ወደ ጐዳና የሚወጡት የሥራ ባህል እጦት ነው ይባላል? በቅርቡ በረንዳ ተኝተው ከተገኙት አረጋዊያን መካከል በቀድሞ መንግሥት ሚኒስትር የነበሩ ሰው ተገኝተዋል፡፡ እውነት እኚህ ሰው የሥራ ባህል ማጣት ነው ጐዳና ያስወጣቸው? ዜጐች ወደ ጐዳና የሚወጡት በመልካም አስተዳድር እጦት አይደለም? ጐዳና ላይ ወጥተው ረሃብ እርዛትና ብርድ ከሚያሰቃያቸው ይልቅ እናንተን ያሳስባችሁ የከተማው መቆሸሽ ነው? ልመናን እያወገዛችሁ፤ እናንተ እንድትለምኑ ፍቃድ አላችሁ? የሚሉ ይገኙበታል፡፡

ጋዜጠኞች ጥያቄ ብቻ ሳይሆን የድርጅቱን ገለጻና ዕቅድ በመቃወም ጠንከራ ሐሳቦች ቀረቡ፡፡ የድርጅቱን ሐሳብ አብጠለጠሉት፡፡ ጋዜጠኞችም ሦስት ቦታ ተከፈሉ፡፡ የተወሰኑ ጋዜጠኞች የድርጅቱ ዓላማና እቅድ ግልፅነት የጐደለው ጥያቄ የሚያጭር በመሆኑ አወገዙት፡፡ ጥቂት ጋዜጠኞች ድርጅቱን በመደገፍ ሐሳብ ሰጡ፡፡ የተወሰኑት መሐል ሰፋሪ ሆነው ተቀመጡ፡፡-

የድርጅቱ አመራሮች መልስ ሰጡ፡፡ በተለይ ኃላፊው አቶ ይማነ "የአቶ መለስን ፎቶ የተጠቀምነው በጣም ስለምንወደው ነው፡፡ እኔ በግሌ ከሰማይ በታች እዚህ ምድር ላይ ያለው ትልቅ ሰው እሱ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡" በማለት መለሱ፡፡ ሌላው የድርጅቱ ሠራተኛ ሲመልስ "አሁን አገሪቱን የሚመራው መለስ ነው፡፡ ልደቱ ቢሆን ልደቱን እናደርግ ነበር፡፡ ብርቱካን ብትሆን ብርቱካንን እናደርግ ነበር፡፡ ኦባማን እንዳናደርግ ኦባማ የኢትዮጵያ መሪ አይደለም፡፡ ማንን እንድናደርግ ፈለጋችሁ? እኛ ሰዎች የሚፈናቀሉት በመልካም አስተዳደር ነው፡፡ ማለት አንችልም፡፡ እና ከምንላችሁ እየወጣችሁ ሐሳብ ከመስጠትና ጥያቄ ከማቅረብ ተቆጠቡ" የሚል መንፈስ ያለው ማሳሰቢ ተሰጠ፡፡ በመቀጠልም "ድሮ ቤተመንግስት ወንጀል የሚፈፀምበት ግቢ ነበር፡፡ ዛሬ ስለልመና የሚመከርበት ግቢ ሆኗል፡፡ ከሚኒስትሮች ጋር ከሰባት ጊዜ በላይ በቤተመንግሥት ተሰብስበን መክረናል፡፡ እናንተም ልመናን በማውገዝ መፃፍ አለባችሁ" ተባለ፡፡ ትዕዛዝ መመሪያ መሆኑ ነው፡፡

ጋዜጠኞችም ኤልሻዳይን ጥያቄ ውስጥ የከተቱ ሐሳቦችና ጥያቄዎች አዥጐደጐዱ፡፡ ጋዜጠኛ ዝም ብሎ ጻፍ የተባለውን እንደማይጽፍ አቋሙን የገለፀበት ምሽት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ጠንካራ ሐሳብ ያቀርቡ ከነበሩት ጥቂት ጋዜጠኞች አንዷ የሆነቺው ጋዜጠኛና መምህርት ርዕዮት ዓለሙ አንዷ ናት፡፡ ከበርካታ ሐሳብ ልውውጥ በኋላ ርዕዮት "ውድ ጊዜን ሰውቼ እዚህ አሳፋሪ ምሽት ላይ ስለተገኘሁ አዝናለሁ" በማለት ከወንበሯ ተነሳች፡፡ ጋዜጠኛ ስለሺ ሀጐስ በተመሳሳ ሁኔታ ገለጻውን በማውገዝ ሁለቱም አዳራሹን ለቀው ወጡ፡፡ ለጥቂት ደቂቃ አዳራሹ መደማመጥ ተሳነው፡፡ አቶ ይማነ እና ርዕዮትን ተከትሎ ወጣ፡፡ የቀሩት የድርጅቱ ሠራተኞች መድረኩን ማረጋጋት አልቻሉም፡፡ የጋዜጠኞች ቁጣ ቀጠለ፡፡ ጥያቄዎቻችን በአግባቡ አልተመለሱም፡፡ እኛን እንዴት ብትቆጥሩን ነው እንዲህ ዓይነት ገለጻ የምታዘጋጁልን የሚል ነበር፡፡ አቶ ይማነ ተመልሶ ወደ አዳራሹ ተመልሶ ይቅርታ በመጠየቅ ለማረጋጋት ሞከረ፡፡ ብዙም አልተሳካለትም፡፡ ፕሮግራሙ እንዲቋረጥና በሚቀጥለው ሳምንት እንዲቀጥል ተብሎ ተወሰነ፡፡ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ቀድሜ ከአዳራሹ ስወጣ ከአዳራሹ ውጪ ባለው ኮሪደር ላይ ርዕዮት ዓለሙና ስለሺ ሀጐስ በሐሳብ ተውጠው ተቀምጠዋል አይቼአቸዋለሁ፡፡ አልፌአቸው ወደ ቤቴ ሄድኩኝ፡፡ ቤቴ ከደረስኩኝ በኋላ ለምን እንደተቀመጡ ስላነጋግራቸው መሄዴ ቆጨኝ፡፡

በማግስቱ ጥዋት ጋዜጠኛ ለስለሺ ዘንድ ደውዬ በሠላም ወደ የቤታቸው መግባታቸውን፤ ከአዳራሽ ከወጡ በኋላ ለምን ኮሪደር ላይ እንደተቀመጡ ጠየኩት፡፡ "ስብሰባው ይቅር በስማችሁ የተዘጋጀውን ራት ሳትቀምስ አትሂዱ ብለው በባህላችን ስለለመኑን ተመልሰን ነው፡፡ የተቀመጥነው ራት በልተን ሄድን" አለኝ፡፡ በመቀጠልም ወደ ቦሌ ወደሚገኘው ኤልሻዳይ ጽ/ቤት አመራሁ፡፡ ከ6 ቤተክርስቲያናት የመጣ የካህናት አቤቱታ አስረዳኋቸው፡፡ እያንዳንዱ ቄስ ከንስሐ ልጁ ለምኖና ስብስቦ ከብር 500-1000 ለኤልሻዳ ገቢ እንዲያደርግ ከቤተክህነት ለየደብሩ ትዕዛዝ የተሰጠ መሆኑ አግባብ አለመሆኑን፡፡ አንሰበስብም ካሉ ካህናት ደግሞ ከወር ደሞዛቸው ገንዘብ የተቆረጠበት ደረሰኝ መያዜን፤ እያንዳንዱ እድር ለኤልሻዳይ ገንዘብ እንዲሰጥ መታዘዙን፤ ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊርጊስ በተገኙበት በሚሊኒየም አዳራሽ ዝግጁ እንደሚደረግ ተገልጾ ገቢው ለኤልሻዳይ የሆነ ትኬት በመቶ 100 ብር በግዳጅ ለየቤተክርስቲያኑና ለየድርጅቶች መሸጡን ማስረጃ እንዳለኝ አስረዳኋቸው፡፡

በአቶ መለስ ፎቶ በማስፈራራት ገንዘብ እየተሰበሰበ መሆኑ ተገቢ አለመሆኑን የሚቃወሙ ዜጐች መኖራቸውን ለማሳየት ሞከሩ፡፡ የኤልሻዳይ አመራሮች በበኩላቸው ጋዜጠኞች የመድረኩን ዝግጅት ማድፍረሳቸውን ቅሬታ እንደፈጠረባቸው ገልፀው ሳምንት በጉዳዩ ላይ እንደ አዲስ ለመነጋገር እንደሚፈልጉ ገለጹልኝ፡፡ የሳምንቱም ስብሰባ ቀረ፡፡ ከወራት በፊት ኤልሻዳይም የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ፡፡ ርዕዮት ዓለሙም በሽብርተኝነት ቃሊቲ ገባች፡፡ ከተወሰኑ ወራት በኋለ ደግሞ የኤልሻዳይ አመራሮች በሙስና ቃሊቲ ገቡ፡፡

## "ያንን ዛፍ ቆረጡት እነልክ አያውቁ ምን ያፈራ ይሆን? ብለው ሳይጠይቁ"

**እመቤት ኃይሌ**

ይህን የሽለላ ወይም የቀረርቶ የግጥም ስንኝ ወይም ሐረግ ስሰማ ሁልጊዜ አእምሮዬ መልስ የሌለው ጥያቄ ይፈጥርብኛል፡፡ መልስ የሌለው ጥያቄ ደግሞ ወይ ጥያቄው በትክክል አልቀረበም፤ ወይም ደግሞ ጠያቂው ግለሰብ ጥያቄውን በአግባቡ አላቀረበውም ወደሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሰኛል፡፡ አሁን ላወራ የፈለግኩት ስለ ጥያቄ አቀራረብና ስለመልስ አሠጣጥ አይደለም፡፡ በግጥሙ ዙሪያ ስላለው ሃሳብ እንጂ፡፡

በግጥሙ ውስጥ ዛፍ ቆራጭ፣ ፍሬ እና ልክ አለማወቅ የሚሉ ዓብያት ቃላት ተሠንዝረዋል፡፡ እስቲ እያንዳንዳቸውን በነጠላ እንመልከታቸው፡፡

ዛፍ እንዲሁ በቁሙ ስንመለከተው ከዕፅዋት የሚመደብ ነው፡፡ የሚሠጠው ጥቅም ለቤት መሣሪያነት፣ ምሰሶና ማገር ሲደክም ጥላ ማረፊያ፣ ሠው ከሠው ሲጋጭ ሸንጎ የሚቀመጡበት፣ አንድ ማህበረሰብ እንደ አድባር የሚገለገልበት ሲሆን ፍሬዉ ደግሞ ሲመገቡት ለሰውነት ይስማማል፣ ይገነባል፣ ከበሽታ ይከላከላል፡፡ ሁሉም ፍሬ ግን ይበላል ወይንም ለምግብነት ይውላል ማለት አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ የማይበላም ቢሆን ፍሬ የራሱን ዘር ጠብቆ ለማቆየት እንኳን ቢሆን በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

ዛፍ ቆራጭ ግለሰብ በገንዘብ ከተስማማ ማንኛውንም የዛፍ ዓይነት ከመቁረጥ ወደ ኋላ የማይል አካል ነው፡፡

‹‹ልክ አለማወቅ›› የሚለዉ አገላለፅ አለማገናዘብን የሚጠቁም ነው፡፡ የዛሬውንና የወደፊቱን የዛፉን ጥቅም ካለመረዳት የሚመጣ ጭፍን ጥፋትን ያመለክታል፡፡ እንግዲህ ይህን ከላይ የተጠቀሰውን የግጥም ስንኝ ስንመለከተው ወይንም ስንመረምረው፤ በሲንቦል (በአምሳያ ደረጃ ዛፍ ጥላ ከለላ የሚሆን የትልቅ ሰው አምሳያ( ትክ) ነው፡፡ ዛፍ ቆራጭ የተባለው ደግሞ በስልጣን ላይ ያለው የገዢው ፓርቲ አምባገነናዊ ባለስልጣናትና ህግ አስፈፃሚ አካላት እንደ ፖሊስና መከላከያ ያሉትን የመንግሥት ባለሥልጣናትን ያመለከታል፡፡ ፍሬ የተባለው የሚገደለው፣ የሚታሰረው በደል የሚደርስበት የሚሰደደው ህዝባችን ለሃገሩ ሊሠራ የሚችለው ዘርፈ ብዙ የዕድገት ስራ የሚያሳየው ዜጋ ነው፡፡ ይህን ለሀገርና ለወገን ሊሰራ የሚችል ዕውቀት ገንዘብና ኃይል ያለውን ትውልድ ምን ሊያፈራ እንደሚችል ካለማገናዘብ እና ልኩን ካለማወቅ ደርሶ ጣቱን ቀሰረብኝ፣ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንቅስቃሴው በሰላማዊ ትግል ለምን ችግሬን አሳየኝ፣ ነቀፈኝ፣ ስህተቴን ገለፀብኝ ከሚል ደካማ አስተሳሰብ ከጨዋታ ውጪ ለማድረግ ዛፉ ፍሬ ሳያፈራ ይቆረጣል ማለት ነው፡፡



አንድ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን እገነባለሁ ከሚል መንግስት ለምን እነካለሁ፣ የኔን ብቻ ስሙ፤ እኔ ብቻ ነኝ እውነተኛና ሐሰት የሌለብኝ በማለት ሌላውን ህብረተሰብ እንዳይናገር አንገቱን እንዲደፋ ከዚያም ባለፈ እንዲታሰር ከዚያም ሲከፋ እንዲሰደድ፣ ከዚያ ሲብስ እንዲገደል፣ እያደረገ ዛፉ ፍሬ ሳያፈራ ዛፍ ቆራጭ እየላከ ልኩን ሳያውቅ ሳይገነዘብ ሊያጠፋ እየተጣጣረ ይገኛል፡፡ መፍትሄው የዛፉ ተረት ነው፤ ዛፎች ከዕለታት አንድ ቀን በመጥረቢያ ላይ አመፁና ስብሰባ አድረጉ "መጥረቢያ እኛን ለማጥፋት የተነሳበት ምክንያቱ ምንድን ነው? ከዚህ በኋላ ለሱ አንገዛም፤ ሊቆርጠን በሚመጣ ጊዜ ተሰባስበን ተባብረን ከምድረገፅ ማጥፋት አለብን" እያሉ ብዙ ብዙ ሃሳብ ሲለዋወጡ አንድ ሽማግሌ ዛፍ እንዲህ ሲል ተናገረ፡፡ "ለመሆኑ መጥረቢያ በራሱ አቅም ኃይልና ጉልበት እንደሌለው ሁላችንም እናውቃለን፡፡ እኛ እራሳችን ነን ለመጥረቢያው እጀታ እየሆን ራሳችንን ያስጠቃነው፡፡ በመጀመሪያ ከመሀከላችን ያሉትን ለእጀታነት የሚያገለግሉትን ቆልማሞች ወይንም ጠማማዎች እንወቃቸው፡፡ ሌሎቻችንም እጥፍ እያልን መቆልመም የለብንም" በማለት ተናገሩ፡፡ ሁሉም የሽማግሌውን ዛፍ ሃሳብ በጭብጨባና በዕልልታ ተቀበሉት፤ አፀደቁት፡፡

ዛሬ ስንቶቻችን ነን ለመጥረቢያው እጀታ የምንሆነው፤ ራሳችንን ልንመረምር ይገባል፡፡ በቀጣዩ ሃገራዊ ምርጫ ገዢው ፓርቲ ምንም ዓይነት እጀታ እንዳያገኝ በምርጫ ቅስቀሳ ህዝባችን ዕውነታውን፣ ያለበትን፣ መንግስት በህዝባችን ላይ እያደረሰ ያለውን ኢ-ሰብአዊ ድርግቶች በግልፅ በማሳወቅ ምንም ዓይነት የምርጫ ካርድ በምርጫ ኮሮጆ ውስጥ እንዳያገኝ በማድረግ እጀታዎች ልናሳጣው ይገባል፡፡ መጥረቢያው በራሱ አቅም፣ ኃይልና ጉልበት የሌለው መሆኑን ያልተረዱ ጥቂት ተቆልምመው የተፈጠሩ ቢኖሩም የነሱን ፕሮፓጋንዳ ወደ ጐን በመተው ሰላምና ዴሞክራሲ የሰፈነባት ሰብዓዊ መብት የተከበረባት፣ ፍትህ የነገሰባት ሉዓላዊት ሃገር ኢትዮጵያን ለመገንባት ዳር እስከ ዳር እንነሳ! እላለሁ፡፡

ለመጥረቢያው እጀታ አንሆንም!

# ከውጭ የሚላከው ሐዋላ የወጣቱን የትግል ስሜት በርዞታል

በለጠ ጉሹ ወ/ሚካኤል

ለዛሬ ርእሴ መግቢያ እንዲሆነኝ አንድ አዛውንት ጓደኛዬ ያጫወተኝን ልንገራችሁ፡፡ የጡረታ አበሉን ለመቀበል ኮመርሺያል ኖሚኒስ ቅርንጫፍ መ/ቤት ሄዶ፣ በሰልፍ ተራውን ይጠብቃል፡፡ ከፊቱ አንድ ወጣት ሴት ልጅ ቆማ እሷም ተራዋን ትጠብቃለች፡፡ ወጣቷ ደረሰኝ አውጥታ ለገንዘብ ከፋይዋ እንደሰጠቻት ካሼሪዋ አሥራ ሦስት ሺ ብር ቆጥራ ሰጠቻት፡፡ በዌስተርን ዩኒየን በኩል የተላከላት ሐዋላ ነበር፡፡ ጓደኛዬ በመንፈሳዊ ቅናት ሁኔታውን ሲከታተል ቆይቶ እሱም ተራው ደረሰና ለዳቦ እንኳን የማትበቃ የጡረታ አበሉን አሥር ሴኮንድ ባልሞላ ጊዜ ተቀብሎ ሄደ፡፡ የእሱ የጡረታ አበል ኢምንት ነበረች፡፡

ጓደኛዬ ከሰላሳ አምስት ዓመታት በላይ በመንግሥት ሠራተኛነት አገልግሏል፤ ግን ጡረታ የወጣው ቀደም ብሎ ስለሆነ የሚያገኛት የጡረታ አበል በኢህአዴ የመንግሥት ሌቦች ለአንድ ቀን ምሣ እንኳን አትበቃም! ይሁንና ቢቸግረውም ስለገንዘብ ብዙም አይጨነቅም፡፡ እሱን የሚያብከነክነው የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆን ነው! "እንዴት ዘጠና ሚሊዮን ሕዝብ ላይ የባህር በር ይዘጋል?" እያለ አሁንም እየተብሰከሰከ ነው፡፡ እሱ እያረጀ ነው፤ ወጣቶቹ ምንም ሳይሰሩ የብር ረብጣ የሚያፍሱ ከሆነ ማን ነው ለኢትዮጵያ የሚቆረቆረው?

ያቺ አሥራ ሦስት ሺ ብር አፍሳ የሄደችው ወጣት ሴት ስለሀገሯ ምን ይሆን የምታስበው? ለመሆኑ የኢትዮጵያ ካርታ በደንብ ታውቀዋለች? ኤርትራ የኢትዮጵያ ተፈጥሮአዊ እና ታሪካዊ አካል እንደሆነች ትገነዘብ ይሆን? ዘጠና ሚሊዮን ሕዝብን ወደብ አልባ አድርጎ አራት ሚሊዮን ለማይሞሉ ኤርትራውያን ከአንድ ሺ ኪሎ ሜትር በላይ የባህር ጠረፍ መስጠት ምን ዓይነት ሴራ ነው? ለአካባቢው ሰላምስ የሚበጅ ነውን?

ያቺ ወጣት ሴት እንደዚህ ማሰብ እብደት ሊመስላት ይችል ይሆናል፡፡ ምንም ሳትሰራ አሥራ ሦስት ሺ ብር ተሸክማ ሄደች፡፡ ገንዘቡን ከቤተሰቦቿ ጋር ተካፍላ ጥሩ ጥሩ ምግብ እየበላች እየጠጣችና እየለበሰች ትዝናናበታለች "ከቦይ ፍሬንዷ" ጋርም ዓለሟን ትቀጭበታለች፡፡ ትምህርት ቤት መሄድም አያስፈልጋትም፡፡ ከዚያ ይልቅ ጫት እየቃመች ሺሻ እያጨሰች ከፍቅር ጓደኛዋ ጋር መዝናናትን ትመርጣለች፡፡ ገንዘቡ ሲያልቅ ዌስተርን ዩኒየን እንደገና ብቅ ማለት ብቻ በቂ ነው!

እኔ በግሌ እንደተገነዘብኩት፣ የአዲስ አበባ ወጣቶች ስለሀገራቸው ብዙም እንዳይጨነቁና በሰላማዊ ትግሉም ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዳያደርጉ ከሚያዘናጓቸው መንስዔዎች አንደኛውና ምን አልባትም ዋናኛው ከውጭ ሀገር የሚላከው ሐዋላ ነው፡፡ እርግጥ የአቶ መለስ አምባገነን መንግሥትም የሚሰጣቸው ልዩ ልዩ መደለያዎች ለችግሩ አቢይ መንስኤ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በየወረዳ ጽ/ቤቱ ኢህአዴግ ወጣቶችን እየሰበሰበ ሰላሣና ሃምሳ ብር እንደሚያድል እናውቃለን፡፡ በመንግሥት መ/ቤቶች የሥራ ዕድል ለማግኘት የኢህአዴግ አባል መሆን የማይተለፍ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ በግል ዘርፉም ቢሆን የስራ ፈቃድ፣ መሬት፣ ብድር፣ ወዘተ ለማግኘት ቢያንስ የኢህአዴግ ደጋፊዎች ፎረም ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይ የአቶ መለስ አምባገነን መንግሥት ከሕዝብ በግብር እና ቀረጥ የሚሰበስበውን እና ከውጭ ዕርዳታና ብድር በየዓመቱ የሚያገኘውን ከ118 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ የሚጠቀምበት ቅጥረኛ አባላትንና ደጋፊዎችን ለማፍራት መሆኑ የተረጋገጠ ነው፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ከውጭ ሀገር የሚላከውም ሐዋላ በመንስዔነት የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቅርቡ ባወጣው ስታትስቲካዊ አሐዝ መሠረት በዓመት ወደ ኢትዮጵያ የሚላከው ሐዋላ 1.7 ቢሊዮን ዶላር ወይም ሰላሣ ቢሊዮን ብር ያህል ነው፡፡ ግን ይህ አሐዝ ከባንክ እና ከሐዋላ ማስተላለፊያ ድርጅቶች ውጪ የሚላከውን እንደማያካትት ይገመታል፡፡ በመሆኑም፣ በዓለም ባንክ ግምት መሠረት በየዓመቱ የሚላከው ጠቅላላ ሐዋላ ከ3.2 ቢሊዮን ዶላር አያንስም፡፡ ይህ ወደ ብር ሲቀየር በዓመት ወደ ስልሣ ቢሊዮን ብር (60 ቢሊዮን ብር) ገደማ ይሆናል፡፡ ይህ ገንዘብ ከ8-10 ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያውያንን እንደሚጠቅም ተገምቷል፡፡

እኔ እንደታዘብኩት የአዲስ አበባ ወጣቶች ገንዘብ ካገኙ፣ "ፖለቲካና ኮረንቲ በሩቁ ነው" ለማለት ጥሩ ሰበብ ይሆናቸዋል፡፡ በየጫት ቤቱ ጫታቸውን ከቃሙ በየመጠጥ ቤቱ ድራፍታቸውን ከተጐነጩ፣ አርሴን እና ማንቼን ካዩ፣ እንደ እንጉዳይ የሚፈሉትን ሀገረኛ ፊልሞች ካዩ፣ ፍቅርና ወሲብ ከሰሩ ወዘተ እስከ አፍንጫው ከታጠቀው ኢህአዴግ ጋረ ግብግብ ውስጥ ምን አስገባቸው? ከዚህም በላይ የአቶ መለስ አምባገነን መንግሥት ወጣቶቹ በነፃነት እንዳያስቡ አካዳሚያዊ ነጻነታቸውን (academic freedom) እንኳን ከልክሎአቸዋል፡፡ ነፃ የተማሪዎች ማህበራት ማቋቋም አይቻልም፡፡ ከዚህ ይልቅ ኢህአዴግ ተማሪዎች በብሔረሰብ ተቧድነው እንዲቧቀሱ ነው የሚፈልገው፤ ሆን ብሎ የትምህርት ጥራቱ እንዲያሽቆለቁል አድርጓታል፡፡ የዩኒቨርሲቲ ግቢዎችን ጨምሮ ትምህርት ቤቶች በኢህአዴግ የታጠቁ ነጭ ለባሾችና ካድሬዎች በስውር እየተጠበቁ ነው፡፡ ለነፃነታቸውና ለመብታቸው የሚከራከሩ ወጣቶች ይደበደባሉ፤ የሰቆቃ ተግባር ይፈፀምባቸዋል፤ ይታሰራሉ፤ ይገደላሉ፤ ለዚህ ማስረጃ እነ በቀለ ገርባን፣ አንዱዓለም አራጌን፣ ርዕዮት ዓለሙን፣ ናትናኤል መኮንን መጥቀሱ ብቻ በቂ ነው፡፡ የኢህአዴግ ታጣቂዎችና አልሞተኳሾች ሰኔ 1/1997 እና ጥቅምት 22/1998 በወጣቶች ላይ የፈፀሙት ዘግናኝ የነብስ ግድያ ወንጀል መቼውንም የሚረሳ አይደለም፡፡ ከዚያ በፊት የደርግ መንግሥት በወጣቶች ላይ ባካሄደው የቀይ ሽብር ዘመቻም እጅግ ዘግናኝ እንደነበር ሁላችንም የምናውቀው ነው፡፡

በሌላ በኩል ሚያዝያ 29 እና ሚያዝያ 30/1997 የተካሄዱት ሰላማዊ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ስለ ወጣቱ ትውልድ ብዙ ባሕርያትን ይጠቁማሉ፡፡ ሚያዝያ 29/1997 በአብዮት አደባባይ ወደ ስድስት መቶ ሺ የሚጠጋ ሕዝብ ለኢህአዴግ ድጋፉን አሳየ፡፡ በማግሥቱ ሚያዝያ 30 ከሦስት ሚሊዮን ያላነሰ ሕዝብ ለቅንጅት ያለውን ልባዊ ድጋፍ ይፋ አደረገ፡፡ በእነዚህ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ የተሳተፉት በአብዛኛው ወጣቶች ነበሩ፡፡ ሚያዝያ 29 ለኢህአዴግ ድጋፍ አሳይተው የነበሩት ወጣቶች "ትናንት ለቲሸርቴ ዛሬ ለሙብቴ" በማለት በሚያዝያ 30ውም ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ተሳትፈዋል፡፡ ነገሩ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ ወጣቱ ትውልድ ሁለት ልብ ነበር ማለት ነውን? ቅንጅት በምርጫ ቢያሸንፍ እንኳ የታጠቀው ኢህአዴግ ስለሆነ ሥልጣን አይለቅም የሚል ግምት በወጣቶቹ ዘንድ የነበረ ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል፣ ስብሰባዎቹ ከመንግሥት ሙሉ ፈቃድ የተሰጣቸው ስለነበር፣ ሰልፍ መውጣቱ አደጋ እንዳልነበረው ወጣቶቹ በሚገባ ያውቁ ነበር፡፡ በሁለቱ ስብሰባዎች የተገኘው የህዝብ ብዛት ሲታይ ወጣቶቹ ለቅንጅት ይበልጥ ድጋፍ እንደሰጡ ግልፅ ነው፡፡ ግን ከፊሎቹ ወጣቶች ለምን ሁልት ልብ ሆኑ? ለዚህ በርካታ ምክንያቶች መስጠት ይቻላል፡፡ አንደኛው ምክንያት በአጠቃላ የወጣቱ ትውልድ ንቃተህሊና ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው የብሔረሰብ ስሜት ሲሆን ሶስተኛው ምክንያት የወጣቱ ትውልድ በመንግሥት ላይ የኢኮኖሚ ጥገኛ ስለሆነ ነው፡፡ አራተኛው ምክንያት ደግሞ "የታጠቀ ያሸንፋል" የሚለው የቆየ ባሕላዊ አመለካከት ሲሆን በአምስተኛ ደረጃ ደግሞ "እሱ ያመጣውን እሱ ይመልሰዋል እንጂ የሰው ጥረት ዋጋ የለውም" የሚለው ኃይማኖታዊ አስተሳሰብ እንደሆነ ይገመታል፡፡

በቀጥታ ወደ ተነሳንበት ርእስ ስንመለስ ደግሞ ከውጭ የሚላከው ሐዋላ አንጻራዊ የኢኮኖሚ ነጻነት ቢሰጥም ውጤቱ በነፃነት ለማሰብ መቻል ሳይሆን ፖለቲካዊ ደንታ ቢስነት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሐዋላ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ከማሟላትም አልፎ፣ ለመዝናኛ የሚሆን ገንዘብ ስለሚያስገኝ ወጣቱ ትውልድ አደገኛ ከሆነው ከኢትዮጵያ ፖለቲካ እንዲርቅ ይገፋፋዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ፖለቲካዊ ደንታቢስነት ይስፋፋል፡፡ እንደሚታወቀው፣ ከሁሉም በላይ አንድን ሕዝብ ወደ ፖለቲካዊ አመፅ እንዲገባ የሚገፋፋው ረሀብ ነው፤ በአጠቃላይም የመሠረታዊ ፍላጐቶች አለመሟላት

ወደ ገፅ 19 ዞሯል

# ከውስጥ ግፊት ሳይኖር ከውጭ ቀባይ አይኖርም

ሙሉጌታ በሪሁን (የህግ ባለሙያ)

ጋዜጦችን ማንበብ እወዳለሁ፤ በቅርቡ አንድ ጋዜጣ ስመለከት ዐይኖቼ "አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ 5,500.000 (አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር) ተዘረፈ" ከሚለው ላይ አረፉ፡፡ እኔም የአክሲዮን ባለድርሻ እንደመሆኔ መጠን ደነገጥኩ፡፡ ይህ ባንክ ሲሰረቅ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑ ነው፡፡ ባለፈው "ተሠረቀ" መባሉን እንጂ ወንጀሉን የፈፀሙት ወይንም የሠረቁት ይያዙ አይያዙ፣ ወይንም ተይዘው ተቀጡ፣ ገንዘቡም ተመላሽ ሆኗል ወይንም በኪሣራ ተመዝግቧል ተብሎ ለባለ አክሲዮኖች አልተነገረንም፡፡ ሾላ በድፍን ሆኖ ነው የታለፈው፡፡ ዛሬ ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ መዘረፉ እጅግ የሚያሣዝንና የሚያሣፍር ነው፡፡ እኔ የዚህ ባንክ ባለአክሲዮን ለመሆን ሳስብ ብሔራዊ ባንክንና መንግሥትን አምኜና ዋስትና አድርጌ ነው፡፡ በተደጋጋሚ ሁኔታ በባንኩ ላይ እንዲህ ዓይነት ዘረፋ ሲካሄድ ግን የመንግስትን አቅም የሚፈታተን ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሥርዓቱን ብልሹነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ እንደ ተባለው የመንግሥት ሌቦች በየባንኮቹ ተሰግስገው ይሆን? በየጊዜው የባንክ ዘረፋና ሥርቆት መከሰቱ አሳሳቢ ነው፡፡

ሌላም መነሳት ያለበት ጉዳይ አለ፡፡ የባንክን የገንዘብ አያያዝና አቀማመጥ ሥርዓትን ጠንቅቀን ለምናውቅ አምስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር ተቆንጥሮ ተሠረቀ ለማለት ይከብዳል፡፡ የጥበቃ ሠራተኞች የሉም ወይ? ካዝናውስ በምን ኮድ ተከፈተ? ወይንም እንዴት ተሰበረ? የሚሉትን ጥያቄዎች ስናነሳ ተራ ሌቦችና ተራ ሥርቆት እንዳልሆነ እንረዳለን፡፡ ለዚህም ነው "ከውስጥ ግፊት ሳይኖር ከውጭ ተቀባይ አይኖርም" ለማለት የተገደድኩት፡፡ ከዚህ ላይ ሌላም ጥያቄ ማንሳት ይቻላል፡፡ ዜጎች ማንን አምነው ነው ገንዘባቸውን ባንክ ሊያስቀምጡ የሚችሉት? እንደ ጥንቱ ጠገራ ብር ቢሆን ኖሮ ሁሉም በየጓዳው እየቆፈረ በቀበረ ነበር፡፡ የወረቀት ብር (ኖት) ለዚህ የተመቸ አይደለም፡፡ ‹‹ብል›› ይበላዋል፡፡ ከብሉ የበለጠ ደግሞ ሌቦች እንክት አድርገው የሚበሉት ከሆነ እጅግ አሳሳቢ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ ካመሰራረቱ ጀምሮ ውዝግብ እንደነበረበት ጠንቅቄ አውቃለሁና፤ በመሆኑም ባንድ ጊዜ ካንበሳነት ወደ ቀበሮነት ደረጃ መውረዱ በጣም አሳዝኖኛል፡፡

ይህ ባንክ ሲመሠረት በባንኩ የቦርድ አባላትና በባለአክሲዮኖቹ መካከል ብዙ ንትርክና ጭቅጭቅ ነበር፡፡ ይህንኑ ጉዳይ ብሔራዊ ባንክ ይከታተል ስለነበር በራሱ አዳራሽ ነሐሴ 15 ቀን 2002 ዓ.ም አባላቱን ሰብስቦ ከዚያ በፊት የተደረገው ምርጫ ውድቅ ሆኖ አዲስ ምርጫ መካሄዱን እንደ አክሲዮን ባለድርሻነቴ አውቃለሁ፡፡ ይህንን ያነሳሁት ችግሩ ገና ከአመሠራረቱ ጀምሮ መሆኑን ስላማውቅ ነው፡፡ ምናልባትም በተደጋጋሚ ስርቆትና ዝርፊያ የተጋለጠውም ከዚህ አንፃር ሳይሆን ይቀራል?

በመሠረቱ "ታዳጊ ያላት በግ ላቷ ደጅ ያድራል" እንደ ሚባለው የጉርድ ሾላ የባንኩ ሥራ አስኪያጅ ስለሁኔታው ተጠይቀው ሲመልሱ "ፖሊስ ጉዳዩን ስለያዘው ለጊዜው ሐሳብ መስጠት አልችልም" ማለታቸው በራሱ አጠያያቂ ነው፡፡ መንግሥት የባለ አክሲዮኖችን መብት ለመጠበቅም ሆነ እንደ መንግሥትነቱ ሕግን ማስከበር አለበት፡፡ ባንክ እስከ መዝረፍ የዘለቁ ሌቦችን አሳዶ በመያዝ ተመጣጣኝ ቅጣት ሊያሰጣቸው ይገባል፡፡ አለበለዚያ ዛሬ ተደራጅተው ባንክ የዘረፉ ነገ ቤተመንግሥትን አይደፍሩም ማለት የዋህነት ነው፡፡ ለማንኛውም አቀባይ ከሌላ ተቀባይ አይኖርምና ይታሰብበት እላለሁ፡፡

# ከመንግስት መግለጫ በኋላም የሙስሊም ተቃውሞ ቀጥሏል

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄያቸውን በአደባባይ ማቅረብ መቀጠላቸው ታወቀ፡፡ ሚያዝያ 27/08/04 ዓ.ም መርካቶ አኑዋር መስጊድ ለሶላት የወጣው ብዙ ሺህ ህዝበ ሙስሊም ከፍተኛ ተቃውሞ ማሰማቱን በቦታው የተገኘው ሪፖርተራችን ለመታዘብ ችሏል፡፡ በለቱ የሶላት ሥነ ሥርዓቱ ከ6፡30 ጀምሮ የቀጠለ ሲሆን ልክ 6፡45 ሲሆን በአስገራሚ አንድነት ተቃውሞ መጀመራቸው ታውቋል፡፡ በለቱ በአካባቢው የነበሩ የፖሊስ አባላት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ቢሆንም ጭንቀት ይነበብባቸው እንደነበር ሪፖርተራችን ተመልክቷል፡፡ ከጣና ገበያ እስከ ይርጋ ሀይሌ፣ ከየመን ኮሙኒቲ ት/ቤት እስከ ነጃሺ ሬስቶራንት በፌደራል እና የከተማ መስተዳድሩ ፖሊሶች ጥብቅ ቁጥጥር ስር እንደነበር ተመልክቷል፡፡ በተመሳሳይ አወሊያ መስጊድም ተመሳሳይ ተቃውሞ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል አንድ ወጣት "አሻዕብ ዩሪድ አስቃጣል መጅሊስ" የሚል ከጀርባው ከፊት ለፊቱ ደግሞ "ያልመረጥኳቸው የመጅሊስ አመራሮች አይወክሉኝም" የሚል ፅሁፍ ያለበት ነጭ ቲሸርት ለብሶ ሲንቀሳቀስ አትክልት ተራ አካባቢ በፖሊሶች ተይዞ የተወሰደ ሲሆን ጣይቱ ሆቴል ፊት ለፊት ወዳለው ፖሊስ ጣቢያ መወሰዱን የፅሁፉ ሪፖርተር ተመልክቷል፡፡

በተያያዘ ዜና በደሴ ከተማ በተመሳሳይ ለት ለሶላት የወጣዉ ህዝበ ሙስሊም ተቃዉሞ ማሰማቱን ምንጮቻችን ተቁመዋል፡፡ በለቱ በተለይ ሁርቃን መስጊድ የነበረዉ ተቀዉሞ ከፍተኛ መሆኑ ተሰምቷል፡፡

# በፓርላማ ብቸኛው የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ አሜሪካ ካሉ ደጋፊዎቻቸው ጋር ተወያዩ

በፓርላማ ብቸኛው  የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ የሆኑትና የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ (አንድነት) ፓርቲ ምክትል ፕሬዚደንት የሆኑት የተከበሩ አቶ ገርማ ሰይፉ በአሜሪካ ከፓርቲው ደጋፊዎች ጋር ተወያዩ፡፡

አቶ ግርማ ባለፈው ሳምንት ለሥራ ጉዳይ ወደ ብራዚል ተጉዘው የነበረ ሲሆን የብራዚል ስራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ አሜሪካን ሀገር በመሄድ ዋሽንግተን ዲሲ እና ቦስተን ከተማ ካሉት የአንድነት ፓርቲ የድጋፍ ማህበር አመራሮች ጋር በአካል መወያየታቸው ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ከሌሎቹ የድጋፍ ማህበራት ጋር በቴሌ ኮንፈረንስ መወያየታቸውም እንዲሁ ፡፡ በውይይታቸውም ላይ ተጨባጭና ወቅታዊ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታን አስመልክቶ ከተነጋገሩ በኋላ በፓርቲያቸው ዙሪያ እና ስለ ድጋፍ ማህበራቱ ግንኙነት እንዴት መሆን እንዳለበትም አንስተው መወያየታቸውን የደረሰን መረጃ አመልክቷል፡፡

በአሁኑ ወቅት አቶ ግርማ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱ ሲሆን የአንድነት ፓርቲ ፕሬዚዳንት የሆኑት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ቀድሞ ወደተማሩበት ዩኒቨርሲቲ ለሥራ ተጋብዘው ለተወሰነ ጊዜ ጀርመን ስለሚቆዩ አቶ ግርማ ሰይፉም በመወከል የፕሬዚዳንቱንም ሥራ ደርበው እየሰሩ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

# የብርሃንና ሠላም . . .

ከገፅ 1 የዞረ

ነጥቦ ተነስተው ውይይት ተደርጎበታል" ብለዋል፡፡

የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን ወክለው በስብሰባው ላይ የተገኙት የአንድነት ፓርቲ ዋና ፀሐፊ አቶ አስራት ጣሴ በውይይቱ ዙሪያ ላቀረብንላቸው ጥያቄ በሰጡን መልስ እንዳሉት "ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ባለ አራት ገጽ እና ባለ 11 አንቀጽ የውል ሰነድ ልኮልን ተመልክተነዋል፡፡ በውሉ አንቀጽ 10 ተራ ቁጥር 1 ና 2 እንደተገለፀው አታሚው በአሳታሚው እንዲታተም የቀረበለት የፅሁፍ ስክሪፕት ሕግን የሚተላለፍ ስለመሆኑ ለማመን በቂ ምክንያት ካለው አላትምም የማለት መብት አለው፡፡ አታሚው አሳታሚው የሕግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል የሕትመት ይዘት የማውጣት ዝንባሌ ያለው መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ካለው በማናቸውም ጊዜ ውሉን ለማቋረጥ ወይም ለመሰረዝ ይችላል፡፡" ይህንን አንቀጽ ስንመለከት ህገ መንግስትን የሚሸር የዜጐችን ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት የሚገፍ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን ውል መፈረም ህገ- መንግስታዊ መብትን አሳልፎ መስጠት ነው፡፡ የህገ መንግስት ድንጋጌም የመጣስ ወንጀል ነው፡፡ ውሉ በአሰሪና ሰራተኛ ወይም በአገልጋይና በተገልጋይ መካከል የሚከናወን ሳይሆን ከዚያ ባለፈ የሚታይ ሆኖ አግኝተነዋል" በማለት ያብራራሉ፡፡

በመቀጠልም አቶ አስራት ሲናገሩ "የፓርቲው አመራር በጉዳዩ ላይ ከተነጋገረ በኋላ ተወካዮች ማተሚያ ቤቱን እንዲያነጋግሩ መመሪያ ሰጥቷል፡፡ ከፓርቲው የተወከልን እኔና ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ጉዳዩ ይመለከታቸዋል የተባሉትን የማተሚያ ቤቱን የሥራ ኃላፊዎች ባለፈው ሐሙስ አነጋግረናል፡፡ ኃላፊዎቹ የሰጡን መልስ አጥጋቢ ሆኖ ባለማግኘታችን የድርጅቱን ዋና ስራ አስኪያጅ ለማነጋገር ቀጠሮ እንዲያዝልን ጠየቅን፡፡ ሌሎች አሳታሚዎችም ጥያቄ ስለአላቸው ሥራ አስኪያጁ በጋራ ያነጋግሯቸዋል፤ ተባልንና በትላንትናው ዕለት በጋራ መገናኘት ችለናል፡፡ በማተሚያ ቤቱ በኩል የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅና የሥራ ኃላፊዎች የተገኙ ሲሆን ከአሳታሚዎች የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ፣ የሪፖርተር ጋዜጣ የፎርቹን ጋዜጣ፣ ካፒታል ጋዜጣ፣ የአዲስ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ወዘተ ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡ ውሉን ከፕሬስ ነፃነት፣ ከህገመንግስት ድንጋጌ፣ ከዜጐች ሐሳብቸውን በነፃነት ከመግለጽ አኳያ፣ ከሰብአዊ መብት ማስከበር፣ ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከመገንባት አቅጣጫ የውሉን አደገኝነት አብራርተን ነግረናቸዋል፡፡ የሥራ ኃላፊዎቹም በጥሞና አድምጠውናል፡፡ የማተሚያ ቤቱ አላፊዎች በበኩላቸው አሳታሚዎች ከሚፈጥሩት ስህተት አታሚው ተጠያቂ እንዳይሆኑ ከሥጋት የተፈጠረ መሆኑን ገልጸውልናል፡፡ በተለይ ረጂም ዓመት ያስተሙ አሳታሚዎች እስከ ዛሬ ድረስ ብርሃንና ሰላም ከኛ ጋር ተኮሶ አያውቅም፡፡ ዛሬ ምን አመጣው በማለት ጠይቀዋል፡፡ በመጨረሻም ብርሃንና ሠላም ረጂም ዕድሜና ታሪክ፣ መልካም ዝና ያለው ሆኖ ዝናውን ጠብቆ ለመቆየት ሊያስብበት እንደሚገባ ገልፀን አሳታሚዎች የአታሚውን ተጠያቂነት በኃላፊነት እንደምንወሰድ እኛም የውሉን ሐሳብ ልናቀርብ ስንስማማ ማተሚያ ቤቱ ደግሞ ከእኛ ጋር ያደረገውን ውይይት ግምት ውስጥ በማስገባት ተመልክተውት በድጋሚ ተገናኝቶ ለመወያየት ግንቦት 10 ቀን 2004 ዓ.ም ቀጠሮ ይዘናል፡፡" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የህገ መንግስቱን አንቀጽ 29 ይጥሳል የተባለውና ቅድመ ምርመራ ወይም ሳንሱር ነው የተባለለት የብርሃንና ሠላም ድርጅት ውል ከፍተኛ ተቃውሞ እያቀረበበት ሲሆን ከውሉ ጀርባ ያለው ማነው የሚለው ጉዳይ የሰሞኑ መነጋገሪያ ሆኖ መሰንበቱ ይታወቃል፡፡

# ነፍሰ-ጡሯ ለመገላገል ወደ ሆስፒቷል ሲሄዱ በዘራፊዎች ተደብድበው ህይወታቸው አለፈ

ልዩ ቦታው ላፊቶ ኮንዶሚኒየም አካባቢ ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ ምስራቅ አክመል ሚያዚያ 17 ቀን 2004 ዓ.ም ከሌሊቱ 7፡30 ሰዓት ላይ ምጥ ይዟቸው ከባለቤታቸው ጋር ሲሄዱ ጎፋ ገብርኤል አደባባይ አካባቢ በዘራፊዎች ተደብድበው ህይወታቸው ማለፉ ተገለፀ፡፡ ወ/ሮ ምስራቅ እና ባለቤታቸው አቶ ታሪኩ ጉዲሳ ላዳ ታክሲ ተኮናትረው ሜክሲኮ በሚገኘው ላንድማርክ ሆስፒቷል እየሄዱ ሳለ ባለታክሲው በድንገት ጎፋ ገብርኤል አደባባይ አካባቢ በድንገት እዚህ ውረዱ ብሎ ካወረዳቸው በኋላ ሁለት ያልታወቁ ሰዎች ወዲያውኑ መጥተው በእጃቸው ያለውን ንብረት መዝረፋቸው ተጠቁሟል፡፡

በወቅቱም ዘራፊዎቹ ያላችሁን ሁሉ አምጡ እያሉ ሲደበድቡ ነፈሰጡሯ ለመጮህ ሲሞክሩ በኃይል ከጀርባቸው እንደገፈተሯቸውና ወደፊት በሆዳቸው  በመውደቃቸው አንድ ድምጽ ካሰሙ በኋላ ፀጥ እንዳሉ ባለቤታቸው አቶ ታሪኩ ተናግረዋል፡፡

በመጨረሻም እኔ ነቅቼ እየጮህኩ የድረሱልን የእርዳታ ጥሪ ሳሰማ በአካባቢው ያሉ መኪና ጠባቂዎች ደርሰው ታክሲ ፈልገው እንዳመጡላቸውና ወዲያው ላንድማርክ ሆስፒታል ሲሄዱ ባለቤታቸው ህይወታቸው አልፎ እንደነበር ከዶክተሮቹ መስማታቸውን አቶ ታሪኩ ይናገራሉ፡፡ በስፍራው ጎፋ አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ ቢኖርም ፖሊሶቹ ግን መኪና ላይ ተኝተው መገኘታቸውን ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡ ድርጊቱን ፈጽመዋል የተባሉ ተጠርጣሪዎችም በቁጥጥር ስር ውለው ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ ክፍል እንደሚገኙ ተጠቁሟል፡፡በፓርላማ ብቸኛው የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ አሜሪካ ካሉ ደጋፊዎቻቸው ጋር ተወያዩ

በፓርላማ ብቸኛው  የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ የሆኑትና የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ (አንድነት) ፓርቲ ምክትል ፕሬዚደንት የሆኑት የተከበሩ አቶ ገርማ ሰይፉ በአሜሪካ ከፓርቲው ደጋፊዎች ጋር ተወያዩ፡፡

አቶ ግርማ ባለፈው ሳምንት ለሥራ ጉዳይ ወደ ብራዚል ተጉዘው የነበረ ሲሆን የብራዚል ስራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ አሜሪካን ሀገር በመሄድ ዋሽንግተን ዲሲ እና ቦስተን ከተማ ካሉት የአንድነት ፓርቲ የድጋፍ ማህበር አመራሮች ጋር በአካል መወያየታቸው ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ከሌሎቹ የድጋፍ ማህበራት ጋር በቴሌ ኮንፈረንስ መወያየታቸውም እንዲሁ ፡፡ በውይይታቸውም ላይ ተጨባጭና ወቅታዊ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታን አስመልክቶ ከተነጋገሩ በኋላ በፓርቲያቸው ዙሪያ እና ስለ ድጋፍ ማህበራቱ ግንኙነት እንዴት መሆን እንዳለበትም አንስተው መወያየታቸውን የደረሰን መረጃ አመልክቷል፡፡

በአሁኑ ወቅት አቶ ግርማ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱ ሲሆን የአንድነት ፓርቲ ፕሬዚዳንት የሆኑት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ቀድሞ ወደተማሩበት ዩኒቨርሲቲ ለሥራ ተጋብዘው ለተወሰነ ጊዜ ጀርመን ስለሚቆዩ አቶ ግርማ ሰይፉም በመወከል የፕሬዚዳንቱንም ሥራ ደርበው እየሰሩ መሆኑንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

# መኢአድ ማህተሙን እንደሚጠቀም አስታወቀ

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ "የፓርቲውን ማህተም ከመጠቀም የሚከለክለኝ የህግ አግባብ የለም" ሲል ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቀ፡፡ ፓርቲው ይህንን ያስታወቀው ዝግጅት ክፍላችን ላቀረበላቸው ጥያቄ ነው፡፡ "ምርጫ ቦርድ ከሚያዚያ 30 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በፓርቲው ማህተም እንዳትገለገሉ፣ በመካከላችሁ የተፈጠረውን አለመግባባት ጠቅላላ ጉባኤ ጠርታችሁ እንድታስወስኑ ትዕዛዝ መስጠቱ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ከነገ ጀምሮ ማህተሙን አትጠቀሙም? ጠቅላላ ጉባኤ ለመጥራትስ አቅዳችኋል?" በማለት ላቀረብንላቸው ጥያቄ በሰጡን መልስ ነው፡፡

የፓርቲው ዋና ፀሐፊ አቶ ተስፋዬ ታሪኩ በሰጡን መልስ "እኛ እየሰራን ያለነው በፓርቲው ደንብ ነው፡፡ ጠቅላላ ጉባኤ የምንጠራውም በማንም ትዕዛዝ ወይም አስገዳጅነት ሳይሆን በህገ ደንባችን መሠረት ነው፡፡ በፓርቲው ደንብ መሠረትጠቅላላ ጉባኤ የሚጠራው በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ነው፡፡ ፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤው ያደረገው በታህሳስ 17-18/2003 ዓ.ም ነው፡፡ ሁለት ዓመት የሚሞላው በታህሣሥ 2005 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ መካከል አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እንድንጠራ የሚያስገድደን የህግ አግባብ የለም፡፡ በመካከላችን የተፈጠረው አለመግባባት በፓርቲው ደንብ መሠረት የመጨረሻው ውሳኔ ተሰጥቶታል፡፡ በፓርቲያችን ደንብ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 8 በተራ ቁጥር 2 በሚያዘው መሠረት በፓርቲው ውስጥ የተፈጠረ የዲስፕሊን ግድፈት በህግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ይታያል፡፡ በህግና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ታይቶ በቀረበ ጉዳይ ላይ የፓርቲ ፕሬዝዳንትና ሥራ አስፈጻሚው ጊዜያዊ እግድ ያደርጋሉ ይላል፡፡ ፕሬዝዳንቱ ወይም ሥራ አስፈጻሚው ጊዛዊ እግድ በተደረገበት ጉዳይ ላይ በመጀመሪያ የሚሰበሰበው ጠቅላላ ጉባኤው ወይም ማዕከላዊ ም/ቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል ይላል፡፡

በዚሁ መሠረት በፓርቲው ውስጥ የድስፐሊን ግድፈት የፈፀሙ ግለሰቦች በደንባችን መሠረት ሲሰጡበት ቆይቶ ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰበሰበው የፓርቲ ማዕከላዊ ም/ቤት የመጨረሻውን ውሳኔ ሰጥቶት ጉዳዩ ተዘግቷል፡፡ በዚህ መካከል ምርጫ ቦርድ ጣልቃ ገብቶ ከደንባችን ወጪ እንድንሰራ የሚያስገድድበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ለዚሁም በደብዳቤ ገልፀንላቸዋል፡፡ ማህተሙንም እንዳንጠቀም የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ የሚያስችላቸው የህግ አግባብ የለም፡፡ ስለዚህ ማህተሙንም እንጠቀማለን፡፡ ጠቅላላ ጉባኤውንም አንጠራም" ሲሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ዜናውን ሚዛናዊ ለማድረግ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡን ወደ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ብናመራም የህዝብ ግንኙነቷን ማግኘት አልቻልንም፡፡ ረዳታቸው ለጊዜው ስብሰባ ላይ ስለሆኑ ከሰዓት ደውሉላቸው የሚል መልስ አገኘን፡፡ ከሰዓት በኋላ በተደጋጋሚ በተንቀሳቃሽ ስልካቸው ላይ ብንደውልም ሊያነሱልን ባለመቻላቸው ጥረታችን ሊሳካልን አልቻለም፡፡


BIG CHAIR CAFÉ & GRILL
2122 Martin Luther King Ave. SE
Washington, DC
202-525-4287
High-Speed
Internet
Logon Here
OPEN for breakfast,
lunch & dinner
Mon-Sat 7am-9pm

# የኢትዮጵያ መምህራን . . .

ከገፅ 6 የዞረ

የመማር ማስተማሩን ሂደት በተግባር ላይ ለማዋልና የትምህርትን ግብ (ተማሪው ህብረተሰቡ የሚፈልገው የባህሪ ለውጥ መቀዳጀቱን) በየደረጃው ለማሳካት ግን ተደጋግሞ እንደሚነገረው በአልፋና ኦሜጋ ሊገለጽ የሚችል ወሳኙ ሰው ያው መምህሩ ነው::

እዚህ ላይ አንድ ቁምነገር አጠንክሬ ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ:: የትምህርት ግብ ትርጉም ተማሪው ህብረተሰቡ የሚፈልገውን የባህሪይ ለውጥ ማቀዳጀት ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በምሳሌ ላስረዳ:: አንድ ልጅ ት/ቤት ከመግባቱ በፊት እያያቸው፤ እየዳሰሳቸውና እየሰማቸው ጥቅም ጉዳታቸውን የማያውቃቸው ብዙ ነገሮች በአካባቢው ይኖራሉ:: በትምህርት እየተገራ፤ አእምሮው እየበሰለ ሲመጣ ግን ከነዚህ ውስጥ ለምሳሌ ያለበትን ህብረተሰብ ጠቃሚ እሴቶች የማድነቅ ስሜት ማዳበር ሲጀምር፤ መሀይም የነበረው ፊደል ለይቶ ማንበብና መጻፍ ሲችል፤ መሬት ዝርግ ትመስለው የነበረ ባሳማኝ ምክንያቶች ክብ መሆኗን ሲረዳና ሲቀበል፤ በዶማ ከመቆፈር በበሬ ማረስ፤ ከበሬ ይልቅ በትራክተር (መኪና) ማረስ የተሻለ መሆኑን ሲአውቅ፤ እነዚህ ማምረቻ መሣሪያዎች ከምንና እንዴት እንደሚሠሩ፤ እነዚህንና የመሳሰሉትን ተጨባጭ እውነታዎችን አውቆና አምኖበት የሥራውን ክህሎት አዳብሮ በመጠቀም ህይወቱን ለመለወጥ ዝግጁ ሲሆን ወይም ሲችል፤ በሌላ አገላለጽ አንድ ተማሪ የትክክለኛ አስተሳሰብ፤ የፈጠራ ችሎታውንና የሙያ ክህሎቱን በትምህርት አንጾ በየደረጃው እንደዝንባሌው ለህብረተሰቡ፤ ለሀገሩ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለመሆን ሲበቃ ይህ ወጣት (ሰው) የባህሪይ ለውጥ ተቀዳጀ ማለት ነው::

እነዚህ ሁሉ ተማሪው የተቀዳጃቸው የባህሪይ ለውጦች በጤናማ ህብረተሰብ ውስጥ የሚፈለጉናቸው:: እነዚህ ሁሉ የሚገኙት በት/ቤት ብቻ ነው ባይባልም በጣም በተጣራና በቀልጣፋ አሠራር ከሁሉም በላይ ከእለት ወደ እለት የመሻሻሉ እድገት አስተማማኝና ቀጣይነት የሚኖረው በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ሲአልፍ ነው:: ለዚህ ታላቅ ሂደት አቅጣጫ አመልካች ኮምፓስ፤ የተወላገደውን እንደ ማገርና ቋሚ ጊድጊዳ አርቆና ደግፎ የሚአቃና፤ ለጨለመበት ብርሀን ፈንጥቆ፤ ለደከመው ነዳጅ ሆኖ ህይወት የሚዘራበት ያ ሰው መምህሩ ነው:: ይህን ወደር የሌለው አገልግሎት የሚሠጠው ደግሞ ለማንም አይደለም:: የአብራካችን ክፋይ ለሆኑ ልጆቻችን ነው:: ይሄን ታላቅ ሰው እያስራቡ፤ ሲታረዝ ዝም እያሉት፤ ለሙያው ክብርና ትኩረት ነፍገ ከቶም የዜግነት መብቱ እንዲከበርለት ህግና ሥርአት ጠብቆ ጥያቄ ባቀረበ ቁጥር የሀገሪቱን ህግ በመተላለፍ እያስፈራሩ፤ እያንገላቱና ከስራው እስከማገድ እየተኬደ ምን የሚሉት ለምንስ የሚፈይድ የትምህርት ፖሊሲ መንደፍ፤ ሥርአተ ትምህርት ብሎ መቅረጽ፤ መጻህፍት ማተም ማሰራጨት፤ መማሪያ ክፍሎች መገንባት እየተባለ የሰው ኃይል፤ ንብረትና ጊዜ በከንቱ ይባክናል? ልጆቻችንስ ት/ቤት ምን ሊፈጥሩ ይመላለሳሉ? መምህሩን ያላሳተፈ፤ የመምህሩን ክብርና ጥቅም እግምት ውስጥ ያላስገባ የትምህርት ጉዳይ ብሎ ሆያ ሆዬ ለማንም ለምንም የማይበጅ የታይታ ደፋ ቀና መሆኑን የማይረዳ አካል ካለ እራሱን እያታለለ ቀን መግፋትን እንደ ትልቅ ጥበብ የሚቆጥር ከንቱ ብልጣብልጥ ፍጡር ነው ቢባል መስመር ያለፈ ምሬት አይሆንም::

የቀድሞውም ሆነ የቅርብ ጊዜ ታሪኩ እንዲሚያረጋግጠው፤ የኢትዮጵያ መምህራንን የመብት ጥያቄና የትምህርቱ ሥራ ሲፈለግ እንደላስቲክ እየለጠጡ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ማዋል ሳይፈለግ ደግሞ በብልጣብልጦች ሸንገላ አድበስብሶ ወይም በጡንቻ አፍኖ ለጊዜው ማዘግየት ተችሏል:: እስከወዲያኛው ማስቀም ግን በፍጹም የሚቻል ተራ ጉዳይ አልሆነም:: ምክንያቱም ጥያቄአቸው ለነገ የማይባል የህልውና ጥያቄ ነው:: የስብእና መከበር ጥያቄ ነው:: በድካማቸው ያገኙትን የትምህርት ደረጃና ለሀገራቸው የሚአበረክቱትን አገልግሎት የሚመጥን፤ ከሌሎች በትምህርት ደረጃ አቻ ሙያተኞች ጋር በማህበራዊ ከበሬታና በቁሳዊ ጠቀሜታ ከሞላ ጎደል የሚአስተካክላቸውና የሐገሪቱን አቅም እግምት ውስጥ አስገብቶ ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን የተከተለ አሠራር እንዲኖር ይፈልጋሉ:: ለዚህ የጋራ ጥቅም መከበር ሲንቀሳቀሱ አንዱን ቀስቃሽ ሌላውን ተቀስቃሽ አስመስሎ መምህራን መከፋፈል፤ በገንዘብ መቅጣትና ከሥራ ማገድ ጭካኔ የበዛበት ኢሰብአዊ ድርጊት ወይም በመደናገጥ የተፈጸመ ስህተት መሆን አለበት:: ካልሆነ በሀገራችን ህግ መሠረት መጠየቅ መብት ነው:: መቃወም መብት ነው፤ ሥራ ማቆም መብት ነው:: እምኑ ላይ ነው የነዚህ ሰዎች በደል? ሌላው ቀርቶ በፖለቲካ ፓርቲ ዲሲፕሊን ተለጉሞ የመናገር መብቱን የተነጠቀ መምህርም ቢሆን ፊት ለፊት መናገር ቢፈራም የደሞዝ ጭማሪውን ጥያቄ አይደግፍም ማለት አይደለም:: ሁሉም መምህራን እኩል የሚጋሩት፤ ህግና ሥርአት ጠብቆ አግባብ ላለው የመንግሥት አካል በቃልና በጽሁፍ በኦፊሴል የቀረበና የሚቀርብ ህጋዊ የድካም ዋጋ ጥያቄ ነው:: ይሄን ጥያቄ ተቀራርቦ በውይይት መፍታት እንጂ ቢአድበሰብሱት፤ በቀጠሮ ቢአንከባልሉት፤ እውነቱን ሆድ እያወቀው ያልሆነ ስም በመስጠት ፍጥጫ ውስጥ መግባት በውስጥም በውጪም ትዝብት ላይ የሚጥል ነው:: ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳ ቦንብ የመቅበር ያክል ነው:: ተመሳሳይ ታሪክ እየተደገመ ስለሆነ የግራ ቀኙ ትንሽ ቆም ብሎ እንዲአስብ ያበረታታው ይሆናልና በዚሁ በህወሀት/ኢህአዲግ የመጀመሪያ ዘመን የሆነውን አንድ ምሳሌ ላስታውስ::

ስለመምህራን 20ዎቹ ጥያቄዎች ማስታወሻ

በሐምሌ ወር 1984 ለመንግሥት በጽሁፍ ቀርበው የነበሩት የኢትዮጵያ መምህራን 20 ጥያቄዎች ሲዘጋጁ በኢመማ የአባላት ጉዳይ ተጠሪነቴ ነበርኩበት:: ከሀገራችን ህግ አኳያና በወቅቱ የሽግግር መንግሥቱ ቻርተር ከሚባለው ጋር ስለመጣጣሙ የህግ ሙያተኞች እንዲአዩት አርገናል:: በተባበሩት የዓለም መንግሥታት የየመስኩ ኤክስፐርት ኤጀንሲዎች (ILO, UNESCO, etc )፤ የዓለም መምህራን መተዳደሪያ ቻርትር፤ የዓለም መምህራን ማህበር፤ የሌሎች ሀገሮች አቻ የሙያ ማህበራትና የሠራተኛ ማህበራት የትግል ተሞክሮ ታሳቢ በማድረግ ከአቀራረብና ከአገላለጽ ጀምሮ ከመሠረታዊ መርሆዎቻቸው ጋር ምንም ዓይነት ተቃርኖ እንዳይኖራቸዉ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርገናል:: መጀመሪያ በማህበሩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት ከመላው ሀገሪቱ (ከኤርትራና ከአሠብ እራስ ገዝ በስተቀር - መለያየታችን በወቅቱ ይፋ ስላልነበረ ነው ስፍራዎቹን የጠቀስኳቸው) ጥያቄዎችን በጽሁፍ ሰበሰብን:: በሚገርም ፍጥነት በመቶዎች የሚቆጠሩ ደረሱን:: ከደረሱን ጥያቄዎች መሀከል ቀለል ያሉትንና አብዛኛውን አባላት ሊመለከቱ አይችሉም ያልናቸውን ነቅሰን አወጣን:: ከባድና የጋራ ችግሮች ናቸው ያልናቸውን አወራርሰንና ጨምቀን አንድ ወጥ እረቂቅ አዘጋጀን:: ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍል በብዙዎቹ መምህራን የተነሱት ጥያቄዎች:-

የመምህሩን የትምህርት ደረጃና የሚሰጠውን አገልግሎት የሚመጥን፤ የወቅቱን የኑሮ ውድነት ያለጭንቀት መቋቋም የሚያስችል የደሞዝ ጭማሬ እንዲደረግ፤ የትምህርት ፖሊሲና የሥርአተ ትምህርት የተጠቃሚውን ህብረተሰብ ባህልና ፍላጎት ተከትሎ ከጊዜው ጋር የሚሄድ መሻሻል እንዲደረግበት፤ በዝግጅቱ ሁሉም የትምህርት ባለድርሻ እንዲሳተፍ፤ መምህራን በሥራቸው እንዲተጉና የማስተማር ሙያ ማህበራዊ ከበሬታ ጎልቶ እንዲታይ የሚአስችል የመምህራንን ክብርና ቁሳዊ ጠቀሜታ እግምት ውስጥ የሚያስገባ የመምህራን የእድገት መዋቅር እንዲዘረጋ፤ በደርግ ታግዶ የነበረው የደሞዝ ጭማሪ እርከን ጣሪያ እንዲነሳ፤ እየተሠራበት ያለውን የትምህርት ሥርአት ደካማና ጠንካራ ጎን ገምግሞ ድክመቱን አርሞና ጠንካራ ጎኑን በማጎልበት በቀጣይነት የወደፊቱን አቅጣጫ የሚተልም ሁሉንም የትምህርት ባለድርሻ ተወካዮችን የሚአሳትፍ ሀገር አቀፍ የትምህርት ሥራ ሲመፖዚየም እንዲዘጋጅ፤ብቃትና ግልጽነት ያለው አስተዳደር፤ ከፍተኛ የትምህርት እድል፤ ምቹ የስራ ቦታ፤ የቆላ አበል፤ ዝውውር፤ ለውስጥ እድገት ውድድር ለሁሉም እኩል እድል እንዲሰጥ፤ከሥራ ባህሪያቸው አኳያ መምህራን ለተላላፊ በሽታዎች የተጋለጡ ስለሆነ የነጻ ህክምና መብት እንዲኖራቸው፤ ደሞዝ ወቅቱን ጠብቆ እንዲከፈል፤ አስተማሪ ለቤተሰቡ ምንም አይነት የትምህርት ነክ ክፍያ እንዳይከፍል፤ በሙያ በነጻ የመደራጀት መብት መከበር፤ የትምህርት ሥራንና የመምህራን ጉዳይ በሚመለከት ማንኛውም ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የመምህራን ተወካይ ሳይኖር

እንዳይፈጸም፤ የውክልናው ድምጽ (የመምህራን ተወካዮች ቁጠር) እንዲጨምር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ነበሩ::

እነዚህ የተመረጡት ጥያቄዎች የአብዛኛውን አባል ፍላጎት ማንጸባረቃቸውን ለመለየትና እንደ ክብደታቸው ቅደም ተከተል በጽሁፍ ለማሰፈር ከተጠቀምንባቸው መመዘኛዎች ዋንኞቹ 1ኛ አንድ ጥያቄ ስንት ጊዜ ተደጋግሞ እንደተጠየቀ ለያንዳንዱ ታሊ ሠራን:: 2ኛ እያንዳንዱን ጥያቄ የላከው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ምን ያክል አባላት እንዳሉት አመሳከርን:: በዚህ መልክ በጥንቃቄ ተነቅሰውና ታሽተው የተዘጋጁት 20ዎቹ ጥያቄዎች ከሰኔ 11-13 ቀን 1984 ዓ.ም በማህበሩ የስብሰባ አዳራሽ አዲስ አበባ በተካሄደው የማህበሩ ማዕከላዊ ም/ቤት ስብሰባ ቀርበው በሙሉ ድምጽ ጸደቁ:: የኤዲቲንግ ሥራ፤ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል የማቅረብና አፈጻጸሙን የመከታተል ኃላፊነት በዋናው ጽ/ቤት ላለው ለማዕከላዊ ጊዛዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተሰጠ::

በዚሁ መሠረት 20ዎቹን ጥያቄዎች የያዘው ደብዳቤ ተዘጋጅቶ በሐምሌ ወር 1984 ዓ.ም በት/ሚ የስብሰባ አዳራሽ አዲስ አበባ በተካሄደው የትምህርት አመራርና አስተዳደር 25ኛው ጠቅላላ ጉባኤ (በጊዜው የሀገሪቱ የትምህርት ሥራ ከፍተኛው የበላይ አካል የነበረው) ላይ በጽሁፍ አንዳድ ኮፒ ለያንዳንዱ ተሳታፊ መ/ቤት ኃላፊ፤ ለሽግግር መንግሥቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ተወካያዎች ጨምሮ ታደላቸው:: የ20ዎቹ ጥያቄዎች ደብዳቤ እንዳለ ለጉባኤተኛው በንባብ ተሰማ:: በጥያቄዎቹ ላይ ውይይት ሲደረግ ለመናገር እድል ያገኙ ሰዎች ሁሉ የመምህራን ሕይወት እጅግ በሚአሳዝንና በሚአሳፍር ሁኔታ መጎሳቆሉን፤ ሞዴል ሳይገቡ (ከቀጣዩ ወር ደሞዝ ላይ ሳይበደሩ) የሚቆዩ መምህራን በጣት እንደሚቆጠሩ፤ ከነጋዴ የተበደሩትን መክፈል እያቃታቸው በህብረተሰቡ ዘንድ አመኔታና ከበሬታ እንዳጡ፤ የተቀደደ ሱሪና ኮሌታው የነተበ ሸሚዝ ለብሰው፤ ተረከዙ የተጣመመ ጫማ አርገው ክፍል እንደሚገቡ፤ ይሄ ሁሉ በሙያው ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ፤ የሀገራችን ትምህርት የጥፋት ጠርዝ ላይ እንደተንጠለጠለ የመጡበትን አካባቢ ተሞክሮ እንደምሳሌ እየጠቀሱ ድጋፍ ከመስጠት አልፎ እነዚህ በኢመማ የቀረቡ ጥያቄዎች አንዳቸውም ከመሬት ጠብ እንደማይሉ ታውቆና ታምኖበት አግባብ ያለው በጎ ምላሽ ካላገኙ የትምህርቱ ጉዳይ እስከወዲያኛው እንደሚአበቃለት ሲቃ እየተናነቃቸው ተናገሩ:: ከትግራይ ክልል ከመጡት አንድ የመንግት ተወካይ (አቶ ገብሩ አሥራት ይመስሉኛል) ብቻ ሙሉ በሙሉ ባይቃወሙም በደፈናው ሁኔታው እንዳልጣማቸው ለመግለጽ ሞክረው ነበር::

ጉባኤተኛው ሀሳቡን ሲአጠቃልል ከ20ቹ ጥያቄዎች በት/ሚኒስቴር ደረጃ የሚፈቱት ተለይተው በዚያ ደረጃ አስቸኳይ መልስ እንዲሰጣቸው፤ የተቀሩት በመንግሥት ደረጃ ውሳኔ የሚአስፈልጋቸው ለጠ/ሚ ጽ/ቤት እንዲቀርቡ የጋራ ስምምነት ላይ ደረሰ:: ይሄንንም የሚያዘጋጅ አንድ ኮሚቴ ከት/ሚ እና ከመምህራን ማህበር ተውጣጥቶ እንዲዋቀር ተወሰነ:: የተዋቀረው ኮሚቴ አምስት አባላት ሲኖሩት ሰብሳቢው ከት/ሚ አቶ አዋሽ ገብሩ ነበሩ:: እኔም ኢመማን በመወከል ነበርኩበት:: በተሰጠን የጊዜ ገደብ ሥርተን አስረከብን:: ከት/ሚ ጋር በሚሰጡት መልሶች ላይ ወዲያው ድርድር ተጀመረ:: የጋራ ስምምነት የደረስንባቸው ለውጦችም ነበሩ:: ከጠ/ሚ ጽ/ቤት ቢሮም መጀመሪያ ላይ ቀና አቀባበል ስለተደረገልን ትንሽ ጊዜ እንደንሰጣቸው ሲነግሩን አልተከፋንም ነበር:: ቁርጥ ያለ ጊዜ ገደብ እንዲሰጡን ጠይቀን ግን አልሆነልንም:: በመሀከሉ መምህራን ከያሉበት ተንቀሳቀሱ:: በየክልሉ በገጠር በከተማ ለ20ዎቹ ጥያቄዎቻችን መልስ ይሰጠን የሚሉ ሰላማዊ ሰልፎች ተቀጣጠሉ:: በማእከል ደረጃም ከየክልሉ የተወከሉ መምህራን የተሳተፉበት እዚህ አዲስ አበባ ሰንጋ ተራ ካለው የማህበሩ ዋና ጽ/ቤት ተነስተን ብሶታችን እያስተጋባን አራት ኪሊ. እስካለው ጠ/ሚ ቢሮ ሰላማዊ ሰልፍ አድርገን ለጥያቄአችን መልስ እንዲሰጠን ጠየቅን:: በየመንገዱ ህዝቡ የጋለ ድጋፍ ይሰጠን ነበር:: የተቀላቀሉን ወጣቶችም ብዛት ነበራቸው:: በሽግግሩ መንግሥት በኩል ግን አባ ከና የሚለን አጥተን ለብዙ ሰዓታት ከጮህን በኋላ የህላፊነቱን ደረጃ ያልገለጸልን አንድ ሰው ከውስጥ ብቅ ብሎ በያላችሁበት ሆናችሁ መልሱን ተጠባበቁ ብሎን ሄደ::

አጠቃላይ አዝማሚያው ያላማራቸው መምህራን የሥራ ማቆም አድማ እንድንጠራላቸው ግፊት ያደርጉ ጀመር:: በየክልሉ ከአሁን በባሰ የይስሙላ የመንግስት ሥልጣን ይዘው የነበሩ ግለሰቦች በህወሀት ሰዎች ትዕዛዝ ውስጥ ውስጡን መምህራን በብሔረሰብና በቋንቋ መከፋፈል ጀመሩ:: የኢመማ ጊዜዊ ሥራ አስፈጻሚና አስተባባሪ ኮሚቴም አይወክለንም እንዲባልና 20ዎቹ ጥያቄዎች ከጀርባቸው እኩይ የፖለቲካ ተልዕኮ እንዳላቸው ለማሳመን ብዙ ተደከመ:: አልተሳካም:: በተለይ እኔ እስከማውቀው 20ዎቹን ጥያቄዎች ጥያቄዎቻችን አይደሉም የሚል አንድም መምህር በየትኛውም ሥፍራ አልተገኘም:: የህወሀት/ኢህአዲግ ካድሬዎችን በማህበሩ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የመግባት ሴራ የማህበሩ ዋናው ጽ/ቤት አውግዞ የሥራ ማቆም አድማውን በመደገፍ መግለጫ አወጣ:: ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ከ4 ኪሎ (ከማዕከል) አመራር የሚሰጠው የኢህአዲግ ግብረ ኃይል በመላው ሀገሪቱ ተሰማርቶ በመምህራን የተመረጡትን የኢመማ መሪዎች በማዋከብ በመንግሥት ካድሬ ሽዋሚዎች የመተካት ዘመቻ በይፋ ተቀጣጠለ:: የመጀመሪያው ተለጣፊ ማህበር የተቋቋመው በነአቶ ተወልደና አቶ ቢተው አመራር ሰጪነት በሀዋሳ ከተማ በ1985 ነበር:: በመቀጠል የተቋቋመው አዲስ አበባ ሲሆን በነአቶ ዮሐንስ ሐጎስ (ወደ ኤርትራ ተመልሰዋል) እነ አቶ ቅዱስ ዓለማየሁ (አሁንም በዛው ቦታ ያሉ) እየተመራ እኛን በማሳሰር፤ ቢሮዎች በማሸግ፤ ንብረት ያለ ፍ/ቤት ትእዛዝ በመውረስ የጥምር መንግሥት ያክል ኃይልና ስልጣን ነበረው:: ከዚያ በኋላ በመምህራንና በሙያ ማህበራቸው ላይ ለዓመታት የደረሰውን ግፍ ሁሉ (ማዋከብ፤ በገንዘብ መቅጣት፤ ከሥራ ማገድ፤ በፍ/ቤት ማንገላታት፤ በፍተሻ ሽፋን ንብረት መውረስ፤ እስራት፤ ግድያ ስለመፈጸሙ) እንኳንስ ባለ ጉዳዩ መምህራን፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብና የዓለም አቀፉ ሕብረተሰብ ጠንቅቆ ያውቀዋል:: አለባብሰው ቢያርሱ ባረም ይመለሱ እንዲሉ ሆነና የዛሬ 20 ዓመት የቀረበ ጥያቄ በተለይ የደሞዝ ጭማሪን አስመልክቶ በወቅቱ ሁነኛ ምላሽ ስለተነፈገ አልፎም በኃይል ስለታፈነ ውስጥ ውስጡን ሲብላላ ቆይቶ አሁን መምህራን ከሚሸከሙት በላይ ስለሆነባቸው አብጦ ፈነዳ:: የመጨረሻዉን ክፍል ሳምነት እንመለስበታለን::

# አንድነት ፓርቲ የአዲስ አበባ ምክር ቤት መሠረተ

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ (አንድነት) ፓርቲ ቋሚ የአዲስ አበባ ምክር ቤት መሠረተ፡፡ ፓርቲው ሚያዚያ 28 ቀን 2004 ዓ.ም. በዋና ጽ/ቤቱ አዳራሽ ቀኑን ሙሉ ከ23ቱም የአዲስ አበባ የምርጫ ወረዳዎች መስራች አባላት ጋር ከተወያየ በኋላ በይፋ ምክር ቤቱ ተመስርቷል፡፡

በምስረታው ላይም የፓርቲው ሥራ አስፈፃሚዎች የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ የሆኑት አቶ ሙላት ጣሰውና የህግና ሰብዓዊ መብት ጉዳይ ኃላፊ አቶ ደምሴ መንግሥቱ የሚመሰረተው ምክር ቤት ከፊቱ ብዙ ስራዎች እንደሚጠብቁት በመጠቆም የመክፈቻ ንግግራቸውን አድርገዋል፡፡

የጊዜያዊ ምክር ቤቱ አስተባባሪ የነበሩት ዶ/ር ንጋት አስፋው ያለፈው ጊዜያዊ ምክር ቤትን የሥራ ሪፖርት በማቅረብ በተለያዩ ምክንያቶች የሚጠበቅበትን ያህል እንዳልሰራ ጠቁመዋል፡፡ ስለሆነም ቋሚ ምክር ቤቱ የአዲስ አበባ ከተማ የ2005 ዓ.ም. ምርጫን ጨምሮ ብዙ ሥራዎች ከፊቱ ስለሚጠብቁት ለዚህ የሚረዳ እቅድም መዘጋጀቱን ይፋ አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም አዲስ አበባ በአሁኑ ወቅት በዋና ጽ/ቤቱ ላይ የቢሮ ጥገኛ ቢሆንም የራሱ የባንክ ሂሳብ ከፍቶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑንም አውስተዋል፡፡

የጊዜያዊ ም/ቤቱን ሪፖርት ተከትሎ ከመስራች አባላተም በርካታ ጥያቄዎች ተነስተው ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የጊዜያዊ ምክር ቤቱ አስተባባሪዎችም ሰርተናል ያሉትን ለመስራች አባላት እንደየስራ ድርሻቸው ያቀረቡ ሲሆን መስራች አባላትም ጊዜያዊ ምክር ቤቱ በተጨባጭ የሰራው ሥራ እንደሌለ በመጠቆም ተችተዋል፡፡ በመጨረሻም ቋሚ ምክር ቤቱን በመመስረት ውይይቱ ማብቂያ ላይ ‹‹ህገ መንግሥቱ ጥላዬ›› የሚል ግጥም በዘላለም ተፈራ በመድረኩ ላይ በማቅረብ የጠዋቱ መርሃ-ግብር ተጠናቋል፡፡

በመቀጠልም ከሻይ ቡና እረፍት በኋላ ከየወረዳዎቹ ተወክለው የመጡት 46 የቋሚ ምክር ቤቱ መስራች አባላት የአዲስ አበባ ሥራ አስፈፃሚዎችንና ኦዲትና ኢንስፔክሽንን በኃላፊነት የሚመሩ እጩዎችን ጠቁመዋል፡፡ በዚህም መሠረት ተወዳዳሪ ያልሆኑ 3 አስመራጮች በፈቃደኝነት ሂደቱን መርተዋል፡፡

የተጠቆሙ እጩዎችም ራሳቸውን፣ የትምህርት ደረጃቸውንና የፖለቲካ ትግል ተሳትፏቸውን ካስተዋወቁ በኋላ ምርጫው ተካሂዷል፡፡

ለሥራ አስፈፃሚነትም ዶ/ር ንጋት አስፋው ሰብሳቢ፣ ወ/ሮ አስካለ ሳህሉ ም/ሰብሳቢ፣ አቶ አያከሉህም ጀንበሩ ፀሐፊ፣ አቶ ተስፋዬ ረታ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፣ አቶ ዘላለም ተፈራ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣ እና አቶ ሽባባው መንግሥቱ የገንዘብና ንብረት ጉዳይ ኃላፊ በመሆን ተመርጠዋል፡፡ ወ/ሮ እጥፍወርቅ በልእስቲ፣ አቶ አለማየሁ በቀለ፣ አቶ ሸዋንግዛው እሸቱ እና አቶ ወንድምአገኝ አስፋው ተጠባባቂ ሆነው ተመርጠዋል፡፡

ለኦዲትና ኢንስፔክሽን ደግሞ አቶ እንግዳወርቅ ማሞ ሰብሳቢ፣ አቶ ሰለሞን ታደሰ ፀሐፊ፣ አቶ ሳሙኤል ብዙአየሁ፣ አቶ ሲሳይ ካሴ እና አቶ አድማሱ አለነ አባል በመሆን የተመረጡ ሲሆን አቶ ብሩክ አሻግሬ እና አቶ ኢሳይያስ ቱሉ በተጠባባቂነት መመረጣቸው ታውቋል፡፡ በመጨረሻም በአዲሱ ሥራ አስፈፃሚ ተመራጮች የመዝጊያ ንግግር በኋላ ምስረታው ተጠናቋል፡፡

## ለአቶ ዘላለም ጀማነህ የወጣው ወጪ ቁጣን መቀስቀሱ ተሰማ

የኦህዴድ ፅ/ቤት ሀላፊ የነበሩት አቶ ዘላለም ጀማነህ የመኪና አደጋ እንዳጋጠማቸው ታወቀ፡፡ አቶ ዘላለም ጀማነህ ሚያዚያ 24/08/04 ዓ.ም ወለጋ ውስጥ ወደምትገኘው የትውልድ ቀያቸው ቤጊ ከባለቤታቸው እና ልጆቻቸው ጋር በሾፌርና በአጃቢዎች ሆነው ሲሄዱ በደረሰ የመኪና መገልበጥ አደጋ ጉዳት እንደደረሰባቸው የታወቀ ሲሆን አብሯቸው የነበሩት ሌሎች ሰዎች የከፋ አደጋ ያለማጋጠሙ አግራሞትን ጭሯል፡፡ አደጋው እንደደረሰ ጉዳት የደረሰባቸውን አቶ ዘላለም በአቅራቢያው ወደሚገኘው ግምቢ አሊያም ነቀምት ሆስፒታል መውሰድ ሲቻል በልዩ ኮንትራት (chartered) በ930 ሺህ ብር አዉሮፕላን ተከራይቶ እንዲመጡ ያደረጋቸው የክልሉ ጽ/ቤት ኃላፊ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደደረሰባቸው የውስጥ ምንጮቻችን ገለጹ፡፡

የክልሉ ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ አበራ ይፋ ጸሐፊዎች ከሚጠቀሙበት ወረቀት ጀምሮ ከፍተኛ ቁጥጥር የሚያደርጉ እንደሆነ የታወቀ ሲሆን ከክልሉ መንግሥት ካዝና ወጭ ሆኖ ወደ አንድ ሚሊየን የሚጠጋ ገንዘብ እንዴት ለአንድ የክልል ስራ አስፈፃሚ ወጪ አንደተደረገ መጠየቅ እንዳለባቸው የጽ/ቤቱ ሰራተኞች መጠየቃቸውን ምንጮቻችን አረጋገጡ፡፡ አስተያየቱን ለፍኖተ ነፃነት የሰጠ አንድ ሰው "ከዚህ በፊት ፀረ ሙስና ኮሚሽን በሰጠን ስልጠና ላይ የሙሉ ቀን ውሎ አበል 46 ብር እንዳንወስድ ለማድረግ ስልጠናውን በግድ ወደ ግማሽ ቀን ያሳጠሩት ሲሆን ከያንዳንዱ 300 ሰልጣኝ 23 ብር ማዳናቸውን ሲያወሩ የነበሩት አሁን ለዚህ ሁሉ ምን አነሳሳቸው?" ሲል ጠይቋል፡፡ ሌላው አስተያየት ሰጪ "የግል አውሮፕላን መኮናተር ባያስፈልጋቸውም ከተደረገ አይቀር ከመንግሥት ሳይሆን ከኦህዴድ መውጣት በተገባው ነበር" ሲሉ አማረዋል፡፡ ገንዘቡን ወጪ ያስደረጉት አቶ አበራ ይፋ ከኢሉባቦር ም/አስተዳዳሪነት የመጡ ሲሆን የአቶ ኩማ ደመቅሳና የወ/ሮ አስቴር ማሞ "የእጅ ስራ" እንደሆኑ በሰፊው ይነገራል፡፡

## እነ አንዱዓለም አራጌ አርብ ፍ/ቤት ይቀርባሉ
## በአንድነት ፓርቲና በኢቴቪ መካከል የተመሰረተው ክስ ሳይሰማ ቀረ

በፌደራሉ አቃቤ ህግ ክስ ተመስርቶባቸው በፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት በ "ሽብርተኝነት" ተጠርጥረው ጉዳያቸው እየታየ ያለው እነ አንዱዓለም አራጌ አርብ ግንቦት 3 ቀን 2004 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ይቀርባሉ፡፡

ፍርድ ቤቱም የአቃቤ ህግ ምስክሮችን ቃል ከሰማና የቀረበለትን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ብይን መስጠቱ ይታወቃል፡፡ ተከሳሾችም የተከሳሽነት እና የመከላከያ ምስክሮቻቸውን ቃን ከማሰማት በተጨማሪ ለቀረበባቸው ክስ የተለያዩ ማስረጃዎቻቸውን ማቅረባቸው ይታወሳል፡፡

የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራቀኙን ከሰማና ከመረመረ በኋላ የፊታችን አርብ ጠዋት ፍርድ ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ ከፍርዱ በፊት የክርክር ማቆሚያ ሐሳብ በጽ/ቤቱ በኩል እንዲቀርብ ማዘዙ ተጠቁሟል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድነት ፓርቲ በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት (ኢሬቴድ)እና በጋዜጠኛ አብዲ ከማል ላይ የፌደራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 9ኛ የፍታብሔር ችሎት ክስ መመስረቱ ይታወቃል፡፡

ፍ/ቤቱም ክሱን ለመስማት ሰኞ ሚያዝያ 29 ቀን 2004 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ላይ ቀነ ቀጠሮ የሰጠ ቢሆንም ዳኛው መዝገቡ አሁን ስለደረሰኝ አላየሁትም ብሏል፡፡ በዚህም መሰረት ፍ/ቤቱ ክሱን ለመስማት በድጋሚ ለግንቦት 3 ቀን 2004 ዓ.ም. ከቀኑ 8፡15 ሰዓት ተለዋጭ ቀነ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡በዕለቱም የአንድነት ጠበቃ አቶ ገበየሁ ይርዳው፣የኢቴቪ ነገረፈጅ አቶ ተማም ሁሴን እና ጋዜጠኛ አብዲ ከማል ችሎት ቀርበው ነበር፡፡

አንድነት ክስ የመሰረተባቸው "አኬልዳማ" በሚለው ዘጋቢ ፊልም ላይ ኢቴቪንና አቅርቢውን ጋዜጠኛ አብዲ ከማልን በመቃወም መሆኑ ይታወቃል፡፡

## የደብረ ማርቆስ . . .

ከገፅ 1 የዞረ

የሆነውና ከትግራይ ክልል የመጣው ገብረ ኪዳን ብርሃኔ ትላንት ጠዋት በጀርባውና በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቹ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰበት ለዝግጅት ክፍሉ ተናግሯል፡፡ በትላንትናው እለት ከጠዋቱ 2፡30 ጀምሮ ‹‹የታሰሩ ተማሪዎች ይፈቱ›› የሚል ጥያቄን ይዞ የቀጠለው ተቃውሞ ቀስ በቀስ ከዩኒቨርሲቲው ውጪ መስፋፋቱን ከከተማው ያገኘናቸው መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ ተቃውሞው በደብረ ማርቆስ ከተማ ጎዳናዎች ላይ በቀጠለበት ወቅት በርካታ የከተማው ነዋሪዎችም ትዕይንቱን ተቀላቅለው ጥያቄው ፖለቲካዊ ይዘት ተላብሶ ገዢውን ፓርቲ በማውገዝ እና ለኑሮ ውድነቱ ገዢውን ፓርቲ መኮነናቸውን ምንጮቻችን ተናግረዋል፡፡ ይህን ተከትሎም ታጣቂቆች ቶክስ በመክፈታቸው ተቃውሞው ተበትኗል ሲሉ ምንጮቻችን ዘግበዋል፡፡ በሁኔታው የተደናገጡት ተማሪዎች ወደ ተለያየ አቅጣጫ ሲበታተኑ ታጣቂዎችና ፖሊሶች አብዛኞቹን እያፈሱ ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንዳጓጓዟቸው የከተማው ነዋሪዎች ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ወደ ህትመት እስከገባንበት ጊዜ ድረስ አፈሳው እንደቀጠለ ተናግረዋል፡፡ ጨምረውም በድብደባዉ ከተጎዱ ተማሪዎች መካከል አይናቸዉ ተመትቶ ኦፐራሲዮን የተደረጉ እንደሚገኙበት አስረድተዋል፡፡ ከስፍራው የደረስን መረጃ እንደሚያመለክተው በተማሪዎቹ ላይ እርምጃ የተወሰደው ስልጠናቸውን ባልጨረሱ ፖሊሶች ጭምር መሆኑን ያመለክታል፡፡ ማምሻውን የደረሰን መረጃ እንደሚያመለክተው አሁንም በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ትገኛለች፡፡

ዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ጥሪ አስተላልፏል፡፡ በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ ለማግኘት ወደ ዩኒቨርሲቲውና ወደ ደብረማርቆስ ሆስፒታል ደውለን ምላሽ ወደ ህትመት እስከገባንበት ሰአት ድረስ ምላሽ ማግኘት አልቻልንም፡፡

## በደቡብ ሌሎች ነዋሪዎች ላይ የመፈናቀል አዝማሚያ እየታየ መሆኑ ተገለፀ

በደቡብ ክልል በሚገኘው አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ ኤልጎዶንቤ ቀበሌ ነዋሪዎች ከሰሜን ሸዋ በተለይም ከመንዝ በ1950 ዎቹ ውስጥ ሄደው የሰፈሩት ለቃችሁ ውጡ መባላቸውን ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡ነዋሪዎቹም ከአካባቢው በተለይም ዘይሴ ከሚባለው ማህበረሰብ ጋር ተዋልደው የልጅ ልጅ ለማየት መብቃታቸውም ተጠቁሟል፡፡

ይሁን እንጂ አንዳንድ የመንግሥት መስተዳድር ኃላፊዎች ባልታወቀ ምክንያቱ ለቃችሁ እንድትወጡ የሚል ማስፈራሪያ እየሰጡ መሆናቸውን በመስማቱ የአካባቢ ነዋሪዎች ተቃውሞ ማሰማታቸው ተገልጿል፡፡

ይሄንንም ጉዳዩ በቀጥታ ይመለከታቸዋል ወደተባሉት የወረዳው አስተዳደር አቶ ግዳኔ ገረመው ጋር በተደጋጋሚ ጥረት ብናደርግም አልተሳካም፡፡ ነገር ግን የወረዳው ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ ኢንስፔክተር መርዶኪዮስ ገልቻ ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው በተጠቀሰው አካባቢ ችግር እንደነበር በመግለፅ የነበረው ችግር ፍትሀዊ የመሬት ክፍፍል እንዲደረግና መፍትሔ እንዲሰጣቸው ያነሱት የጋራ ጥያቄ መሆኑን አስታውሰዋል፡፡ ለዚህም ከወረዳው መስተዳድር ጋር ሄደን አነጋግረናቸው በቅርቡ መፍትሔ እንደሚሰጣቸው ከአስተዳደሩ እንደተነገራቸውና ጉዳዩ ከብሔር ጋር የሚያያይዘው ነገር እንደሌለ ጠቁመዋል፡፡

አያይዘውም ጥያቄውን ያነሱት የአካባቢው ነዋሪዎች የሆኑት የዘይሴና የአማራው ማህበረሰብ በጋራ እንደሆነና ከመንዝ የመጡት ለረጅም ጊዜ የቆዩና ወልደው ተቀላቅለው በሠላም እየኖሩ ስለሆነም ማንም ውጡ ሊላቸው እንደማይችል አረጋግጠዋል፡፡

የጋሞ ጎፋ ዞን ፖሊስ መምሪያ ኃላፊ የሆኑት ኮማንደር ታዬ ጫርቃ በበኩላቸው የተጠቀሰው አካባቢ ማህበረሰብ ዘይሴፋንጎ የሚባል ቀበሌ ተሻግረው በማረሳቸው የተፈጥሮ ደን በመጎዳቱ ለመስተዳድሩ ህጋዊ የሆነ ቦታ በአግባቡ እንደሚሰጣቸው ተነግሯቸዋል እንጂ ሌላ የተፈጠረ ችግር የለም ብለዋል፡፡ ነዋሪዎችንም ቢሆን የጋራ የሆነ የአካባቢውን የተፈጥሮ ሀብት እንዲጠብቁ ከመንገር ውጭ ውጡ ያለ እንደሌለና ማንም ሊል እንደማይችል ምላሽ ሰጥተውናል፡፡

የዞኑ መስተዳድር ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ እሸቱ ገላጋይ በበኩላቸው ከአካባቢው ተበደልን የሚሉ ወገኖች መጥተው ተገናኘተን ከታያየን በኃላ ለከፋት የማይሰጥ ባለመሆኑ ወደ አካባቢው እንዲመለሱ ተደርጓል ብለዋል፡፡

## የመድረክ ከፍተኛ አመራር የመከላከያ ምስክሮች ቃል መደመጥ ጀመረ

በፌዴራሉ አቃቤ ህግ በ‹‹በሽብርተኝነት››የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የተመሠረተባቸው እነ አቶ በቀለ ገርባ የመከላከያ ምስክሮቻቸውን ቃል ለፍ/ቤቱ ማሰማት ጀመሩ፡፡

በተለይ የመድረክ ከፍተኛ አመራር፣ የኦፌዴን ምክትል ፕሬዚዳንት እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት በቀለ ገርባ ከተከሰሱባቸው ክሶች ውስጥ በ2 የክስ ጭብጥ ላይ ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም. የመከላከያ ምስክሮቻቸውንና የተከሳሽነት ቃላቸውን ለፍ/ቤቱ አሰምተዋል፡፡

መከላከያ ምስክሮቻቸውም የተከበሩ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ፣ የመድረክ ሥራ አስፈፃሚ አባል የሆኑት አቶ በቀለ ነጋ፣ባልደረባቸው የሆኑት መምህር አለሙ ዋቅጅራ እና ባለቤታቸው መምህርት ሐና 3ኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡

ሚያዚያ 26 ቀን 2004 ዓም በዚሁ የክስ መዝገብ 3ኛ ተከሳሽ የሆኑት የወጣት አልቤካ ለሚ ምስክሮች ከርቀት የክልል አካባቢ በመምጣታቸው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡

ኦልባና ሌሊሳን ጨምሮ የሌሎች ተከሳሾችን የተከሳሽነት እና የመከላከያ ምስክሮችን ቃል ለመስማት ፍ/ቤቱ ለግንቦት 2 ቀን 2004 ዓ.ም. ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ተለዋጭ ቀነ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

# ወጣቱ አገራዊ አጀንዳዎች ላይ የነቃ ተሳትፎ ይኑረው

ስንታየሁ ቸኮል

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘው ነው፡፡ ይህ የህብረተሰብ ክፍል ማንኛውንም ዓይነት እውቀት ለመቅሰም የሚያስችል ቀልጣፋና ብሩህ አእምሮ፣ ለምርታማነት ተግባር ሊውል የሚያስችል ጉልበትና በቀላሉ የማይዝል አካላዊ ጥንካሬ ያለው ነው፡፡ በዚያው ልክ በአግባቡ ካልተያዘ በስተቀር ከወጣትነቱ ተፈጥሮአዊ ሁኔታ በተያያዘ ምክንያት በተለያዩ አደጋዎች በቀላሉ ሊጋለጥ የሚችል ነው፡፡

የወጣቱ ዝንባሌ የብዙ ጉዳዮች ድምር ውጤት ነው

ብዙ ጊዜ በወጣትነት እድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ዜጎች መካከል ጥቂቶቹ ጥፋት በሚፈፅሙበት ወቅት ወጣቱን እንዳለ የማውገዝና የማማረር አዝማሚያ ጎልቶ ይንፀባረቃል፡፡ የዘቀጠ፣ ደካማ፣ የሀገር ፍቅር የሌለው፣ ለሰዎች ክብር የማይሰጥ፣ በንቀት የተወጠረ ወዘተ ትውልድ እያሉ የወጣቱን ባሕሪይ መጥፎ ምስል የሚሰጡ ሰዎች ጥቂት አይደሉም፡፡

የእነዚህ ተቀፅላ ስሞችን በሚያናፍሱ ሰዎች አብዛኛው ወጣት አቅሙንና እውቀቱን በመጠቀም ተፈጥሮዊ ዝንባሌውንና አገራዊ ራዕዩን እንዳያሳካ ከየትኛውም ጊዜ በላይ አሁን አገሪቷን እየመራ ያለው ገዥው ስርዓት እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡ ወጣቱን ረግጦና ከፋፍሎ ለመግዛት የተለያዩ ስልቶችን የሚጠቀመው የኢህአዴግ ስርዓት በአገራዊ አጀንዳዎቹ ላይ ገለልተኛ በማድረግና አካዳሚያዊ እውቀቱንም የላሸቀ በማድረግ የፈረንጅ ባህል ተከታይ እና በተለያዩ ሱሶች በቀላሉ ተጠቂና ተጋላጭ እያደረገው ይገኛል፡፡ ይሄ አይነቱ ሰይጣናዊ አመለካከት ትውልድን ከመግደል ጀምሮ በአገራዊ ጉዳይ ላይ የነቃ ተሳትፎ የሚያደርግ ወጣት እንዳይፈጠር ሆን ብሎ እየሠራበት ይገኛል፡፡

ለወጣቱ ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት፣ ጤንነቱን የጠበቀ ዘላቂ ህልውናውን የሚጠቅም የሥራ ዕድል፣ የዴሞክራሲና የልማት አጀንዳ ቀርፀውለት፣ የረባ ነገር ሳይሰሩ ትላንት ወጣት የነበረው እንዲሁ በከንቱ ጎልማሳ እየሆነ ዘመንን ዘመን እየተካው መኖር የተለመደ ሆኗል፡፡ በአለም ውስጥ ካሉት አገራት እንደ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ሁሉንም አይነት ዕድል የተነፈገባቸው ለመከራና ስቃይ ብቻ የተጋለጡ አሳዛኝ ስለ መኖራቸው ያጠራጥራል፡፡

በኢትዮጵያ ያሉት ወጣቶች የስርዓቱን እድሜ ማራዘሚያ ተደርገው በርካሽ የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ጊዜቸውን እንዲያሳልፉ የተፈራደባቸው ይመስላሉ፡፡ የአገራችን ወጣት ጦርነት የሚለበልበው፣ ርሃብ የሚጨርሰው፣ እስርና ግርፋት የበዛበት፣ አገሩን ጥሎ መሰደድ ያንገሸገሸው የመማርና ስራ የማግኘት የዜግነት መብቱን የተገፈፈበት፣ ለበሽታና ለተለያዩ አደጋዎች የተጋለጠ በዓለም ላይ አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ተፈጥሮአዊ አቅሙንና ለጋ አእምሮውን ተጠቅሞ ሕገ መንግስታዊ ክብሩንና ሰብዓዊ መብቱን ለመጠበቅና ለማስጠበቅ እንዳይችል ሀሳቡን በነጻነት ለመግለፅና ሕገ መንግስታዊ የሆነውን ሰላማዊ ተቃውሞውን እንዳይገልጽ ለትንታኔ በማይመች ሕግ በመቆላለፍ ቅርቃር ውስጥ ለማስገባት እየተሰራበት ይገኛል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሽብርተኝነት ሕግ ከብዙ በጥቂቱ አመላካች ነው፡፡ ይህ በወጣቱ ላይ እየተሰራበት ያለውን ደባ የስርዓቱን መሰሪ የጥፋት መንገድ የሚያጋልጡና የተሻለ ሀሳብ አለን ለሚሉ ወጣቶች የተዘጋጀ መጣያ መሆኑን የኢህአዴግ ስርዓት ለወጣቱ ያለው አመለካከት ማሳያ ነው፡፡ ለዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብታቸው ዘብ የቆሙ ወጣት ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ላይ የተቃጣው ድርጊት ስርዓቱ በወጣቱ ላይ የከፈተው ዘመቻ ከመሆኑም በላይ ስርዓቱ የሚያራምደው የተሳሳተ የፖለቲካ ድምር ውጤት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

«መብቴ ተነካ፣ ጥቅሜ ተጓደለ፣ ነጻነቴ ተገፈፈ» የሚሉትን ወጣቶች ሳያዳምጡ እንዲሁ ከማንኛውም የውይይት አጀንዳ ውጭ አድርገው የረሱትን ወጣት ዳር ድንበር ሲደፈር የአገር አንድነት ሲናጋና መውጫ መግቢያ ሲጠፋ ብቻ «አገር ተረካቢ ወጣቱ፣ የአገር ተስፋ ወጣቱ፣ የአገር መከታ ወዘተ» እያሉ ከወረቀት ያላለፉ ተረት ማሞካሸት በኢህአዴግ ቤት የተለመደ ነው፡፡

ብዙውን ጊዜ የወጣቱ አብይ ፍላጎቶች በዴሞክራሲና ሰባዓዊ መብቶች የታነፀ ስርዓትና የተረጋጋ ሰላም ማግኘት፣ ጤናው የተጠበቀ ዜጋ መማርና እውቀቱን ማስፋቱ በሙያው ስራ ማግኘት የመሳሰሉት ከብዙ ጥቂቶቹ ፍላጎቶቹ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች አለመታደል ሆኖ በሁሉም ሁኔታ ፈተና ውስጥ ለመኖር ቢገደዱም ከዚህ ለመውጣት የሚያስችል የህይወት አማራጭ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሞትን፣ ራሃብን፣ ስደትን፣ መሃይምነትን፣ በሽታን ጦርነትን፣ የሙብት ረገጣን እየኖሩበት ስለሆነ ጉዳቱን በሚገባ ያውቁታል፡፡ ይህንን አገራዊ ውርደት ተሸክሞ መቆየት ጥሩ የህይወት አማራጭ እንዳልሆነ ይረዱታል፡፡ በመሆኑም ወጣቱ ከዚህ የተሻለ ህይወት እንዲኖር ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው ለማህበረሰብ ፍላጎት መሳካት በምናደርገው እልህ አስጨራሽ የሰላማዊ ትግል ላይ በተናጠል ሳይሆን የተደራጀ አቅም በመፍጠር በሚደረገው ሰላማዊና ሕገ መንግስታዊ ጥያቄ ፊት መቆም ስንችል ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ወጣቱ አቅሙንና ጉልበቱን ተጠቅሞ ትግሉን መቀላቀል ያለበት ከየትኛው ጊዜ በላይ አሁን ነው፡፡ ሁላችንም የድርሻችንን በመወጣት በተባበረ ክንድ የአገራችን ተስፋ እናለምልም የምንግዜም ሀሳቤ ነው፡፡

---

## የፖለቲካው ውጥረት . . .

ከገፅ 4 የዞረ

እንደሚጠቀም የሚያመላክቱ ሆኑ፡፡

የኢ/ፌ/ዴ/ሪ ሕገመንግስት በአንቀፅ 11 መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ እንደሆኑ ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሁሉንም ሃይማኖት በእኩል ለማስተናገድ መደላድል የሚፈጥር ይመስላል፡፡ ሆኖም መንግስት የሃይማኖት ተቋማት በመንግስት ጉዳዮች ውስጥ እንዳይገቡ በሩን ቢቆልፍም፤ በሃይማኖት ተቋማቱ ጉዳይ ውስጥ ግን ከእልፍኝ እስከ ማጀት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እንደሚገባ ይነገራል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተስፋፋ ስለመጣው የሙስሊሞች ሀገር አቀፍ ተቃውሞ ለመረዳት አንድ ወጣት ጋዜጠኛ አገኘሁ፡፡ የሱፍ ጌታቸው ይባላል፤ የሙስለሞች ጉዳይ የተባለች ኢስላማዊ መጽሄት ላይ ዋና አዘጋጅ ነው፡፡ ጥቂት የማይባሉ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ክፍሎች «የመንግስት ረጃጅም እጆች በመጅሊሱ ውስጥ ያሻቸውን የደርጋሉ » ሲሉ ይደመጣል፡፡ ዩሱፍም ይህንን እምነት ይጋራል፡፡ በመጅሊሱ ውስጥ የመንግስት እጅ ጎልቶ መታየት የጀመረው በ1987 ዓ.ም መመጅሊሱ ውስጥ ተከስቶ የነበረውን የስልጣን ሽኩቻ ተከትሎ የሚፈልጋቸው አካላት ስልጣን እንዲይዙ ባደረገበት ወቅት እንደ ነበር ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ግለሰቦች ያስታውሳሉ፡፡ ይሄ ሁሉ ሆኖም አብዛኛው ሙስሊም የገዢው ፓርቲ ደጋፊ ነበር የሚለው የሱፍ «ኢህአዴግ የፈጠረው የፌደራሊዝም አወቃቀር ለሙስሊሙ አመቺ በመሆኑ በአንዳንድ አካባቢዎች ኢህአዴግ 100% የሚደርስ ድጋፍ ነበረው፡፡» ይህ ሁኔታ ግን ህዝበ-ሙስሊሙ በመጅሊሱ ላይ የኔነት ስሜት እንዲያዳብር አላደረገውም፡፡ እንደ ጋዜጠኛ የሱፍ ጌታቸው አባባል አሁን በስልጣን ላይ ያለው መጅሊስ የኢስላምን ዶክትሪናዊ መስፈርት አያሟላም፡፡ በዩሱፍ ገለፃ መሰረት ኢስላም ለመጅሊስነት የሚመረጡ ግለሰቦች ሊያሟሉ የሚገባቸው 3 ነጥቦች አሉ፡፡

1.የዲን(ሃይማኖታዊ) እውቀት(በዲኑ በአግባብ መኖርና ለሌሎች አርአያ መሆን)

2.አድል(ፍትሀዊነት)

3.ማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ተቀባይነት የሚሉት ናቸው፡፡

በዩሱፍ ትንተና መሰረት መጅሊሱ አባላት ይሄ ነው የሚባል የዲን እውቀት የላቸውም፡፡ ማስረጃውም በየትኛው ቦታ ሲያስተምሩ አለመታየታቸው እንደሆነ ይናገራል፡፡ አድል(ፍትሀዊ) አለመሆናቸውንም አስመልክቶ እስልምና ውስጥ ያሉትን አስተምህሮቶች መስፈርቶች በፍትሀዊነት አይስተናግዱም፡፡ ለምሳሌ ሱፊ፣ ሀለልሱና ወልጀማ፣ ወሐቢያ፣ተብሊክ ጀምአን የመሳሰሉትን አስተምህሮቶች አንዱን ወግነው አንዱን ያፃረራሉ፡፡ ማህበረሰቡ ውስጥ ታዋቂነት የላቸውም፡፡ ተሾሙ ሲባል በዜና ከመታየታቸው ውጪ ቀድመው አለመታወቃቸውን ያስረዳል፡፡

በሃይማኖች መሪዎች ላይ ያለው የኔነት ስሜት ጉድለት በሌሎች ሃይማኖት ተከታዮችም ላይ ይስተዋላል፡፡

አንዳንድ የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታዮችም የሃይማኖት መሪዎቻቸውን እንደ መንግስት «ካድሬ» ይቆጥሯቸዋል፡፡ ስሙን እንዳልጠቅስ የስጠነቀቀኝ አንድ መምህር ግን የማህበረ ቅዱሳን ራሱን ነፃ አድርጎ ለመጓዝ ያደረገው ጥረት ለምእመናኑ መፅናኛ ሆኗቸዋል፡፡ ሰሞኑን አቶ መለስ ለፓርላማ ባቀረቡት ንግግር ማህበረ ቅዱሳንን ከሙስሊም ጽፈኞች መሳ ለመሳ መፈረጃቸው ተዳፍኖ የቆየውን ተቃውሞ እንዲያገረሽ ምክንያት ሆኗል፡፡ ሆኖም ማህበሩን ወክለው ስሜታቸውን የሚያጋሩኝ ኃላፊዎችን ለማግኘት አልቻልኩም፡፡ መረጃ የሰጡኝ አካላትም ስማቸውንና ኃላፊነታቸውን ደብቀውኛል፡፡ በሚገርመው ሁሉም የጠቆሙኝ አደባባይ በተባለ የጡመራ መድረክ ላይ ኤፍሬም እሸቱ ያሰፈረውን «በጠቅላይ ሚኒስትሩ አባባል አልስማማም» የሚለውን ጽሁፍ ነው፡፡ «የማህበሩን አቋም በድረገፃችን ላይ አስፍረናል፤ ተጨማሪ ነገር ለመናገር አልፈልግም» ያሉኝ አንድ የማህበሩ ኃላፊ በደምሳሳው የአቶ መለስ አስተያየት ስህተት ላይ የተመሰረተ መሆኑን በምክንያት አስደግፈው አስረድተውኛል፡፡ በኃላፊው ማብራሪያ መሰረት ማህበሩ የጥምቀት በአል አከባበርን በበላይነት አስተባብሮ አያውቅም፡፡ ስለዚህም በበአሉ ላይ የሚስተጋቡ መፈክሮች ማህበሩን አይመለከቱም፡፡«ጠ/ሚሩ የጠቀሱት መፈክር ይዘት ስህተት አይደለም፡፡ ቃሉ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ » ካሉ በኋላ አክራሪነቱ ግን እንደማይመለከታቸውና ክርስትናም እንደማይፈቅደው አብራርተዋል፡፡ በኦርቶዶክሳውያኑ የሚነሳውን ጥያቄ ካባባሱት ክስተቶች መሀከል በዋልድባ ገዳም ላይ ተጀመረ የሚባለው ልማት በመነኮሳቱ፣ በአካባቢው ነዋሪዎች እንዲሁም በሃይማኖቱ ተከታዮች እና በመንግስት መሀከል የፈጠረው ውጥረት ሌላው የተቃውሞው አካል ነው፡፡

የሙስሊሙ ጥያቄ 3 ነጥቦችን የያዘ እንደሆነ ቅርበት ያላቸው አካላት ያስረዳሉ ፡፡ የመጀመሪያው አህባሽ የተባለውን እንግዳ አስተምህሮ አንቀበልም የሚለው ጥያቄ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ መጅሊሱ የአወሊያ የሙስሊም ሚሲዮናዊ ተቋምን የማስተዳደር ሞራላዊም ሆነ የዕውቀት ብቃት የለውም የሚል ነው፡፡ ሶስተኛው ለአመታት ሲብላላ የከረመው ጥያቄ መጅሊሱን በድምፃችን የመምረጥ መብታችን ይከበር የሚል ነው፡፡

የሙስሊሙን እንቅስቃሴ በስጋት የሚከታተሉ አካላት አሉ፡፡ መንግስትም እንቅስቃሴው ኢስላማዊ መንግስት ለማቋቋም ያለመ ፅንፈኛ አዝማሚያ የያዘ እንደሆነ ገልፃል፡፡ ይህ ስጋት መሰረተ ቢስ አይደለም በቅርብ ጊዜያት በፅንፈኛ ሙስሊሞች በተወሰዱ ዘግናኝ ጥቃቶች በመቶዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች (የኦርቶዶክስና የወንጌላውያን አማኞች) ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትም ተቃጥለዋል፡፡ የሱፍ ጌታቸውም ከኢስላም አስተምህሮ ያፈነገጡና ክርስቲያን ወንድሞቻችንን ያሸበሩ ጥቃቶችን ያደረሱ ፅንፈኛ አካላት በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ እንዳሉ ይስማማል፡፡ ለእነዚህ አካላት መበራከት ምክንያት መንግስትና መጅሊሱ የየበኩላቸውን ኃላፊነታቸውን አለመወጣታቸው አስተዋፅኦ እንዳደረገ ያብራራል፡፡ «መጅሊሱ አደገኛ አስተምህሮዎች ሙስሊሙ ውስጥ እንዳይሰራጭ መከላከል ተፈጥሮም ሲገኝ እርምት መስጠት አልታረም ያለውን ደግሞ ለመንግስት አሳልፎ መስጠት ነበረበት» የሚለው ዩሱፍ ጌታቸው «ለመንግስትም ግብር የምንከፍለው ደህንነታችንን እንዲያስጠብቅ ጭምር ስለሆነ ...እነዚህ አካላት ጉዳት እንዳያደርሱ ማድረግ ነበረበት» ይላል፡፡ ኢስላማዊ መንግስት ኢትዮጵያ ውስጥ ለማቋቋም በየትኛውም የመዋቅር ደረጃ ማቋቋም አስፈላጊ ነው ብሎም እንደማያምን ሲያስረዳ «በኢትዮጵያ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ይህን አይፈቅድም፡፡ ከ60% በላይ ክርስቲያን ባለበት ሀገር ይሄ የማይታሰብ ነው፡፡» በማለት ይደመድማል፡፡

መንግስት በምርጫ 97 ወቅት ሙስሊሙን ነጥሎ እንዳወያየው ሁሉ አሁንም ክርስቲያኑን ነጥሎ የማወያየት እርምጃው ብዙዎችን አሳዝኗል፡፡ «በሕዝበ-ክርስቲያኑ ላይ የሌለ ሽብር እየነዛ ነው» የሚሉም ወገኖች አሉ፡፡ ሁላችንንም ሊያስማማ የሚችለው ነጥብ ግን መንግስት በሀይማኖት ውስጥ እጁን መክተቱና «የአብዮታዊ ዴሞክራት አባቶች የሚያመጡት መዘዝ » ሀገራዊ ውጥረቱን ሩብ ጉዳይ እንዳደረሰው ነው፡፡ እነዚህ ተቃውሞዎች በይፋ፣ በአደባባይ ስላልተንሸራሸሩ «የምን ተቃውሞ?...የምንስ ብሶት?...» የሚሉ፣ የተቃውሞውን መጠን በአግባቡ ያልተረዱ እንዲሁም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያላወቁ የፖለቲካ ተዋናዮችን እንደ መመልከት ምን የሚያስጨንቅ ነገር አለ? የፖለቲካው ውጥረት ሩብ ጉዳይስ ወዴት ያመራ ይሆን?

## Somo Moto - Kiswahili for 'Hot Lesson'!

As successful initiators of the Tanzanian Khanga into the AGOA program (the USA -African Growth Opportunity Act) category 9 benefit, Somo Moto is spearheading the Tanzania khanga culture and tradition into the universal fashion arena.





Khangas are Sold as a pair, our standard measurements are 46"X 1.68mtrs



Celebrate and enjoy your History beautifully with our creative Histori-Kali Khangas

## Somo- Moto Enterprises Ltd

P.O.BOX 105441
DAR ES SALAAM,TANZANIA
TEL: (22) 2862 761
CEL:+255773 975 445,787267307
Email: nefertiti100@gmail.com

# Histori-kali khanga

Celebrating history fashionably The Swahili way!

Versatile and colorful, this soft Tanzanian traditional cotton cloth is prized for generations along the East Afrikan coast as a Woman's best friend !



With a myriad of uses, the Swahili (East Afrikan coastal people) have embraced and molded the cultural significance of the khanga as an effective medium of communication and fashion statement.

Histori-Kali Khangas is now sharing this wonderful culture in Preserving, Advocating and celebrating History—fashionably everywhere...

*Made in Tanzania (the cradle of mankind), East Afrika for the world......*

## 180 የሃዘንና . . .

ከገፅ 4 የዞረ

የሚሉት የኢህአዴግ ሹመኞችም የሕዝቡን ዓይን ላለማየት ፈርተው ተሸሸጉ፡፡

የተከማውም ነዋሪ በከፍተኛ ጭንቀትና ስጋት ከመዋጡ የተነሣ ለበርካታ ቀናት የመኪና ጐማ ሲፈነዳ ተኩስ የተከፈተ መስሎት ሩጫውን በየአቅጣጫው የሚከፍተው ህዝብ ጥቂት አልነበረም፡፡ በዚህ የነፍስ አውጪኝ ሩጫ አዛውንቶች ነፍሰጡሮች፣ ሕፃናቶች፣ አካለ ጐዶሎዎች የሚሄዱበት ጠፍቷቸው ሲርበተበቱ መመልከት ህሊናን ያቆስል ነበር፡፡

ከጥቅምት 28 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮም ለሕዝቡ ቤት የመዋልን ጥሪ የቅንጅቱ‹ ‹ተረፈ አመራር›› ሥፍራው ካልተገለፀ ቦታ ሆኖ ጥሪ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም፣ ከሁለት ቀን በኋላ ግን "ከዲፕሎማቲኩ ማህበረሰብ ጋር በተደረገ ውይይት ለሌላ ጊዜ ተላልፎአል" ሲል መግለጫውን በአማርኛ ከውጪ በሚተላለፉ ሬዲዮ ጣቢያዎች አማካኝነት አሳወቀ፡፡

‹‹ፕሮፌሰር መስፍን ሞተዋል፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋም በድብደባ ብዛት ኮማ ውስጥ ገብተዉ ሆስፒታል ተኝተዋል›› የሚል ወሬ ከተማ ውስጥ ተናፈሰ፡፡ ከአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ሊያመልጡ ነበር የተባሉ ከ8 የሚበልጡ እስረኞች ሲገደሉ በርካታዎች ቆሰሉ፡፡ እስከ ህዳር 4 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስም የሟቾቹ አስከሬን ያልተረከቡ ወላጆች እንደ ነበሩም በጊዜው የተገለፀ ነዉ፡፡

በየመሥሪያ ቤቱም በረብሻው ሰሞን በትራንስፖርት ችግርና በፀጥታው ስጋት ምክንያት ከሥራ ገበታቸው ላይ ያልተገኙ ከሥራ ትባረራላችሁ መሰል የማስፈራሪያና የዛቻ መልዕክት እንዲርሳቸው ተደረገ፡፡ በመርካቶ የሚገኙ የንግዱ ማህበረሰብ አባላትም በከተማው የተፈፀመው ሁከትና ግርግር በመፍራትና የመንግሥትን ያልተመጣጠነ እርምጃ በመቃውም ሱቃችን አንከፍትም በማለታቸው ሱቃቸው ታሽጐባቸዋል፡፡ እንዲከፈትላቸውም ወደ ሚመለከታቸው አካሎች ቢሄዱም አቤት ቢሉም በመጀመሪያ አቋም ገልፃችሁና ቅንጅትን የሚያወግዝ አስተያየትን ጨምሮ ከእናንተ ማህል ፓርቲውን የሚደግፍ አጋልጣችሁ ስጡ በሚል ለተነሳባቸው ትዕዛዛዊ ጥያቄ ምላሽ ሳይሰጡ ለበርካታ ቀናት ከርመዋል፡፡

ይኽን አሳዛኝና ሌላም ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶችን ያጋልጡ የነበሩ የነፃ ፕሬስ አባላትንም ሥራ ታሪክ ምንጊዜውም አይረሣቸውም፡፡ በዚህ የመረጃ ምንጭነታቸው በእጅጉ የተከፋው ኢህአዴግም የነጻ ፕሬሱን ስራ ሙሉ በሙሉ አገደው፡፡ የተወሰኑ ጋዜጠኞችንም ወደ ወህኒ ወረወረ፡፡ ሕዝብ የመረጃ ምንጭ ባጣበት አጋጣሚም ቁጭቱ የነበራቸው የመንግሥት ኤሌክትሮኒክስ ህትመት ሚዲያ (በወ/ሮ ሚሚ ስብሐቱ ባለቤት በዋና አዘጋጅነት ይመራ የነበረው ኢፍቲንን ጨምሮ ከፍተኛ የሆነ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ከፈቱ፡፡ ወ/ሮ ሚሚም በኤፍ ኤም የራዲዮ ስርጭታቸዉ በኩል ቀደም ስል የኢነጋማ ፀሐፊ የነበሩትን አቶ ወንድወሰን መኮንንና በአሁኑ ጊዜ የጋዜጦች ህብረት ሊቀ መንበር ነኝ የሚሉትን አቶ አንተነህ አብርሀ፤ (እኚህ ሰዉ የአትሌትክስ ፌዴሬሽን አቃቤ ንዋይየአቶ አማኑኤል አብረሀ ወንድም ናቸው) ጨምሮ ሌሎች እንግዶችን በመጋበዝ በነጻው ፕሬስ መቃብር ላይ አበባ ለማስቀመጥ በጅጉ ተረባርበዋል)፡፡

### በግፍ የሞቱ ወገኖች

በከተማችን ውስጥ አስከሬናቸው ሆስፒታል ሳይደርስና ቤተሰብ ወደቤቱ የወሰዳቸው ተጠሪዎች ያልተገኙላቸው (ተገለው በመንግሥት ኃይሎች የቀበሩትን) ቁጥር ሳይጨመር ከ46 በላይ ንፁሓን ዜጐች ተገለው ከ100 በላይ በጥይትና በድብደባ መቁሰላቸዉ ተገለፀ፡፡ ከነዚህም መሐል ከብዙዎቹ መሀል ጥቂቶችን እንቃኝ፡፡

ተዳጊው ሕፃን ሰይድ ኑረዲን ይባላል፡፡ ነዋሪነቱ በወረዳ 6 ቀበሌ 25 ቤት ቁጥር 1081 ሲሆን የ6ተኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ ጥቅምት 22 ቀን ከቀኑ 8፡00 መኖሪያ ቤቱ አጠገብ ካለች ትንሽ ሜዳ ከጓደኞቹ ጋር ኳስ በመጫወት ላይ እንዳለ የፌዴራል ፖሊሶች ድንገት ሲመጡ የሰፈሩ ሕጻናት እየተንጫጩ ወደ ቤታቸው ይገባሉ፡፡ ኳስ የሚጫወቱትም እንዲሁ፡፡ ኳሷንም ትቶ ለመሄድ የሕፃን ልቡ ያልፈቀደለት ሰዒድ ግን ኳሷን ለማንሣት ባጐነበሰበት ወቅት በሁለት ሜትር እርቀት ላይ የነበረ የፀጥታ ኃይል በጥይት ገሎታል፡፡ የአረሯንም ቤት (ቀለሃ) የሠፈሩ ልጆች መሬት ላይ ወድቆ አግኝተውታል፡፡

በሕፃኑ መሞት ወላጅ እናቱ እታፈራሁ ገዛኸኝ ሕሊናዋ ክፉኛ ቆስሏል፡፡ እንባዋ እንደጐርፍ ወርዷል "ልጄን አስተምሬ ሰው ይሆንልኛል በማለት ከዛሬ 8 ዓመት በፊት ነው ከሀገር የወጣሁት ልፋቴና ዕቅዴ ሁሉ መና ቀረ፡፡ እንደናፈኩት አይኑን እንኳን ሳላየው ሞተብኝ" በማለት በጊዜው ተናግራለች፡፡ እናት ለልጇ ቀብር እንድትደርስ ካለችበት የመን ድረስ ስልክ ቢደወልላትም ለቀብር ሳትደርስ ቀርታለች፡፡

ወጣት ስንታየሑ ውበት መለስ ዕድሜው 20 ሲሆን ነዋሪነቱ በወረዳ 6 ቀበሌ 10 በቤት ቁጥር 268 ነው፡፡ አማኔኤል አጂፕ አካባቢ በ22/21/98 ጧት በጥይት ተመቶ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል SICU ውስጥ ክፍል ቁጥር 404/5 ተኝቶ የነበረ ቢሆንም ምሽት አንድ ሰዓት ላይ ህይወቱ አልፋለች፡፡ በእለቱም እህቱ ተማሪ ልኪቱ ውበት ተደብድባ ተወስዳ ታስራለች፡፡

ተማሪ መቆያ መብራቱ ታደሰ ነዋሪነቱ በወረዳ 22 ቀበሌ 01 ቤት ቁጥር 561 የሆነና የ10ኛ ክፍል የጥቁር አንበሳ ተማሪ የነበረ ሲሆን በ23-2-98 ከጧት 4፡30 መኖሪያ ቤቱ አካባቢ እያለ በጥይት ተመቶ ሞቶአል፡፡ የቀብሩ ሥነ ሥርዓትም አየር ጤና ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡

ስለግፍ አገዳደሉ አክስቱና አሳዳጊው ወ/ሮ መሰሉ ሽጋው ሲናገሩ "እናት አባቱ በሕይወት የሉም፡፡ እንደወላጅ ሆኜ ያሳደኩት እኔ ነኝ፡፡ ተምሮ ቁምነገር ላይ ይደርስልኛል፡፡ ያልኩት ልጄ ምኑም ውስጥ ሳይኖርበት በቆመበት በገዛ ወገኖቹ ጥይት ተገደለብኝ፡፡ ቁርጡ የታወቀው ጣላት ገሎት ቢሆን ኖሮ እንዲህ ባላንገበገበኝ" ሲሉ መሪር ሀዘናቸዉን ገልፀዋል፡፡

አቶ ክብረት በድሉ እልፍነህ እድሜያቸው 40 ሲሆን በአንድ የግል ድርጅት በጥበቃ ሠራተኝነት ተቀጥረው ይሰራሉ፡፡ መኖሪያቸውም ወ 4 ቀን 37 ቤት ቁጥር 841 ነው፡፡ የአራት ልጆችም አባት ናቸው፡፡ ከወ/ሮ ደብሬ ገ/ሕይወት ጋር በትዳር ዓለም ረጅም ዓመታትን አሳልፈዋል፡፡ ባለቤታቸው ከመጣወ ለቅሶ ደራሽ ጋር ሁሉ እንደ አዲስ ይላቀሳሉ፡፡ አቶ ክብረት የተገደሉት በጥይት ሳይሆን የጊቢያቸው በር ላይ እንደቆሙ በፀጥታ ኃይሎች መሬት ከተጣሉ በኋላ ብልታቸውንና የዘር ፍሬያቸውን በጫማ በመምታትና በማሸት መሆኑን በቅርብ የነበሩ የአካባቢው ነዋሪዎች ይመሰክራሉ፡፡

ወጣት ዮሴፍ ሙሉጌታ ዕድሜው 17 ነዋሪነቱ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 03 ቤት ቁጥር 3 711 የሆነ ራሱን በራሱ በታክሲ ረዳትነት ተሰማርቶ የሚያስተዳድር የነበረና ወላጅ የሌለው ሲሆን አየር ጤና አካባቢ በፀጥታ ኃይሎች በተተኮሰ ጥይት ጭንቅላቱን ተመቶ ህይወቱ አልፏል፡፡

ነዋሪነታቸው በወረዳ 5 ቀበሌ 23 የሆኑትና የሁለት እንስት መነኩሴዎች እናት ወ/ሮ ብርዞም ከቤተክርስቲያን ፀበል ይዘው በሚመጡበት ወቅት ወደ ሰፈራቸው መግቢያ ላይ አንድ ሰው በጥይት ሲገደል አይተው ገዳዩን "ሰው ለምን ትገላለህ" በማለታቸው እሳቸውንም በጥይት ገሏቸዋል፡፡ እኝህን መሰል እናቶችም ወደ ፈረንሳይ ለጋሲዮንና መርካቶ ክልል ተገለዋል፡፡ በአሁኑ ዘመቻ ግድያውና ድብደባዉ ግዞቱ እናቶች አዛውንቶችና ወጣት ሴቶች እንዲካተቱ ያተደረገው ሌላ ጊዜ ረብሻ እንዳይነሳ የቤተሰቡን አባላት ይመክራሉ ያስጠነቅቃሉ በሚል ስሌታዊ ግምት የተሠራ መሆኑን ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ውስጥ አዋቂ የደህንነቱ ተንታኞች በጊዜው መናገራቸው አይዘነጋም፡፡

## ከውጭ የሚላከው. . .

ከገፅ 12 የዞረ

ነው፡፡ ረሀብ ብቻም በቂ የማይሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ረሀብ ያለ መሠረታዊ ንቃተኅሊና ሕዝባዊ አመፅን ላይቀሰቅስ ይችላል፡፡ በሀገራችን ረሀብ ብዙ ጊዜ ወደ ልመና ነው የሚያመራው፡፡ ይሁንና ለምሳሌ የአዲስ አበባ ወጣቶች በመጠኑም ቢሆን የንቃተኅሊና ደረጃቸው ከፍ ያለ እንደመሆኑ የመሠረታዊ ፍላጐታቸው አለመሟላት ወደ ሕዝባዊ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ሊያመራ የሚችልበት ዕድል አለ፡፡ ይሁንና ከረሀብም የከፋ ነገር አለ፡፡ ይኼውም ሞት ነው ለምሳሌ አንድ መጠነኛ ንቃተኅሊና ያለው የአዲስ አበባ ወጣት ስለተራበ አደባባይ ወጥቶ ያስራበውን መንግሥት ከተቃወመ በጥይት ተደብድቦ የሚገደል ከሆነ ንቃተኅሊናው በቂ ቢሆን እንኳ "ከመሞት መሰንበት" በማለት ከዓመጽ እንደሚቆጠብ መገመት አያዳግትም፡፡ እርግጥ አንዳንድ እንደ የኔሰው ገብሬ ያሉ ንቃተኅሊናቸው ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ ሰዎች ከረሃብ በመለስ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችን ተጥሰዋል በማለት ብቻ ሞትን ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ በቡዲስቶች ዘንድ የምናየው መስዋዕትነት ነው፡፡ የቱኒዚያው ቦአዚዚዝን መስዋዕትነት የምናየው ከዚሁ አኳያ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ ታጠቅ ህሉፍንም እንደዚሁ

ከውጭ የሚላከው ሐዋላ የመሠረታዊ ፍላጐቶች አለመሟላት ሥጋትን በከፍተኛ ደረጃ ቀንሶታል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ከ8-10 ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የሐዋላ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ከሐዋላ ተጠቃሚ የሆኑት ወጣቶች ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም ጠንካራ የፖለቲካ ጥያቄ ቀስቃሽ የሆነውን የኢኮኖሚ ችግር አለዝቦታል፡፡ ወጣቶቹ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ፍላጐቶቻቸው ከተሟሉላቸው፣ ለዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው መከበር ብለው ከፍተኛ መስዋዕትነት መክፈል የሚፈልጉ አይመስልም፡፡ ሐዋላ ወጣቶቹ እንዳይራቡ በማድረግ ይበልጥ እንዳይነቁም አድርጐአቸዋል፡፡ አሁን የምናየውም የፖለቲካ ደንታ ቢስነታቸው የሚመጣው ከዚህ መሠረታዊ ሐቅ ይመስለኛል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ የኢህአዴግ መንግሥት ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ከመጣስም አልፎ እያስራበን ነው፡፡ ሐዋላ ባይኖር ኖሮ የረሀብተኛው ቁጥር በእጅጉ ይጨምር ነበር፡፡ ይህም ሰላማዊ ትግሉን ያጠናክረው ነበር፡፡ ኢህአዴግ ራሱ ርሃብ እንዳይከሰት በደመወዝም በአበልም መልክ ለሕዝቡ ትንሽ ትንሽ ገንዘብ እየሰጠ ነው፡፡ ግን የሚሰጠው ገንዘብ መሠረታዊ ፍላጐቶችን እንኳን የሚያሟላ ባለመሆኑ በቅርቡ ሦስት መቶ ሃምሣ ሺ መምህራን እስከ ሥራ መቆም አድማ የዘለቀ ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ ሞክረዋል፡፡ ሐዋላ ባይኖር ኖሮ ትግሉ ምን ያህል ይጠነክር እንደነበር መገመት አያዳግትም፡፡

የመምህራኑን ሰላማዊ ትግል የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የመንግሥት እና የግል ሠራተኞች እና ሰፊው ሥራአጥ ሕዝብ ቢቀላቀሉት ኖሮ አሁን እያሳየ እንዳለው የመፍረክረክ አዝማሚያ አያሳይም ነበር፡፡

ውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያውያን ሕልውና ለዴሞክራሲያዊ አንድነት እና የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ያደረጉት ከፍተኛ ተጋድሎ በኢትዮጵያ ታሪክ በወርቅ ቀለም የሚፃፍ ለመሆኑ አንዲት ደቂቃ እንኳን አልጠራጠርም፤ ግን አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት ሀገር ቤት ላሉት ዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸው የሚልኩት ሐዋላ ሰላማዊ ትግሉን በማቀዝቀዝ ረገድ ቀላል የማይባል ሚና እየተጫወተ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለውጭ ምንዛሪ የሚልኩት ሐዋለ ለሕዝቡ የሚደርሰው በኢትዮጵያ ብር እንደመሆኑ በባንክና ባሐዋላ አስተላላፊ ድርጅቶች በኩል የሚላከውን የውጭ ምንዛሪ የሚወስደው አምባገነኑ የአቶ መለስ መንግሥት ነው፡፡

ስለዚህ ውድ ሀገራችንን ሻዕቢያ እና ወያኔ ከቀየሱት የጥፋት ሴራ ለመታደግ ስል በመጠኑም ቢሆን ጭካኔ የሚታይባቸው የመፍትሄ ሃሳቦች ሳቀርብ እንደማትታዘቡኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ የመፍትሄ ሃሳቦቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ዲያስፖራው ወደ ሀገር ቤት ለዘመድና ወዳጅ የሚልከውን በዓመት ወደ 60 ቢሊዮን ብር የሚገመተውን ሐዋላ ቢያንስ በ20 በመቶ እንዲቀንስ

2. ከ60 ቢሊዮን ብር ሐዋላ ተቀናሽ የሚሆነው ወደ 12 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ገንዘብ ለሐቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲልክ ቢያደርግ

3. ሐቀኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከሐዋላ ተቀንሶ የሚላክላቸውን ገንዘብ ሕዝቡን ለማንቃት ለማደራጀትና ለሰላማዊ ትግል ለማንቀሳቀስ እንዲጠቀሙበት፤ ለዚህም አስፈላጊዎቹን ሥራአጥ ወጣቶች በደመወዝ ቀጥረው እንዲያሰማሩ ቢያደርጉ

4. ዲያስፖራው የሚልከው ሐዋላ በተቻለ መጠን ከባንክ እና ከሐዋላ አስተላላፊ ድርጅቶች ውጪ እንዲሆን በማድረግ አምባገነኑ የአቶ መለስ መንግሥት ኪስ የሚገባውን የውጭ ምንዛሪ እንዲቀንስ ወይም እንዲያስቀር ቢደረግ ይችን ሀገር እንደ ሀገር ጠብቆ በማቆየትና የሕዝቡን ሰቆቃ ለመታደግ መሠረታዊ መፍትሄ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

# አንተነህ ሙሉጌታ ለአንድነት ፓርቲ እርዳታ ሰጡ

በአውስትራሊያ በትምህርት ላይ የሚገኙት አቶ አንተነህ ሙሉጌታ ለአንድነት ፓርቲ ማጠናከሪያ በቅርቡ ካሳተሙት መጽሐፍ እርዳታ መስጠታቸውን የፓርቲው ህዝብ ግንኙነት ክፍል ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቀ፡፡ ህዝብ ግንኙነት ክፍሉ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፀው "አቶ አንተነህ ሙሉጌታ የሁለት ዓለም ሰዎች የተዋረደው ፍ/ቤት በሚል ርዕስ ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ ለእስር የተደረጉት የቅንጅት አመራሮች አባሎችና ደጋፊዎች የፍርድ ሂደትን የሚያሳይ መጽሐፍ ለፓርቲው ሰጥተዋል፡፡" ብለዋል፡፡

እንደ ህዝብ ግንኙነቱ መረጃ "እስከ አሁን ድረስ ከ800 በላይ መጽሐፍ ፓርቲው የተረከበ ሲሆን በቅርቡም ተጨማሪ መጽሐፍቶችን ገቢ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡" ብለዋል የህዝብ ግንኙነት ክፍሉ አያይዞም ሲገልፁ "አቶ አንተነህ በተጨማሪም ፓርቲው ወደፊትም መጽሐፉን አሳትሞ እንዲጠቀም ፈቅደዋል፡፡" ሲሉ አስታወቀዋል፡፡

አቶ አንተነህ ሙሉጌታ በምርጫ 97 ቅንጅትን ወክለው አዲስ አበባ ወረዳ 19 የምርጫ ጣቢያ ላይ ለአዲስ አበባ ም/ቤት ከተመረጡ በኋላ ሥልጣን ያልተረከበው የአዲስ አበባ ም/ቤት የም/ቤቱ ዋና ፀሐፊ አድርጎ መርጮአቸው ነበር፡፡ አቶ አንተነህ ወደ ኢዴፓ /ቅንጅት/ ከመደራጀታቸው በፊት የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኛ ሆነው ያገለግሉ የነበሩ የህግ ባለሞያ ናቸው፡፡ የቅንጅት አመራር አባላትንና የደጋፊዎችን የፍርድ ሂደት ሞያዊ ትንተና የሰጡበት "የተዋረደው ፍ/ቤት" መጽሐፍ ከፍተኛ ተነባቢነትን አትርፏል፡፡ መጽሐፍ በገበያ ላይ የሚገኝ ሲሆን በአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤት ውስጥ እየተሸጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል፡፡

የአንድነት ፓርቲ የህግና ሰብአዊ መብት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ "መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች" በሚል ርዕስ የህግ ባለሙያ በመጋበዝ የውይይት መድረክ አዘጋጅቶአል፡፡
ውይይቱ የተዘጋጀው ለ23ቱም የወረዳ አንድነት አመራርና ለቋሚ ኮሚቴዎች አባላት በሙሉ መሆኑን ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡
ቀን እሁድ ግንቦት 5/2004 ዓ.ም

ሰዓት ከጠዋቱ 3፡00 ጀምሮ
ቦታ አንድነት ፓርቲ ዋናው ጽ/ቤት
የአንድነት ፓርቲ የህግና ሰብአዊ መብት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ

## የሻማ ምሽት ጥሪ

ዓርብ ግንቦት 3 ቀን 2004 ዓ.ም በኢትዮጵያ የሚገኙ የፖለቲካና የህሊና እስረኞችን አስመልክቶ የሻማ ማብራት ዝግጅት በአንድነት ፓርቲ ፅ/ቤት ይካሄዳል፡፡ የተለያዩ ዝግጅቶችም ይቀርባሉ፡፡ ስለዚህ በእለቱ የህሊናና የፖለቲካ እስረኞችን ለማሰብ የምትፈልጉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ተጋብዛችሁዋል፡፡

ቦታ፡- በፅ/ቤት
ሰዓት፡- ከ11 ሰዓት ጀምሮ

# በነፃ አስተሳሰብ ላይ...

ከገፅ 2 የዞረ

ሌሎችም) የህዝብ አመኔታ ማጣት፣ የዜግነት ክብርና መብት ማጣት፣ የገዥው መንግስት አምባገነንነት እየጨመረ መሄድ፣ ሀገሪቱን ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይከታት የሚሰጉ አልጠፉም፡፡ ይህንንም በአፈናና በርሃብ የሚተገበር "የጦር መሣሪያ የሌለበት ሽብር ጥቁር ሽብር" ነው ይላሉ፤የነፃ አስተሳሰብ በር መዘጋቱንም በመግለፅ፡፡

አሁን ባለው የኢህአዴግ አካሄድ አገዛዙ ማብቃቱን በመጠቆም አመራሮቹ በተለያየ መንገድ ባለባቸው ሀገር የመምራት ብቃት ማነስና ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሳቸውን ስልጣን ላይ ለማቆየት ሲሉ የተለያዩ አስከፊ ስልቶችን በመቀየስ ህዝቡ ላይ ርምጃ ሊወስዱም እንደሚችሉ የሚጠቁሙ ሁኔታዎች እንዳሉ ይነገራል፡፡

ለዚህም አማራጭ አድርገው ይወስዳሉ የተባለውም የአንዱን ማኅበረሰብ ባህልና ወግ ሌላው እንደናቀ አድርጎና አስመስሎ በመናገር፣ አንዱን የኃይማኖት ተከታይ በሌላው ላይ ማነሳሳትና ፍርሃት መፍጠር፣ አንድ ቋንቋ ተናጋሪ ላይ ሌላውን ማስነሳት፣ ባለሃብት ነጋዴዎች ላይ ደግሞ ሌላ ባለሃብት ራሳቸው በመፍጠር ከንግድ ዓለም በተለያየ መንገድ እንዲወጡ ማድረግ እና አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ የእርሻ ግብዓቶችን (ማዳበሪያና ዘር) በውድ ዋጋ ከኢህአዴግ የንግድ ድርጅቶች እንዲወስዱ በማስገደድ የሚወስዱት ርምጃ ሊኖሩ እንደሚችል በመጠቆም፤ ይህም ከወዲሁ እየተተገበረ እንዳለና ወደፊትም ሊቀጥል እንደሚችል ይገመታል፡፡

በተለይ ለኢህአዴግ ስጋት ሆነዋል የተባሉት በጥቂቱ ባሉት ህጎችም ቢሆን እየተንቀሳቀሱ ያሉ ጋዜጦች (ከመንግስት ውጭ) በቀጥታ ከመዝጋት ይልቅ ገዥው መደብ በማተሚያ ቤቶች አማካኝነት ከገበያ ውጭ ለማድረግና ለማስቀረትም እየታሰበ እንዳለ አንዳንድ መረጃዎች እየጠቆሙ ነው፡፡

የነኚህ ሂደቶችም መንግሥት በመጪው 2005 ዓ.ም ለሚካሄደው የአዲስ አበባ ምርጫና የህዝቡን የታፈነ ዝምታ ለመግታት ታስቦ ከወዲሁ አፋኝ ድርጊቶችን ሊፈፀም እንደሚችል ይገመታል፡፡ በተለይ ለኢህአዴግ ስጋት ይሆናሉ(ለኢትዮጵያ ያይደለ) ተብለው ከላይ የተጠቀሱት የሚተገበሩ ከሆነ መጪው ጊዜ ለኢትዮጵያ መጥፎ (አስከፊ) ነው፡፡ ምናልባትም በሀገሪቱ ይታያል ተብሎ የሚታሰበው የዴሞክራሲ ጭላንጭል ፍፃሜው ይሆንና ሀገሪቱ ያልታሰበ አዘቅት ውስጥ ልትገባ ትችላለች፡፡ ህዝቡም ሆነ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ወደ ዴሞክራሲያዊ አካሄድ የሚያመሩ መንገዶች ከተዘጉና ወደ ሌላ የትግል ስልት ያመራና ታሪክ ሊደገም ይችል ይሆናል፤ግን ባይሆን ይመረጣል፡፡

ከላይ በተጠቀሱ ሐሳቦች ምክንያትም ሀገሪቱ ከፍጹማዊ አምባገን አገዛዝ "በምርጫ" ወደ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ እያመራች ነበር ቢባልም ቀጣዩ ጉዞ የባሰ እየሆነ እንደመጣ ይገመታል፡፡ ይህም ኢትዮጵያ አንድ ወደፊት ሁለት ወደኋላ እየተጓዘች እንደሆነ እያመለከተ እንደሆነ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም ሀገሪቱንና ህዝቦቿን ወደ ጨለማ ጉዞ ውስጥ እየከታት ነው በማለት ስርዓቱን ተጠያቂ የሚያደርጉ ዜጐችም እየተበራከቱ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የቀረበው የኢህአዴግን አምባገነንነት በግልፅ የሚያረጋግጥ እንደሆነ በመጠቆም በተለይ በነፃ አስተሳሰብ ላይ የተቃጣ ጥቁር ሽብርና በፕሬስ ላይ የታወጀው የመጨረሻው ዘመቻ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማሳያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

# አንድነት በደቡብ . . .

ከገፅ 1 የዞረ

በመምታት እጁ ላይ ጉዳት ማድረሱ ተገልፃል፡፡

ህዝቡ ወደ አዳራሽ ከገባ በኋላ የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች ሲገቡ ወዲያውኑ ሌሎች ሰዎች እንዳይገቡ የግቢውን አጥር በር በሰንሰለት መቆለፋቸው የተጠቆመ ሲሆን ህዝቡ ባሳየው ቆራጥነት ሊሰናከል የነበረው ውይይት በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁ ታውቋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሚያዝያ 28 ቀን 2004 ዓ.ም ደግሞ በጋሞ ጐፋ ዞን አርባምንጭ ከተማ በፖሊስ አዳራሽ በተመሳሳይ መልኩ ውይይት መካሄዱ ታውቋል፡፡ በተለይ በአርባ ምንጭ ለነበረው ውይይት የአዳራሽ ፈቃዱ እንዳለቀ እየታወቀ አዳራሹን ለባዛር ብለው ሸንሽነውት እንደነበርና ህዝቡም ሜዳ ላይ እንወያያለን ብለው ስብሰባው ከተጀመረ በኋላ ወደ አዳራሹ እንዲገቡ መፈቀዱ ተጠቁሟል፡፡

በሁለቱም አካባቢዎች ህዝቡ በነፃነት መወያየቱንና በርካታ ጥያቄዎችም የጠየቀ ሲሆን ከፓርቲው አመራሮችም ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በውይይቱ አብይ ርዕስ የነበሩት አዲሱ የከተማ ቦታ ሊዝ አዋጅ፣ ምጣኔ ሀብት (ኢኮኖሚ)ና ሌሎች ወቅታዊ የሀገሪቱ ጉዳዮች ላይ መወያየታቸው ታውቋል፡፡

ተሳታፊው ህዝብም ለውጥ እንደሚፈልግና በስቃይ ላይ መሆኑን በመግለፅ የተበታተናችሁ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለህዝብና ለሀገር የምትሰሩ ከሆነ ለምን አንድ አልሆናችሁም? ጠንክራችሁ ለመሄድ ምን ያህል ዝግጁ ናችሁ? ወደገጠሩ ማኅበረሰብ በመውረድ ገበሬውን ለምን አታወያዩም? በፖሊሲያችሁ ዙሪያ ለምን እንደዚህ እየተንቀሳቀሳችሁ አትገልፁም? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተው ከመድረኩ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡በተጨማሪም የፖለቲካ አመራሮችን ለስልጣን ከመሮጥ ጥርጊያውን ማመቻቸት እንዳለባቸው በመጠቆም ለነፃነት መስዋዕት የከፈሉት ኔልሰን ማንዴላንና የእንግሊዙን ገበሬ ፈለግ መከተል እንዳለባቸው ተጠቁሟል፡፡

በተለይ በመሬት ፖሊሲ ዙሪያ አንድነት ፓርቲ መሬት የግል ፤የህዝብና የመንግስት ይሆናል ብሏልና ግልፅ አድርጉልን ብለዋል፡፡ የፓርቲው አመራሮችም በግል ይዞታ ያለው የከተማና የገጠር መሬት የራሱ የባለቤቱ የግል ንብረት እንደሆነ ፤የህዝብ የተባለው ደግሞ ህዝቡ ለጋራ እሴቶች፣ ለግጦሽና ለመዝናኛ ሜዳ የሚጠቀምባቸው የአካባቢው ህዝቡ የጋራ ንብረት መሆኑንና የመንግሥት የተባለውም ብሔራዊ ፓርኮችና በግለሰብም ሆነ በህዝብ ያልተያዙ ቦታዎች በመንግስት ስር ይሆኑና ለህዝቡ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ አመራሮቹ አብራርተዋል፡፡ በሁለቱም የውይይት ቦታዎች ላይ በሺህዎች የሚቆጠሩ ተሳታፊዎች መገኘታቸውና በመጨረሻም ውይይቶቹ በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቃቸው ታውቋል፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
የገቢ ማሰባሰቢያ የራት ፕሮግራም

አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየታገለ ይገኛል፡፡ ለትግሉ ስኬት የእርስዎ ድጋፍ ወሳኝ ነው፡፡

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ የራት ዝግጅት ፕሮግራም አዘጋጅቷል፡፡ ለመግብያ ባለ 1,000፣ 500ና 300 ብር መግቢያ ካርዶች ተዘጋጅተዋል፡፡

በራት ፕሮግራሙ ላይ ታዋቂ ግለሰቦች ንግግር ያደርጋሉ፡፡ የእራት ግብዥው ግንቦት 25 ቀን፣ 2004 ዓ.ም. ይደረጋል። የሆቴሉ ስም ግንቦት 13 ቀን 2004 ዓ.ም. በሚወጣው ፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ላይ ይገለፃል፡፡

በውጭ ሀገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያኖች በሀገር ውስጥ በሚኖሩ ቤተሰቦችና ጓደኞች አማካኝነት ካርዱን መግዛት ትችላላችሁ፡፡

ለተጨማሪ መረጃና ካርድ ለመግዛት በሚከተለው አድራሻ ይጠቀሙ፤
በቢሮ ስለክ ቁጥር 011-840-08-11
በተንቀሳቃሽ ስልክ 091-161-84-34
ኢ-ሜል፡
andientfinance@yahoo.com
ወይም andinet@andinet.org

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
የሂሳብ ቁጥር፡ 510
ንብ ባንክ ዑራኤል ቅርንጫፍ

ለዴሞክራሲ ስርዓትና ለህግ የበላይነት መመስረት፣ ሁላችንም ካርዱን በመግዛት ድርሻችንን እንወጣ!